

የጤናው ዘርፍ የደረሰበትን ደረጃ ያሳየ አውደ ርዕይ

ገጽ 8



የአልኮል መጠጥ ሱሰኝነትና መዘዙ

ገጽ 16


# አዲስ ዘመን

82ኛ ዓመት ቁጥር 287 ሰኔ 17 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## “ወጣት ሴት ዲፕሎማቶችና አምባሳደሮች ፈተናዎችን ተቋቁመው ስኬታማ ለመሆን ጥረት ማድረግ አለባቸው”

- ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ:- ወጣት ሴት ዲፕሎማቶችና አምባሳደሮች በሥራቸው በሚገጥሟቸው ገፊ ምክንያቶች ተስፋ ሳይቆርጡ ፅናትን በመላበስ ስኬታማ ለመሆን ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ አሳሰቡ::

ዓለም አቀፍ የሴቶች የዲፕሎማሲ ቀንን ምክንያት በማድረግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትናንት ባዘጋጀው መርሃግብር ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለም አቀፍ የሴቶች የዲፕሎማሲ ቀን ሰኔ 17 እንዲከበር ማጽደቁ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሴቶችን ውክልና ለማረጋገጥና በዲፕሎማሲው ዘርፍ ያላቸውን ሚና ለማሳወቅ

“ወጣት ሴት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በዓመት ከ10 ሺህ በላይ ትራክተሮችን ማምረት የሚችል ፋብሪካ በሞጆ ከተማ ሊገነባ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ:- ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ በዓመት ከ10 ሺህ በላይ ትራክተሮችን ማምረት የሚችል ፋብሪካን ለመገንባት ከቻይናው ኩባንያ "ዋይ ቲ ኦ" ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ::

የኢትዮ ኢንጅነሪንግ ግሩፕ ዋና ስራ አስፈፃሚ አምባሳደር ሱሌይማን ደደፎ እና የ"ዋይ.ቲ.ኦ" ኩባንያ ፕሮጀክት ማናጀር ዋንግ ሰን የተፈራረሙት በትናንትናው ዕለት ነው::

የኢትዮ ኢንጅነሪንግ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አምባሳደር ሱሌይማን ደደፎ በፊርማ ሥነሥርዓቱ

በዓመት ከ10 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “የመሠረተ ልማት ተቋማት ተቀናጅተው ባለመሥራታቸው የአገር ሀብት ለብክነት እየተዳረገ ነው”

- የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች

## “የቅንጅት ችግሩን ለመፍታት ተቋማቱ የጋራ ስምምነት አድርገዋል፤ ማስተር ፕላንም እየተዘጋጀ ነው”

- የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር

ገጽ 4

## በሲዳማ ክልል ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን የጸጥታው ዘርፍ መዋቅራዊ ሪፎርም እየተካሄደ ነው

- 157 የፖሊስ አመራርና አባላት ከሥራ ተሰናብተዋል

ገጽ 4
















# የተጀመሩ የኤሌክትሪክ ማስፋፊያዎች በፍጥነት እንዲጠናቀቁ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የተጀመሩ የኤሌክትሪክ ማስፋፊያዎች በፍጥነት መጠናቀቅ እንዳለባቸው የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ፡፡

የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የአገልግሎት ዘርፍ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢና የቡድኑ አስተባባሪ የተከበሩ ወይዘሮ መአዛ ጥጋቤ ተቋሙ በ10 ዓመት የልማት ዕቅዱ ላይ መብራት ለሁሉም ለማድረስ እየሰራ ያለው እንቅስቃሴ እንደ አገር ያለው ሚና ከፍ ያለ በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

የተከበሩ ወይዘሮ መአዛ አክለውም ኮርፖሬሽኑ በአማራ ክልል ከፍተኛ የኃይል እጥረት በመኖሩ የአካባቢውን ማህበረሰብ የመብራት ተጠቃሚ ለማድረግ የኃይል ማከፋፈያ ግንባታ በባህር ዳርና ከአዘዞ-ጭልጋ፣ ከባህር ዳር-ወልድያ፣ ከአዘዞ-ዳንሻ ባከር ሁመራ፣ ከባህርዳር-ቡሬ-ደብረ ማርቆስ እና ሌሎች የማስፋፊያዎች ሥራዎች በተቀመጠላቸው እቅድ እየተፈፀሙ ባለመሆኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በሥራ ላይ የሚከሰቱ ተግዳሮቶችን በፍጥነት በመፍታት ተጠናቀው የሕዝቡን የመብራት ጥያቄ መመለስ እንዳለባቸው አሳስበዋል።

አያይዘውም በአማራ ክልል ባሉ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የሚኖረው የገጠር ከተሞች እና ቀበሌ አርሶ አደር መብራት እንደማያገኝ አስታውሰው፤ ተቋሙ የችግሩን ስፋት እና የሕዝቡን ቅሬታ በመገንዘብ የኃይል አቅርቦቱን ሰብስቴሽን በመገንባት የኤሌክትሪፊኬሽን ማስፋፊያን ሥራዎች አቅዶ በመፈፀም ፍትሐዊ ተደራሽነትን በማስፋን የአካባቢው ሕዝብ የመብራት ተጠቃሚ ማድረግ እንዳለበት ተናግረዋል።

የመብራት ኃይል ፕሮጀክቶችን ጀምሮ የመጨረስ ችግር ስላለ በ18 ወራት ለመጨረስ ውል የተገባላቸው የመብራት ፕሮጀክቶች ከ4 እስከ 5 ዓመታት ስለወሰዱ ፕሮጀክቶችን አጠናቆ ሕዝቡን የመብራት ተጠቃሚ የማድረግ ችግር እንዳለም ቡድን አስተባባሪዋ ጨምረው አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሙላት ገዛኸኝ በበኩላቸው የመብራት መስመሮችን ለመዘርጋት የወሰን ማስከበር፣ ካሳ በወቅቱ የመገመት ችግርና የሲሚንቶ እጥረት ለፕሮጀክቶቹ መጓተት ምክንያት መሆኑን ጠቅሰው፣ ብሔራዊ ባንክ ኤሊሲ በወቅቱ ባለመከፈቱ ከውጭ የሚመጡ ዕቃዎችን አምጥተው ፕሮጀቶችን ለማጠናቀቅ እንቅፋት እንደነበረ ገልጸዋል፡፡

አቶ ሙላቱ፤ አክለውም ካሳ የተከፈላቸው ሰዎች መነሳት ሲገባቸው በተለያየ ምክንያት ባለመነሳታቸው የኤሌክትሪክ መስመር ለመዘርጋት መቸገራቸውንና ሲሚንቶ በወቅቱ አለማግኘት ለፕሮጀክቶች መጓተት ምክንያት በመሆኑ ቋሚ ኮሚቴው የበኩሉን ድጋፍ ሊያደርግላቸው እንደሚገባ ጠይቀዋል።

የቡድን አባላቱም በበኩላቸው በአካባቢው ያለውን የካሳ ክፍያ ችግር ለመፍታት ከክልል፣ ከዞን፣ ከወረዳና ከቀበሌ አመራሮች ጋር በትብብር መሥራት ቢቻል ችግሩን ሙሉ በሙሉ ማስቆም ባይቻል እንኳን መቀነስ እንደሚቻል አስረድተዋል።

አክለውም የሲሚንቶ ችግርን ለመፍታትም ከሲሚንቶ ፋብሪካዎች ጋር በመነጋገር ችግሩ መፍታት እንደሚቻል ጠቁመው፤ ችግሩ አሳሳቢ በመሆኑ ቡድኑ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሪፖርት በማቅረብ ችግሩ እስኪፈታ ድረስ ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተል መሆኑን ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያገኘነው መረጃ አመላክቷል።




# ዘምዘም ባንክ አጠቃላይ የሀብት መጠኑ 6 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ደረሰ

## . የቅርንጫፎቹ ቁጥር 75 ደርሷል

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- ዘምዘም ባንክ አጠቃላይ የሀብት መጠኑ 6 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር መድረሱንና የተቀማጭ ገንዘብ መጠኑም 4 ነጥብ 5 ቢሊዮን መድረሱን አስታወቀ፡፡ ባንኩ የቅርንጫፎቹን ቁጥርም 75 ማድረሱን አስታውቋል፡፡

ዘምዘም ባንክ በትናትናው ዕለት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያከናወናቸውን ተግባራት እና ሊሰራቸው ያቀዳቸውን ሥራዎች አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል፡፡

በፕሮግራሙ ንግግር ያደረጉት የባንኩ ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሊካ በድሪ እንደገለጹት፤ ባንኩ የተቀማጭ ገንዘብ መጠኑን አራት ነጥብ አምሥት ቢሊዮን ብር አድርሷል፡፡ አጠቃላይ የሀብት መጠኑንም ስድስት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ማድረስ ችሏል፡፡

ዘምዘም ባንክ የማኅበረሰብ ተጠቃሚነት ላይ እየሠራ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ባንኩ የፋይናንስ አቅርቦትን ያለማስያዣ በማቅረብ የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየሰራ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ዘምዘም ባንክ የዋና መስሪያ ቤት ህንፃ መገንቢያ የሚውል መሬት የፋይናንስ ማዕከላት በተሰባሰቡበት በልደታ ክፍለ ከተማ አራት ሺህ ካሬ ሜትር በላይ ስፋት ያለው ቦታ ከአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ እንደተፈቀደለት ወይዘሮ መሊካ ገልጸዋል፡፡

ለባንኩ የተፈቀደው የህንጻ መስሪያ ቦታ የፋይናንስ ተቋማት ተሰባስበው በሚገኙበት ዕምብርት ቦታ ላይ መሆኑ የአገራችንን የፋይናንስ ሥርዓት አካታችነት መሠረት መጣሉን በጉልህ ማሳያ መሆኑን ወይዘሮ መሊካ ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም ዘምዘም ባንክ በአዲስ አበባ 38 ቅርንጫፎችን እንዲሁም በክልል 37 ቅርንጫፎችን በአጠቃላይ ከ75 በላይ ቅርንጫፎች መክፈት መቻሉን አስረድተው፤ የደንበኞቹን ቁጥር በማሳደግ ላይ እንደሚገኝ እና ከ12 ሺህ 700 በላይ ባለአክሲዮኖችም እንዳሉት አብራርተዋል፡፡

ዘምዘም ባንክ የሸሪዓ ሕግን ተከትሎ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በመላ አገሪቷ አገልግሎት ለመስጠት እየሰራ መሆኑን ወይዘሮ መሊካ አስረድተው፤ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች በቅርበት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን አሰራር ዘርግቶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑንም አብራርተዋል።

ዘምዘም ባንክ ሙሉ ለሙሉ ከወለድ ነጻ አገልግሎት በመስጠት አገልግሎቱንና ተደራሽነቱን ለማስፋት ይሰራል ያሉት ወይዘሮ መሊካ፤ ህብረተሰቡ የቁጠባ ባህሉን በማሳደግና የተለያዩ የባንክ አገልግሎቶችን በመጠቀም ለባንኩ እድገት የበኩሉን እንዲወጣ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

ዘምዘም ባንክ የመጀመሪያው ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነፃ ባንክ በመሆን ግንቦት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ሥራ መጀመሩ የሚታወስ ነው።

# በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት አካባቢን መለወጥና ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል

## . ዘንድሮ ከ20 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች ይሳተፋሉ

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት አካባቢን መለወጥና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ እንደተቻለ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በዘንድሮው የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ከ20 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች ይሳተፋሉ ተብሏል፡፡

የዘንድሮው የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ማስጀመሪያ መርሐግብር "በጎነት ለኢትዮጵያ ከፍታ" በሚል መሪ ቃል በትናንትናው ዕለት ተከናውኗል፡፡

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በማስጀመሪያ መርሐግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ አገልግሎቱን ተግባራዊ ማድረግ ከተጀመረ ጀምሮ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወጣቶች በበርካታ የልማት ሥራዎች እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡

ወጣቶች በተግባር በተሰማሩባቸው የልማት እንቅስቃሴዎች አካባቢን የለወጡ እና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ያደረጉ በርካታ ውጤቶችን ማግኘት ተችሏል ብለዋል፡፡

የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደኢትዮጵያ በማደግ ላይ ላሉ አገራት ከፍሀነት ለመላቀቅ፣ ፈጣን፣ ዘላቂ፣ ቀጣይነትና አስተማማኝነት ያለው ልማትና ዕድገት ለማስመዝገብ በሚደረገው ሁለንተናዊ ጥረትና ርብርብ ውስጥ ድርሻው የጎላ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ወጣትነት ብዙ ፍላጎት የሚንጸባረቅበት፣ እምቅ እውቀትና ጉልበት የተከማቸበት፣ እውቀትና ጉልበትን አስተባብሮ ፍላጎትን ማሟላትና ካሰቡት ደረጃ ላይ ለመድረስ ብርቱ ትግል የሚደረግበት የዕድሜ ክልል ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ወጣቶች ከአልባሌ ድርጊቶችና ሱሶች በመራቅ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና እውቀታቸውን ከራሳቸው አልፎ ለአገርና ለወገን ጠቃሚ በሆኑ የሥራ መስኮች ላይ ማዋል እንዳለባቸው አስገንዝበዋል፡፡


ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ

በአገሪቱ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ የመጣውን የልማት ፍላጎት በሚፈለገው ደረጃ ለማሟላትና የተጀመረውንም ሁለንተናዊ ዕድገት አጠናክሮ ለማስቀጠል በሚያስችል አግባብ ወጣቱ ሊሳተፍ ይገባል ብለዋል፡፡

ወጣቶች በሁሉም የልማት ሥራዎች ውጤት እንዲያስመዘግቡ ባለድርሻ አካላት ተገቢውን ትኩረት መስጠትና ትክክለኛውን አቅጣጫ ማሳየት እንደሚገባቸውም አሳስበዋል፡፡

በዘንድሮው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ከ20 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር፣ በትምህርትና ጤና አገልግሎት፣ በአካባቢ ውበትና ጽዳት፣ በማህበረሰብ አቀፍ ልማት፣ በሰላምና ደህንነት፣ በትራፊክ መንገድ ደህንነት አገልግሎት፣ በግብርና ልማት ሥራዎች እና መሰል ተግባራት እንደሚሳተፉ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፣ ወጣቶች በክረምቱ ወራት በሚያከናውኗቸው የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ከ51 ሚሊዮን በላይ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ በዚህም ከ15 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንደሚሰጥ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

አገልግሎቶቹ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን በመቅረፍ የህብረተሰቡን የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና መንግሥት ለዘርፉ የሚያወጣውን ገንዘብ ለማስቀረት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ጉልህ ነው ያሉት ዶክተር ኤርጎጌ፤ የአገሪቱን ሁለንተናዊ ዕድገት ለማስቀጠል ወጣቶች የማይተካ ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

ወጣቶች በራሳቸው ተነሳሽነት፣ መልካም ፈቃድና ፍላጎት ተንቀሳቅሰው ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ባሻገር በምላሹ ከህብረተሰቡም ጠቃሚ የሆኑ የሕይወት ልምዶችንና ክህሎቶችን፣ ጠቃሚና በጎ ባህላዊ እሴቶችን የሚቀስሙበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እና የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ወጣቶች የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡



# በከተማዋ የሚገኙ አብያተ መጻሕፍትን ምቹና ተመራጭ ለማድረግ እየተሠራ ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በከተማዋ የሚገኙ አብያተ መጻሕፍትን ምቹና ተመራጭ ለማድረግ የከተማ አስተዳደሩ በጀት መድቦ እየሰራ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ አዘጋጅነት 7ኛው ዙር የንባብ ባህል ሳምንት "ንባብ ለዘላቂታዊ ልማት" በሚል መሪ ቃል ከትናንት በስቲያ በኢትዮ ኩባ ወዳጅነት ፓርክ ተጀምሯል፡፡

የንባብ ባህል ሳምንት መርሐ ግብሩን ያስጀመሩት የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው፤ የአገርን ዘላቂ ዕድገትና ልማት ለማረጋገጥ አንባቢ ትውልድ መፍጠር እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

አንባቢ ትውልድ አገርን መገንባት የሚችል በመሆኑ ንባብ ባህል ሊያድግ ይገባል ያሉት ኃላፊዋ፤ የአገሪቱን ልማት ለማፋጠን፣ የከተማውን ሕዝብ የንባብ ፍላጎት ለማሳደግ፣ መጻሕፍትን ለማስተዋወቅ፣ መጻሕፍት ሻጮችን ለማበረታታት፣ በዕውቀት የዳበረ አንባቢ ትውልድ ለመፍጠር እና የንባብ ባህልን ለማሳደግ ለሰባት ተከታታይ ዓመታት በየሩብ ዓመቱ የንባብ ባህል ሳምንት እየተከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

አንድ ሰው የንባብ ባህልን በቀን አምስት ገጽ በማንበብና አንድ ገጽ በመጻፍ መጀመር አለበት ያሉት ዶክተር ሂሩት፤ ትውልዱን ጥልቅ አንባቢ ለማድረግ ምቹ የንባብ ቦታዎችን ማመቻቸት እና የተመረጡ የንባብ መጻሕፍትን ማዘጋጀት እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

በከተማዋ የሚገኙ ቤተ መጻሕፍትን ምቹና ተመራጭ ለማድረግ ከተማ አስተዳደሩ በጀት መድቦ እየሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህ ስራ ላይ ማህበረሰቡና ባለድርሻ አካላት እገዛ ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ወርቅነሽ ብሩ በበኩላቸው፤ በአገሪቱ ዘላቂ ልማትን ለማምጣት አንባቢ ትውልድን መፍጠር ተገቢ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ ቤተ መጻሕፍትና ቤተ መዛግብት ኤጀንሲ አንባቢያን በማንኛውም ቦታ ሆነው መጻሕፍትን በጽሁፍ፣ በድምጽና በምስል ማግኘት የሚችሉበትን የ"ኢ-ለርኒግ" መተግበሪያ ከ30 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ አበልጽጎ በሥራ ላይ እንደሚገኝ የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ሁሉም ማህበረሰብ ሊጠቀምበት እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ለሰባት ዓመታት በዓመት አራት ጊዜ እየተካሄደ ያለው ከተማ አቀፍ የንባብ ሳምንት በአገሪቱ ሁሉም አካባቢዎች ተጠናክሮ እንዲቀጥል አሳስበዋል።

# ስምምነቱ በአገሪቱ ያለውን የዲጂታል አጠቃቀም ክፍተት ለማጥበብ ትልቅ ሚና አለው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የትብብር ስምምነቱ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የስማርት ሞባይል ስልኮችን ተደራሽነት በመጨመር በአገሪቱ ያለውን ከፍተኛ የዲጂታል አጠቃቀም ክፍተት ለማጥበብ ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው ተገለጸ፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም፣ ቴክኖ ሞባይል ኩባንያ እና ትራንሲዮን ማኑፋክቸሪንግ ስማርት የሞባይል ስልኮችን በአጋርነት ለማቅረብ እና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የሦስትዮሽ የመግባቢያ ስምምነት በትናንትናው እለት ተፈራርመዋል፡፡

የኢትዮ ቴሌኮም ሽያጭ ዳይሬክተር አቶ ታምራት ተስፋዬ በስምምነት ሥነሥርዓቱ ላይ እንደገለጹት፤ የተደረገው ስምምነት ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የስማርት ሞባይል ስልኮችን ተደራሽነት በመጨመር፣ ደንበኞች የ4ጂ እና 5ጂ ኔትዎርክ እንዲሁም የዲጂታል አገልግሎቶችን በስፋት እንዲጠቀሙ ለማስቻል በአገሪቱ ያለውን የዲጂታል አጠቃቀም ክፍተት ለማጥበብ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡




አቶ ታምራት እንዳስታወቁት ኢትዮ ቴሌኮም ከኮኔክቲቪቲ አገልግሎት ባሻገር የተቋማትን የዕለት ተዕለት የቢዝነስ እንቅስቃሴን ለማዘመን እና ለማሳለጥ እንዲሁም መሪ የዲጂታል አገልግሎት አቅራቢ በመሆን ዘመኑን የዋጀ የዲጂታል አገልግሎት ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ በርካታ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ነው፡፡

ለዚህም ጠንካራ ተነሳሽነት እና ራዕይ አካል የሆነ እና ስማርት የሞባይል ስልኮችን በአጋርነት ለማቅረብ እና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የሦስትዮሽ የመግባቢያ ስምምነት ለማድረግ ተችሏል ብለዋል፡፡

የስትራቴጂያዊ አጋርነት ስምምነቱ በዋናነት የደንበኞችን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ ጥራት ያላቸው የቴክኖ ሞባይል ስልኮችን ለመገጣጠምና ለማቅረብ፣ በቂ የሞባይል ስልኮችን እና መለዋወጫዎችን ለማቅረብ፣ ደንበኞች የላቀ የዲጂታል ዕውቀት እና ተሞክሮ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ የሞባይል ስልኮችን ለማቅረብ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም የአገር ውስጥ ቋንቋዎችን እና ይዘቶችን የሚደግፉ ሞባይሎችን ተደራሽ ለማድረግ፣ የሞባይል ሽያጭን በትብብር ለማካሄድ፣ የድህረ ሽያጭ አገልግሎትን ለማሻሻል እንዲሁም ሥልጠናዎችን እና የቴክኒክ ድጋፎችን በጋራ ለማከናወን የሚያስችሉ ማዕቀፎችን የሚያካትት ነው ሲሉ አቶ ታምራት ተናግረዋል፡፡

በስምምነቱ ሦስቱ ኩባንያዎች የቴክኖ ሞባይል ኩባንያ የመጨረሻው የቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑትን ካሞን 20 ፕሮ 5ጂ እና ካሞን 20 ፕሪምየም 5ጂ የተሰኙ እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተራቀቁ እንዲሁም ደንበኞች የላቀ የአገልግሎት ተሞክሮ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ የስማርት ሞባይል ስልኮችን ለግብይት ማቅረባቸውን በጋራ አብስረዋል፡፡

በቀጣይም እነዚህን እና መሰል የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ፋይዳ ያላቸውን ምርት እና አገልግሎቶችን ለማህበረሰቡ በሰፊው በማቅረብ የቴክኖሎጂ ተደራሽነትን እና አካታችነትን ለማረጋገጥ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል ሲሉ አስታውቀዋል፡፡

# በኦሮሚያ ክልል ሁለተኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር ነገ ይጀመራል

## - 4 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ሁለተኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር ነገ እንደሚጀምር የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በመርሃግብሩ አራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል፡፡

በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የኦሮሚያ የገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪ አቶ አብዱራህማን አብደላ የሁለተኛውን አረንጓዴ አራሻ መርሃግብርን አስመልክተው ትናንት በሰጡት መግለጫ፤ ሁለተኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር "ነገን ዛሬ እንትከል" በሚል መሪ ሃሳብ እሁድ ይጀምራል። በመርሃ ግብሩም አራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል፡፡

እንደ አቶ አብዱራህማን ገለጻ፤ የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚያስችል የአረንጓዴ ኢኮኖሚን መገንባት ወሳኝ ነው። ይህም እንደ ኢትዮጵያ ባሉት ታዳጊ አገራት ላይ የሚፈጥረውን ጫና በማስቀረት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ይረዳል፡፡

በሁለተኛው ዙር አራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን የተለያዩ ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል ያሉት አስተባባሪው የሚተከሉት ችግኞችም 40 በመቶ ለደን ሽፋን ፣ 35 በመቶ ለብዝኃ ሕይወት፣15 በመቶ ለእንስሳት መኖነትና አንድ በመቶ ቀርከሀ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

እንደ አገር የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ሲተገበር መቆየቱን ጠቅሰው በመጀመሪያው የአረንጓዴ መርሃግብር 25 ቢሊዮን ችግኝ መትከል ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ የክልሉ ድርሻ 55 ነጥብ 4 በመቶ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በመጀመሪያው የ2011 ዓ.ም መርሃግብር አንድ ነጥብ 91 ቢሊዮን ችግኞች መተከላቸውን ጠቅሰው፤ በ2012 ዓ.ም ሦስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ችግኝ ተተክሏል። በ2013 ዓ.ም አራት ነጥብ 26 ቢሊዮን እንዲሁም በ2014 ዓ.ም አራት ነጥብ 49 ቢሊዮን ችግኞች መትከል ተችሏል ብለዋል።

በመጀመሪያው ምዕራፍ አራት ዓመታት ውስጥ 13 ነጥብ 86 ቢሊዮን ችግኞች መተከላቸውን ገልጸው የተተከሉት ችግኞች የጽድቀት መጠን 84 ነጥብ 95 በመቶ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡ በዚህም በተከላውና በእንክብካቤው ላይ አስራ ሁለት ሚሊዮን የህብረተሰብ ክፍሎች መሳተፋቸውን ገልጸዋል።

በመርሃግብሩም 15 በመቶ የነበረውን የክልሉን የደን ሽፋን ወደ 26 ነጥብ 6 በመቶ ማሳደግ የተቻለ መሆኑን ጠቅሰው የውሃ ሀብትን በማሳደግ ምርትና ምርታማነትን እንዲጨምር ማስቻሉንም ተናግረዋል፡፡

በክልሉ የሁለተኛው ዙር መርሃግብር እሁድ ሰኔ 18 ቀን 2015 ዓ.ም የሚጀምር ሲሆን እስከ መስከረም ድረስ እንደሚቆይም ተገልጿል፡፡

ዜና

# “የመሠረተ ልማት ተቋማት ተቀናጅተው ባለመሥራታቸው የአገር ሀብት ለብክነት እየተዳረገ ነው”

## . የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች

# “የቅንጅት ችግሩን ለመፍታት ተቋማቱ የጋራ ስምምነት አድርገዋል፤ ማስተር ፕላንም እየተዘጋጀ ነው”

## . የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የመሠረተ ልማት ተቋማት ተቀናጅተው ባለመሥራታቸው ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ሊሆኑ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ። የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር በበኩሉ፤ በተቋማቱ መካከል የጋራ ስምምነት የተደረገ መሆኑን ገልጾ፤ ችግሩን በይበልጥ ለመፍታት የመሠረተ ልማት ማስተር ፕላን እየተዘጋጀ ነው ብሏል።

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ አቶ ተሾመ ነጋሽ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የመሠረተ ልማት ግንባታቸው ከተጠናቀቀ ዓመት ያልሞላቸውና ከፍተኛ መዋለ-ንዋይ የፈሰሰባቸው መንገዶችን በመቆፈር የውሃ፣ የቴሌ - ኮም እንዲሁም የመብራት ተቋማት መሠረተ ልማት ለመዘርጋት በሚደረግ ጥረት በርካታ የአገር ሀብት እየወደመ ነው።

ይህ ሥር የሰደደ ችግር የሀገሪቱ እቅዶች በተያዘላቸው ጊዜ እንዳይጠናቀቁ፣ የተጠናቀቁትም ጉዳት እንዲደርስባቸው እያደረገ ነው ያሉት አቶ ተሾመ፤ የመሠረተ ልማት ተቋማት ተቀናጅተው ባለመሥራታቸው የእግረኛ መንገዶች ውበት ከመበላሸታቸው ባለፈ ደረጃቸውን ጠብቀው የተሰሩት ዳግም እንዲበላሹ እያደረገ ነው፤ በተጨማሪም አቅመ ደካሞች እና አካል ጉዳተኞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ ነው ብለዋል፡፡

ሰዎችም የእግረኛ መንገዱ በተለያዩ ምክንያቶች የጠቆፋፈረ፣ ውሃ ያዘለ እና ጭቃ ያለበት በመሆኑ በአስፋልት መንገድ ይጓጓዛሉ ያሉት አቶ ተሾመ፤ ይህም ሰዎችን ለመኪና አደጋ እያጋለጠ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ስለዚህ ይህን ችግር የሚመለከተው አካል በትኩረት ሊመለከተው ይገባል ብለዋል።

አቶ አድማሱ መንግሥቴ በበኩላቸው፤ አንዱ የመሠረተ ልማት ተቋም የገነባውን ሌላው የማፍረስ ችግር ይታያል። የተቋማት ተቀናጅቶ የመስራት ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተፈታ ቢመጣም በሚፈለገው መልኩ ተናቦ የመሥራት ባህል አሁንም አልዳበረም ሲሉ አስረድተዋል።

በዚህ የተነሳም ህብረተሰቡ ለምሬት እየተዳረገ ይገኛል ያሉት አቶ አድማሱ፤ ይህ ችግር በመሠረተ ልማት ተቋማት የቅንጅት ክፍተት የሚደርስ በመሆኑ ሊጠየቁ ይገባል ብለዋል።

እንደ አቶ አድማሱ ገለፃ፤ ተቋማቱ ተቀናጅተው እንዲሰሩ የሚመለከተው አካል ክትትል ማድረግ አለበት። ይህም ተደጋጋሚ የመሠረተ ልማት ወጪን የሚታደግ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንዳይስተጓጎል የሚያግዝ ነው።

የመንገድ መሠረተ ልማት በሚከናወንበት ወቅት ፕሮጀክቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ፋይዳው ላቅ ያለ ቢሆንም የፈረሰውን አሻሽሎ መገንባት ደግሞ አገራዊ ግዴታ ነው ያሉት ደግሞ ወይዘሮ አዲስዓለም ታደሰ ናቸው።

እንደ ወይዘሮ አዲስዓለም ገለፃ፤ መሠረተ ልማት የአንድ አገር ዕድገት ወሳኝ ግብዓትና ውጤት ነው። ለዚህም ነው አገሪቱ ከፍተኛ በጀት በመመደብ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን እና የጥገና ሥራዎችን እያካሄደች የምትገኘው። ይሁንና በግንባታና ጥገና ወቅት እየታየ ባለው የቅንጅትና መናበብ ጉድለት ምክንያት ከፍተኛ መጠን ያለው የአገር ሀብት ብክነት ይታያል።

የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት የመሠረተ ልማት ገንቢ ተቋማት የሚታየውን የቅንጅት ክፍተት ማረም ይገባቸዋል ያሉት ወይዘሮ አዲስዓለም፤ ተቋማቱ በተናበበ መልኩ ወደ ተሻለ አሠራር በመግባት የአገርን ሀብት ከብክነት መታደግ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ኢትዮጵያ በደቻ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በአገር ደረጃ ለመሠረተ ልማት ዝርጋታ ትልቅ ትኩረት በመሰጠቱ አገሪቱ አመርቂ እድገት እያስመዘገበች ነው። ይሁንና ተቋማት ተቀናጅተውና ተናበው የመሥራት ባህላቸውን አሁንም በሚገባው ልክ ማሳደግ አለመቻላቸው አገሪቱን ዋጋ እያስከፈለ ነው።

የዚህን ችግር ለመፍታት ከዚህ በፊት የተቀናጀ የመሰረተ ልማት ድርጅት ተቋቁሞ የመሠረተ ልማት ተቋማት ተቀናጅተው እንዲሰሩ ጥረት ሲያደርግ ነበር። ነገር ግን ችግሩን ሊፈታ አልቻለም፡፡ በዚህ የተነሳ ችግሩ አሁንም ድረስ እየታየ ነው። ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ካለፈው አንድ ዓመት ጀምሮ የድርጅቱን ተግባር እና ሌሎች ጉዳዮችን አብሮ የሚይዝ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ተቋቁሟል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በ2015 ዓመተ ምህረት በመሠረተ ልማት ተቋማት መካከል የጋራ ስምምነት እንዲኖር ያደረገ ሲሆን ለችግሩም ዘለቄታዊ መፍትሄ ለመስጠት የመሠረተ ልማት ማስተር ፕላን እያዘጋጀ እንደሆነ ገልጸዋል።

# በሲዳማ ክልል ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን የጸጥታው ዘርፍ መዋቅራዊ ሪፎርም እየተካሄደ ነው

## . 157 የፖሊስ አመራርና አባላት ከሥራ ተሰናብተዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል ሰላምን ለማጽናት በጸጥታው ዘርፍ መዋቅራዊ ሪፎርም እየተካሄደ መሆኑን የክልሉ ሰላምና ጸጥታ ቢሮ አስታወቀ፡፡ 157 የፖሊስ አመራርና አባላትን ከሥራ የማሰናበት እርምጃ መወሰዱም ተገልጿል፡፡

የክልሉ ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ሃላፊ አቶ አለማየሁ ጢሞቲዎስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት የክልሉን ሰላም ለማጽናት መዋቅራዊ ሪፎርም እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በዚህም 157 የፖሊስ አመራርና አባላት ከሥራ የማሰናበት እርምጃ ተወስዷል፡፡

እንደ አቶ አለማየሁ ገለጻ ክልላዊ የጸጥታው ዘርፍ ሪፎርም ከተጀመረ አንድ ወር አስቆጥሯል። በዚህም ክልሉ ከተደራጀ ወዲህ በጸጥታው አካል የተሰሩ ጠንካራና ደካማ ተግባራት ተገምግመዋል፡፡

በክልሉ የሥነ ምግባር ጉድለትና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ያለባቸው የፖሊስ አመራሮችና አባላት ተለይተዋል ያሉት ኃላፊው 157 የፖሊስ አመራርና አባላት ላይ ከሥራ የማሰናበት እርምጃ መወሰዱንና 305 ለሚሆኑት ማስጠንቀቂያ መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡

ክልላዊ የጸጥታ ችግሮችን በዘላቂነት ለመቅረፍ የጸጥታውን ዘርፍ ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው በተከናወኑ የደካማና ጠንካራ ተግባራት ግምገማ ላይ 15 ሺህ 300 የጸጥታ አካላት ተሳትፈዋል ብለዋል፡፡

በክልል በሚገኙ የሰሜን፣ ምሥራቃዊ ፣ በደቡብና በማዕከላዊ ዞኖች ላይ ግምገማዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተደርገዋል፡፡ ይህም በእያንዳንዱ ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች ላይ የነበሩ ብልሽቶችን ለመለየት የሚረዳ መሆኑን አስረድተዋል።

በጸጥታ መዋቅር ውስጥ ሆነው ከወንጀለኞች ጋር የሚያብሩ፣ በተመደቡበት ቦታ ላይ ሕዝብና መንግሥት የጣለባቸውን ሃላፊነት የማይወጡ የጸጥታ አካላት መኖራቸውን ገልጸው ተገቢውን ምርመራ በማድረግ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ገልጸዋል፡፡

አቶ አለማየሁ እንደገለጹት፤ ሪፎርሙ በክልሉ የሥርዓት አልበኝነትና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በዘላቂነት ለመቅረፍ የሚረዳ ነው። በተለይም የዘረፋና ጠለፋ ወንጀሎችን ለማቆም የሚያስችል የተደራጀ የጸጥታ መዋቅር ለመፍጠርም የሚያስችል ነው፡፡

በመካሄድ ላይ በሚገኘው ግምገማ ተግባራት ተስፋ ሰጪ ግብዓቶች መገኘታቸውን ጠቅሰው ለውጡን ስኬታማ ለማድረግ እና ዜጎች ያለ ሥጋት እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችል መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትን ጠብቀው ዜጎችን ከማንኛውን ችግር ለመታደግ ብቁ የሆኑ አመራሮችና አባላት መኖራቸውን ገልጸው ብቁና በሕዝቡ ተቀባይነት ያላቸውን አመራሮች ወደ ፊት የማምጣት ሥራዎች በመሰራት ላይ መሆናቸውንም ተናግረዋል።

በቀጣይ የክልሉን ሰላምና ጸጥታ በማረጋገጥ የኢንቨስትመንትና የቱሪዝም ሥራዎችን ለማስፋፋት እየተሰራ ነው፡፡ በመሆኑም የጸጥታ ሥርዓቱን በዲጂታል ካሜራ የተደገፈ ለማድረግ የሚያስችል ሥራዎች በመሰራት ላይ ናቸው ሲሉም አስረድተዋል።

በተጨማሪም በክልሉ የመረጃ አያያዝ ሥርዓቱን ለማጠናከር እየተሰራ ነው ያሉት ኃላፊው የመረጃ ሃይሎችን የማሠልጠን ተግባራት የሚከናወኑ መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

# “ወጣት ሴት ዲፕሎማቶችና...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

መሰረታዊ ርምጃ ነው ብለዋል፡፡

ሴቶች በዲፕሎማሲና በሌሎች ዘርፎች እኩል ተሳትፎ እንደሚኖራቸው የገለጹት ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ፤ ወጣት ሴት ዲፕሎማቶችና አምባሳደሮች በሥራቸው ፅናትን የተላበሱ እንዲሆኑና በሚገጥሟቸው ገፊ ምክንያቶች ተስፋ እንዳይቆርጡ አሳስበዋል፡፡

ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ እንዳሉት፤ ለረጅም ጊዜ ዲፕሎማሲው በወንዶች ቁጥጥር ስር የነበረ ቢሆንም ሴቶችም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ የሴቶች አስተዋፅኦ ትኩረት ተነፍጎት ቆይቷል፡፡ ባለፈው ዓመት የጸደቀው ታሪካዊ ውሳኔ ክፍተቱን ለመቅረፍ ያለመ ሲሆን፣ በሁሉም የዲፕሎማሲ መስክና በሁሉም የሥራ አይነት እኩል ተሳትፎ እስኪመጣ ድረስ በጋራ መስራት አስፈላጊ ነው፡፡

እንደ ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ገለጻ፤ በዲፕሎማሲ ዘርፍ የተወሰኑ ማሻሻሎች አሉ፤ በርካታ ሴቶች ወደ ሙያው እየተቀላቀሉ ነው፤ ይሁን እንጂ አሁንም በርካታ ገፊ ምክንያቶች እንዳሉ መዘንጋ የለበትም፡፡ ብዙዎቻችን ብዙ ጉዞ ብናደርግም አሁንም ሴቶች በዲፕሎማሲው ዘርፍ ሊያደርጉት ስለሚገባ ጉዞ ማሰብ አስፈላጊ ነው፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ ተሞክሯቸውን ባጋሩበት ወቅት እንደገለጹት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሴቶችን የዲፕሎማሲ ቀን ማክበር ለሴቶች የተሰጠውን ትኩረት የሚያሳይ ሲሆን፣ ወጣት ሴት ዲፕሎማቶችን ለማፍራትም ትልቅ እገዛ ያደርጋል።

አዲስ አበባ ሦስተኛ የዲፕሎማሲ ማዕከል በመሆኗ ሴት ዲፕሎማቶች ተገናኝተው የሚመክሩበት፣ የሚወያዩበትና ግንኙነታቸውን እንዲያጠናክሩ የሚያስችል የሴት ዲፕሎማቶች ማህበር መቋቋም አለበት ብለዋል፡፡ ማህበሩን ለማቋቋም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፈቃደኛ ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በበኩላቸው፣ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ያሉ ችግሮችን በመቋቋም በርካታ ሴቶች አምባሳደርና ዲፕሎማት በመሆን ኢትዮጵያን አገልግለዋል ብለዋል። በየዘመኑ ለችግሮች እጅ ባለመስጠት ለአገራቸው በዲፕሎማሲው ዘርፍ ጠንካራ ሥራ የሰሩ ሴት ዲፕሎማቶች መኖራቸውን በመግለጽም ወጣት ዲፕሎማቶችም ልምድ ካላቸው ዲፕሎማቶች በመማር ጠንካራ መሆን እንደሚገባቸው ገልጸዋል፡፡

ከጥንት ጀምሮ በርካታና ሴት ዲፕሎማቶች ለአገራቸው አስተዋጽኦ ነበራቸው ያሉት ሚኒስትሯ፤ በ15 ኛው ክፍለ ዘመን ንግሥት እሌኒ ኢትዮጵያ ከአውሮፓና ከሌሎች አገራት ጋር በማገናኘት ትልቅ ሚና እንደነበራት ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜም በርካታ ወጣት ሴት ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቶች መኖራቸውን አንስተው፣ ወደፊት ሴቶች እንዲበዙ እየተሰራ ነው፤ የሴቶች እኩልነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የፖሊሲና የሕግ ማእቀፎች ላይ ማሻሻያ እየተደረገ ነው ብለዋል። በኢትዮጵያ ከ22 ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ውስጥ 9ኙ በሴት ሚኒስትሮች እንደሚመሩም ዶክተር ኤርጎጌ ተናግረዋል።

# በዓመት ከ10 ሺህ በላይ...



ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ላይ እንደተናገሩት፤ በሞጆ ከተማ የሚገነባው ፋብሪካ ግንባታው በ 11 ወር ይጠናቀቃል። ፋብሪካው በቀን እስከ 50 ትራክተሮችንና በዓመት ከ10 ሺህ በላይ ትራክተሮችን የማምረት አቅም ያለው ነው።

የትራክተር ፋብሪካው የአገራችንን ግብርና ለማዘመን ከፍተኛ ፋይዳ አለው ያሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፤ ከትራክተሮች በተጨማሪ የግብርና ማሽነሪ የሆኑትን ኮምባይነር፣ ሃርቨስተርና ሌሎች ማሽኖችን ማምረትም በስምምነት ውስጥ የተካተተ እንደሆነ ገልጸዋል።

የኢትዮ ኢንጅነሪንግ ግሩፕ የቦርድ አባል ወይዘሪት ያስሚን ውሃብረቢ በበኩላቸው፤ ስምምነቱ ግሩፑን በኢትዮጵያና በምስራቅ አፍሪካ ውስጥ የብቸኛ ወኪል ባለቤትነትን የሚያረጋግጥለት ነው፤ ይህም አገሪቱ በዘርፉ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ በማስቀረትና የውጭ ምንዛሪን በማስገኘት ረገድ ከፍተኛ ፋይዳን ያበረክታል ብለዋል።

የኮንትራት ስምምነቱ ከፋብሪካ ግንባታ በተጨማሪ የድህረ ሽያጭ አገልግሎት ማዕከልንም ያካተተ በመሆኑ ዘላቂና አስተማማኝ አገልግሎት እንዲኖር የሚያስችል ነው ያሉት ወይዘሪት ያስሚን፤ የፋብሪካው መገንባት በተለይም በግሩፑ ስር የሚገኘውን የአዳማ ግብርና ማሽነሪን ትክክለኛ የአምራች ቁመና እንዲኖረው በማድረግ፣ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር በማምጣት ለብዙዎች የሥራ እድል በመፍጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ነው ብለዋል።

ስምምነቱ የግሩፑን ባለሙያዎች በተግባርና በንድፈ ሃሳብ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በማሠልጠን በሶስተኛ ወገን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ እንደሚያስችልም ገልጸዋል።

የ"ዋይ ቲ ኦ" ኩባንያ ፕሮጀክት ማናጀር ዋንግ ሰን በበኩላቸው፤ የዋይ ቲ ኦ ካማኮ ኩባንያ በቻይና ቁጥር አንድ የትራክተር አምራች መሆኑን ገልጸው፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ የፋብሪካውን ግንባታ ለማጠናቀቅ እና ሥራ እንዲጀምር ለማድረግ ኩባንያው ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል ብለዋል።

ፋብሪካውን ለመገንባት የሚያስችል የመሠረት ድንጋይ ነሃሴ 2014ዓ.ም መቀመጡም በስምምነቱ ተገልጿል።

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹በአግባቡ ራሱን እየተቆጣጠረ የሚሄድ የተፈጥሮ ሥርዓትን ማዛነፍ ዋጋ ያስከፍላል››

*-ዶክተር ጌቴ ዘለቀ*

*በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የውሃና መሬት ሀብት ማዕከል ዋና ዳይሬክተር*

አስቴር ኤልያስ



**የተወለዱት በቀድሞ አጠራሩ ጎጃም ክፍለ ሀገር አዲስ ቅዳም በምትባል ከተማ ሲሆን፣ ያደጉት ደግሞ የታላቁ አባይ ወንዝ መፍለቂያ በሆነችው ግሽ አባይ ሰከላ አያታቸው ዘንድ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን የተማሩት በዚያው በሰከላ በደጃዝማች ዘለቀ ደስታ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ የተማሩት በዳንግላ ሃይስኩል ነው፡፡**

**ከሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በኋላ ያመጡት ነጥብ ከፍተኛ በመሆኑ የአለማያ ዩኒቨርሲቲን ተቀላቅለው በእርሻ ምህንድስና (በአግሪካልቸራል ኢንጂነሪንግ) በመጀመሪያ ዲግሪ ተመረቁ፡፡ እንደተመረቁም ሥራ የጀመሩት የአፈርና ውሃ ጥበቃ ባለሙያ በመሆን በደብረማርቆስ አውራጃ ስናን በምትባል ደጋማ አካባቢ ነው፡፡ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በኔዘርላንድስ ዋግኒንገን ዩኒቨርሲቲ በአፈርና በውሃ ማኔጅመንት ሠሩ፡፡ እንዳጠናቀቁም ወደ አገራቸው ተመልሰው የተሰማሩት በተፋሰስ ልማት ላይ ነው፡፡ የሦስተኛ ዲግሪያቸውን የሰሩት ደግሞ በስዊዘርላንድ በርን ዩኒቨርሲቲ በሁለት ነጥቦች ላይ ነው፤ አንደኛው በኢትዮጵያ የመልክዓ ምድሩ ትራንስፎርሜሽን ከ1959 ዓ.ም ጀምሮ ምን ይመስላል? የሚለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የመሬት መራቆት መጠንን በተፋሰስ ደረጃ ማወቅና እንዴት መቀነስ ይቻላል? በሚል ነው፡፡**

**በእርግጥ አስቀድመው በሠሩት ሥራም ሆነ በተመረቁበት ዘርፍ ከአገር ውጪ መስራት የሚያስችላቸው እድል ቢኖርም እዛ መቅረትን አልወደዱም፡፡ መሬት መራቆት ላይ ሠርተውና ለውጡን አይተው ስለነበርም ያንን ትተው ምቾት ወደአሰው ስፍራ ለመሄድ ለሕሊናቸው ምቾት አልሰጣቸውም፤ በመሆኑም ተመልሰው የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራ ላይ ቀጠሉ፡፡ በሒደትም ፕሮጀክቱን መሰረቱ፡፡**

**አንድ ሰው ሆነው የጀመሩት ፕሮጀክት በአሁን ሰዓት ከ200 በላይ ባለሙያን ይዞ ወደ ማዕከልነት አድጓል፡፡ ይህ ተቋም ለአገር የሚጠቅም ትልቅ ሥራ እየሰራ ሲሆን፣ ወደ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ልማት መቀየር የሚችል ብዙ የምርምር ውጤቶች ያለው ነው፡፡ አዲስ ዘመንም የዛሬ እንግዳ ያደረገው ማዕከሉን በዋና ዳይሬክተርነት የሚመሩትን ዶክተር ጌቴ ዘለቀን ነው፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- አንድ ሰው አንድ ተቋም መሰረተ ሲባል ብዙ የተለመደ አይደለም፤ ተቋሙን ለመመስረት ያነሳሳዎ ምንድን ነው የሚለውን ጥያቄ አስቀድመን ውይይቱን እንጀምር?**

**ዶክተር ጌቴ፡-** የውሃና መሬት ሀብት ማዕከል ሥራ ከመጀመሬ በፊት የስዊዝ መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ሆኖ እኤአ በ1982 ላይ በአፈርና ውሃ ጥበቃ ፕሮጀክት ብዙ ሥራዎችን ሠርቷል። የዚህ ፕሮጀክት አመሰራረትም በወቅቱ በ1966 በተለይ የሰሜኑ፣ የምሥራቁና የደቡቡ አካባቢ የተከሰተው ድርቅ ያመጣው ከአካባቢ መራቆት ጋር ቁርኝት አለው የሚል እምነት በመያዙ (በተለይም በአፈር ብክለት) እና በተለይም በቀይ መስቀል የሚመራው ቡድን በቀድሞው ወሎ ክፍለ ሀገር በሲሪንቃ አካባቢ የአፈርና ውሃ ጥበቃ በመጀመሩ ለዚያ የሚሆን በሳይንስ የተደገፈ መልስ ለመስጠት ነበር።

ምክንያቱም በወቅቱ እኤአ በ1966 አካባቢ ዘመናዊ በሆነ መንገድ የአፍርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ስለማይታወቅ የተጀመረው በተለመደው የአፍርና ውሃ አጠባበቅ ሥራ ነው፤ የትኛው ለኢትዮጵያ የአየር ጸባይ እንዲሁም የአፈር አይነት ይሆናል በሚል አይደለም። ምክንያቱም የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ እንደየስነምህዳሩ አይነት የሚለያይ ነው። ለምሳሌ ዝናብ የሚበዛበት አካባቢና ዝናብ አጠር አካባቢ የሚያስፈልጋቸው የቴክኖሎጂ አይነት አንድ አይነት መሆን አይችልም። በትክክለኛው ቴክኖሎጂ ባለመሰራቱ ያንን የተመለከቱ የሲውዘርላንድ ባለሙያዎች በተለይ ፕሮፌሰር ሃንስ ሁርኒ በወቅቱ ከነበረው የግብርና ሚኒስቴር ጋር እና ሌሎችንም ይዘው የአፈር ጥበቃ ፕሮጀክት መሰረቱ።

የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማው የነበረው አንደኛው በኢትዮጵያ በተለያዩ አግሮ ኢኮሎጂዎች ምን አይነት የአፈርና ውሃ ጥበቃ ቴክኖሎጂ ነው የሚያስፈልገው? የሚለውን መለየት ነው። ሁለተኛው እንደ ተዳፋቱ አይነት እንዴት ይሰራል? የሚለውን መለየት ነው። ሦስተኛው ደግሞ በዓመት እየታጠበ የሚሄደው የአፈር መጠን በአንድ ተፋሰስ ወይም በሔክታር ምን ያህል ነው የሚለውን መለየት ነው። አራተኛው ደግሞ አቅም ማጎልበት ሲሆን፣ የግብርና ባለሙያውንም ሆነ አርሶ አደሩን ማሰልጠን ነው።

ሥራው የተጀመረው አካባቢው እኤአ በ1982 በደሴ ሃያ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ማይባር በምትባል ተፋሰስ ላይ ነው፤ ሁለተኛው ተፋሰስ ደግሞ የማዕከላዊ ጎጃምን ይወክላል የተባለ አንጄኒ በምትባልባት እኤአ በ1984 ላይ ደምበጫ አካባቢ ተጀመረ። በወቅቱ አካባቢው የተመረጠው እንደሚታወቀው ጎጃም ትርፍ አምራች ነው፤ ግን አካባቢው ከፍተኛ ዝናብ ያለበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በቦረቦር የተጠቃ አካባቢ ስለነበር ያንን ለማስተካከል ታስቦ ነው። ቀጥሎም ወደሰሜን ሸዋ አካባቢ በልግ አምራች በሆነው ቦታ ጣርማ በር አንዲት-ጥድ በምትባልበት ዳገታማው አካባቢ ተመሰረተ።

ከዚያ ቀጥሎ ጭሮ አካባቢ የጨርጨር ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ሐረር ሁንዴላፍቶ በሚባል አካባቢ፤ ከዚያም በደቡቡ አካባቢ የሚወክል ወላይታ ውስጥ ጉኑኖ ተፋሰስ በሚባልበት አካባቢ ተመሰረተ። ከዚያም የቀሩት ሁለት ተፋሰሶች የደቡብ ምእራብ አካባቢ ደንና ረግረጋማ አካባቢ ያለበትን ቦታ የሚወክል ኢሉአባቦር ውስጥ ዲዚ በሚባል ቦታ ላይ ሌላ ተመሰረተ። እነዚህ ዋና ዋና የሚባሉ ስነምህዳርን የሚወክሉ ናቸው። በወቅቱ ኤርትራም አንዷ የኢትዮጵያ ግዛት ነበረችና ኤርትራ፣ ትግራይንና ዋግኸምራን በተወሰነ ደረጃ ደግሞ በወሎና በአፋር መካከል ያለውን ደረቃማ ቦታ የሚወክል ኤርትራ ውስጥ አፈደዩ የምትባል ቦታ ሌላ ተመሰረተ።

አጠቃላይ ሰባት ዋና ዋና የሚባሉ የተለያዩ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ስነ ምህዳሮችን የሚወክሉ ተፋሰሶች ተመስርተው ሥራ ተጀመረ። ይህም አስቀድሜ እንደነገርኩሽ በስዊዘርላንድ መንግሥትና በግብርና ሚኒስቴር አስተባባሪነት ማለት ነው። በእነዚህ የተፋሰስ ጣቢያዎች ውስጥ ወዲያው በአጭር ጊዜ ውስጥ በዓላማቸው መሰረት የትኛው ቴክኖሎጂ ለየትኛው አካባቢ ይመጥናል የሚለውን መለየት ተቻለ።

በየአግሮኢኮሎጂው በሔክታር እየተጠረገ የሚሄደው የደለል መጠን ምን ያህል ነው? የሚለው መለየት ተቻለ። የወንዞቹን ፍሰትና የአየር ንብረቱን እንዲሁም የዝናብ መጠኑ ምን ያህል ነው? የሚለው ተለየ። እኤአ በ1982 ተጀምሮ 1987 አካባቢ የመጀመሪያው የልማት ጣቢያ ሠራተኞች የአፍርና የውሃ ጥበቃ መመሪያ ተጻፈ። ከዚያም የአፈርና ውሃ ጥበቃ በስፋት መሠራት ተጀመረ። የመጀመሪያው ተፋሰስ ከተመሰረተ በኋላ ሌሎችም ወዲያው ተከታትለው ተመሰረቱ። የማስተዋወቁ ሥራ በስፋት ቀጠለ። በእንዲህ አይነት ሁኔታ እስከ ደርግ መጨረሻ ጊዜ ድረስ ቀጠለ።

በኋላ ላይ የመንግሥት ለውጥ ሲመጣ ፕሮጀክቱ ወጣ። እኔ በወቅቱ ዶክትሬት ዲግሪዬን እየሰራሁ ነበርና ከፕሮፌሰር ሃንስ ጋር ተወያየን፤ እነዚህ ተፋሰሶች እንዲሁ ከምናስቀራቸው ከመንግሥት ተቋማት ጋር እናያይዛቸው ብለን ተማከርን። በመሆኑም እንደያሉበት ቦታ በክልል ደረጃ ካሉ የምርምር ማዕከላት ጋር አያያዝናቸው። በአማራ አካባቢ ያሉትን ከአማራ ክልል ውስጥ በሚገኙ ምርምር ማዕከላት ጋር ሌሎችን እንዲሁ ከየክልሎቹ ጋር አስተሳሰርናቸው። እኔ በወቅቱ የአማራ ክልል የግብርና ምርምር ተቋም ዳይሬክተር ጄነራል ነበርኩ። የቀረን አፈደዩ የተባለው በኤርትራ ውስጥ የሚገኘው ሲሆን፣ ኤርትራ እንደ አገር ራሷን ችላ በመውጣቷ እሱ ቀረ።

ካስተሳሰርናቸው በኋላ ተቋማዊ ሥርዓቱ የፖለቲካውን ስልት እየተከተለ ዥዋዥዌ ሲበዛበትና የሰው ኃይልም ሲቀያየር እንዲሁም ቀደም ሲል የነበረው የየሰው አስተሳሰብም ሲቀያር የነበረው ነገር እየቀነሰ መጣ። ማዕከላቱም የሚያመነጩት መረጃ ጥቅም ላይ መዋሉ ቀረ። በመሆኑም ከፕሮፌሰሩ ጋር ተነጋገርንና ለየት ያለ ተቋማዊ ሥርዓት እናብጅለት በሚል ወሰንን። ምክንያቱም በተፋሰስ ደረጃ ለረጅም ዓመታት በዚህ መልኩ መረጃ የሚሰጥ ተቋም በአፍሪካ ደረጃ የለም። ምክንያቱም በዚህ አሰራራችን የአየር ንብረት ለውጡን፣ የውሃ መጠኑንና የጎርፉን መጠንም ሆነ የአፈር ክለት መጠኑን እንከታተል ነበርና ነው። እንዲህ አይነት የረጅም ጊዜ ክትትል ምናልባት በትንሹ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ሊኖር ይችል ይሆናል፤ ስለዚህ ይህንን ሥራ ከፕሮጀክት ወደ ማዕከል እንቀይር በሚል ተነጋገርን። ተሟሙቆ የነበረው ተሳትፎአዊ የተፋሰስ ልማትም ወደ የዘመቻ ሥራ ስለተቀየረና ዘላቂነት ጥያቄ ውስጥ ስለገባ ምርምር ብቻ መስራቱ ብዙም አይደለም የሚል እምነት ነበረንና ከምርምሩ በተጨማሪ የተፋሰስ ልማት ሰርተን እናሳይ ወደሚለው መጣን። ለዚህም የሚሆን የሲውዘርላንድ መንግሥት እኤአ 2011 ላይ የተወሰነ ሪሶርስ መደበልን።

በወቅቱ ጀምረናቸው የነበሩትን ስድስቱን የምርምር ተፋሰሶች በማደራጀት ከየክልሉ የምርምር ተቋማት ጋር ሆነን ሥራቸው ተጠናክሮ እንዲሄድ ማድረግ አንዱ ነው። ሁለተኛ እስካሁን ድረስ ያለውን መረጃ በመተንተን እና ትርጉም በመስጠት ለሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤትና ለፖሊሲ አውጪ አካል ለግብዓትነት እንዲጠቀሙ ማድረግ ነው። ሦስተኛውና ዋናው ሠርቶ ማሳያዎችንና ሞዴል የመማሪያ ተፋሰስ መመስረትና ሠርተን ማሳየት የሚል ነው። ለዚህ ሥራችን ስድስት አነስተኛ ተፋሰሶችን በአባይ ተፋሰስ ውስጥ መረጥን። በወቅቱ የመረጥናቸው ተፋሰሶች የየራሳቸው መስፈርት ነበራቸው። አራተኛው ዓላማ አቅም ማጎልበት ነው። በዚሁ መሰረት እኤአ በ2011 በአጭር ጊዜ ውስጥ በእኔ አነሳሽነት በሁለቱ አገራት መካከል ስምምነቱ ተፈረመ። እኤአ በ2012 ጥር ወር ላይ ሥራ ተጀመረ። ሥራው መሰራት የተጀመረው ነባሮችን መልሶ ማቋቋምና አዲሶችንም በመስራት ነው።

እኔ እንደ ባለሙያ የሚቆረቁረኝ ይህ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራ የብዙ ባለሙያ ጉልበትን የሚጠይቅ ነው። ነገር ግን በዘመቻ የሚሰራው ዛሬ ተሰርቶ ነገ ይፈርሳል። ስለዚህ ያደረግነው ከሕዝቡና ከሚመለከታቸው የክልል፣ የዞንና የወረዳ አመራሮችና ባለሙያዎች ጋርም መመካከር ነበር። ስንጠቀም የነበረው በየዓመቱ ለአፈር ጥበቃ የሚወጣውን የሰው ጉልበት ነበር። በዛ ላይ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማስገባት ጀመርን። አካባቢያቸውን በደንብ ለጠበቁ ቴክኖሎጂውን በድጉማ እናቀርባለን። የከብቶች መዋያ የሚባለውን የተራቆተ ቦታዎችን ከተጠቃሚው ማህበረሰብ ጋር በመመካከር በመከለል አካባቢው እንዲያገግም በማድረጋችን ስራችንን በመስክ ጉብኚ ማሳየት ቻልን። በዚህ ብቻ ሳያበቃ በየአካባቢው ያሉ አርሶ አደሮች የጓሮ ልማቱን፣ ፍራፍሬውንና ለከብቱ መኖውን ማልማት ጀመሩ። በተለይም በጓሮ ልማት ዙሪያ ወደ 11 ፓኬጆችን በማዘጋጀት ማለትም፣ ፍራፍሬ መትከል፣ መኖ ማልማት፣ አትክልት ማምረት፣ ኮምፖስት ማዘጋጀት፣ ንብ ማነብ፣ ዶሮ ማርባት፣ ከብት ማደለብ፣ አነስተኛ የወተት ልማት፣ እንስሳትን አስሮ መቀለብ፣ ውሃ ማዘጋጀት፣ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ በማሰራት በጥቅሉ አካባቢያቸውን ወደጥምር ግብርና በመቀየር የአኗኗር ዘይቤያቸውን እንዲለወጡ አደረግን። በስድስቱ ተፋሰስ ሰፊ ለውጥ ማምጣት ቻልን።

እኤአ በ2016 ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማእቀፍ ስር በራሳችን የምንተዳደር ተቋም ሁነን፤ ስራችን ከፕሮጀክትነት ወደተቋምነት ተቀየረ። በዚህ ጊዜ ከሌሎችም ድጋፍ ማግኘት ቻልን። የሰው ኃይላችንም ቢሯችንም መለወጥ ጀመረ። በዘርፉ በጣም ሰፊ ሥራ እየሰራን ትኩረታችንን ደግሞ ውሃና መሬት ላይ አደረግን።

**አዲስ ዘመን፡- ውሃና መሬት ላይ በዋናነት ስትሰሩ የነበረው ምንድን ነው?**

**ዶክተር ጌቴ፡-** ውሃ ላይ የምንሰራው የውሃ አያያዝና የውሃ ብክለት ላይ ነው። ለምሳሌ የአዲስ አበባ ወንዞች ሲታዩ ይፈሳሉ እንጂ በውስጣቸው ሕይወት የለም።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ‹‹በአግባቡ ራሱን እየተቆጣጠረ...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ይፈሳሉ እንጂ በውስጣቸው ሕይወት የለም። ይህ በካይ ነገር የመጣው ከየት ነው በሚል ዝርዝር ሥራ እንሰራለን። በሰው ጤና እና በአካባቢ ላይ ያለውን ጉዳት እናጤናለን። በዚህ መልኩ በስፋት ለጊዜው እየሰራን ያለነው የአዋሽ ተፋሰስ ላይ ነው። ይህን ተፋሰስ የመረጥነው አንደኛ የአገሪቱ ዋና ከተማ ያለው አዋሽ ተፋሰስ ውስጥ ሲሆን፣ ብዙ ሚሊዮን ሕዝብንም የሚያካትት በመሆኑ ነው። ሌላው የአዋሽ ተፋሰስ ውስጥ ከ65 በመቶ በላይ ኢንዱስትሪዎችና ትልልቅ የንግድ እርሻዎችም ያሉ ስለሆነም ነው። ስለዚህ ይህን ታሳቢ አድርገን የአዋሽን የውሃ ብክለት ከላይ እስከ ታች መቃኘትና መንስዔውን ማወቁ ተገቢ ነው። ስለዚህ አዋሽ ላይ ትኩረት አድርገን መስራት የጀመርነው እኤአ ከ2015 ጀምሮ ነው።

ሥራውን የበለጠ ሊያጠናክርልን የሚችል እኤአ በ2015 ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን የእንግሊዝ መንግሥት የሚያግዘው አንድ ፕሮጀክት አገኘን። ፕሮጀክቱም ‹‹የውሃ ደህንነት ድህነት ለመቀነስ›› በሚል መሪ ሐሳብ የሚንቀሳቀስ ነው። ፕሮጀክቶቹ ኬንያ፣ ባንግላድሽና ኢትዮጵያ የሚተገበር ሲሆን፣ እኛ የኢትዮጵያ አስተባባሪ ሆንን። ዋና አጋራችን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና ዩኒሴፍ ናቸው።

ከውሃ ጋር ተያይዞ ሌላ ትልቅ ፕሮጀክት ከእንግሊዝ መንግሥት አገኘን። በአምስት አገሮች ይተገበራል፣ ኢትዮጵያ፣ ኮሎምቢያ፣ ህንድ፣ ማሌዥያና እንግሊዝ፤ የኢትዮጵያን ምርምር የምናስተባብረው እኛ ስንሆን የሁሉንም አገር የሚያስተባብረው ደግሞ ኒውካስትል ዩኒቨርስቲ ነው። በዚህ ፕሮጀክት በሦስት ተፋሰሶች ላይ ማለትም አባይ፣ አዋሽና ስምጥ ሸለቆ ላይ አተኩረን እንሰራለን። የምንሰራቸው ምርምሮችም የውሃ ብክለትና ጉዳት፣ የውሃ አጠቃቀምና ስርጭት፣ የዝናብ ውሃ አጠቃቀም፣ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ግንኙነት በዝርዝር ማጥናት ነው፤ እንዲሁም የውሃ ስርጭት ብዙ ጊዜ የውሃ ፍላጎትና አንድ ተፋሰስ ያለው የውሃ አቅርቦትን በዝርዝር ማጥናትም ሌላው ሥራ ነው። የከተሞች የውሃ አቅርቦት በምን አግባብ መያዝ አለበት የሚለው ሲሆን፣ ውሃ ኦዲት የማድረግ ሥራም ጭምር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ውሃ ኦዲት የሚደረገው እንዴት ነው?**

**ዶክተር ጌቴ፡-** አንደኛ በዛ ተፋሰስ ውስጥ ምን የውሃ መሰረተ ልማቶች አሉ? ግድብ፣ መስኖ. የከተማና የገጠር አቅርቦት፣ መሰረተ ልማቶች፣ ምን አይነት ደረጃ ላይ ናቸው? የሚይዙት የውሃ መጠን፣ የውሃ ዓመታዊ ፍሰታቸውና የሚሰጡት መጠን፣ ያለባቸው ችግር ቁጥጥር ይደረግባቸዋል ወይ? ባለቤቱ ማን ነው? የመስኖ መሰረተ ልማት ዲዛይን አላቸው ወይ? የሚለው ሁሉ ዝርዝር ጥናት ሲጠና ኦዲት ተደረገ እንደማለት ነው፤ እኛም ይህን ሁሉ አጠናን። ይህን የሠራነው አዋሽ ተፋሰስ፣ ስምጥ ሸለቆና ዓባይ ተፋሰስ ላይ ነው። ይህ በጣም ሰፊ ጥናት ነው።

እሱ ብቻ ሳይሆን ከስምምነታችን ወጣ ብለን የውሃ ኦዲት መረጃ ሥርዓት ሶፍትዌር አለማን። በሦስተኛ የምንሰራው የውሃ ኦዲት አትላስ ነው። በአትላስ የት ቦታ ምን አለ? አቅሙስ ምን ያህል ነው? የሚለውን እየሠራን ነው። ሥራውን በቅርቡ ይፋ እናደርገዋለን። ለምሳሌ በአንድ ‹‹ክሊክ›› በአቃቂ ተፋሰስ ውስጥ ስንት ጥልቅ ጉድጓድ አለ ተብሎ ቢጠየቅ ከነካርታው ይወጣልናል። እያንዳንዱን ጥልቅ ጉድጓድ ደግሞ ‹‹ክሊክ›› ስናደርግ የጉድጓዱ ጥልቀት፣ ባለቤቱ፣ የውሃ መጠኑ፣ መቼ እንደተቆፈረና አሁን ላይ ያለበት ደረጃ ምን እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

በአሁኑ ወቅት ውሃን በመቆጣጠር ደረጃ በጣም ብዙ ሥራ መሥራት አለበት። ለምሳሌ አቃቂ ተፋሰስ ውስጥ 913 ጥልቅ ጉድጓዶች አሉ። እነዚህ ጥልቅ ጉድጓዶች የተወሰኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚቆጣጠራቸው ውጪ ብዙዎቹን ሆቴሎች፣ ኢንዱስትሪዎች፤ የንግድ ማዕከላት በግል የቆፈሯቸው ናቸው።

የመቆፈር ፈቃድ ብቻ ነው ያላቸው እንጂ ምን ያህል ውሃ አላቸው? በከርሰ ምድር ላይ ምን ተጽዕኖ ያመጣል? የሚለው ነገር የላቸውም። እሱ ክፍተት ነው። አዲስ አበባ በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ያለች ከተማ ናት፤ የሕዝብ ብዛቱ እየጨመረ ነው። በገጸ ምድር ላይ ያሉ ግድቦቿ ለገዳዲ፣ ድሬና ገፈርሳ የቆዩ ግድቦች ናቸው። እኛም ከሕዝቡ መጠን ጋር የውሃ ሀብትን የአስተዳደሩ ሁኔታ በምን ያህል የሚጣጣም ነው የሚለውን እያጠናን ነው። የሚቆፈሩ ጥልቅ ጉድጓዶች በምን ያህል መጠን እየሄዱ ናቸው የሚለውንም እያጠናንና ከሚመለከታቸው ጋር እየተነጋገርን ነው። በአሁኑ ወቅት የውሃን ጉዳይ ስናይ ከብክለት አኳያ፣ ከሕዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ መጠኑ በጣም እየተመናመነ ነው፤ እኛም ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ ተቋማት ጋር በመሆን በእኛ ጥናት ላይ መሰረት ተደርጎ ዝርዝር የወደፊት የዘላቂ የውሃ አቅርቦትና የአያያዝ



ሥርዓት በአጭር ጊዜ ውስጥ መሥራት አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ከመመናመኑ የተነሳ አደጋ ውስጥ ያለውን ውሃ መታደግ የሚቻለው እንዴት ነው?**

**ዶክተር ጌቴ፡-** መታደግ ይቻላል፤ በጣም ቀላል ነው። በጣም ብዙ አማራጮችም አሉ። አንደኛው የለገዳዲና የገፈርሳ ውሃን ማጎልበት ሲሆን፣ ሁለተኛው እንደተፈለገ የሚቆፈረውን የጥልቅ ውሃ ጉድጓድን የቁጥጥር ሥርዓትን ማበጀት ነው። ሦስተኛው ደግሞ የላይኛውን የተፋሰስ አካል ማልማትና ውሃ ወደ ከርሰምድሩ እንዲሰርግ ማድረግ ነው፣ አራተኛው የውሃ ብክነት እንዳይኖር መቆጣጠር ነው። አምስተኛው የውሃ መበከልን መቀነስ ነው። ብዙዎች ጥናት ያካሄድንባቸው ኢንዱስትሪዎች ቆሻሻቸውን የሚለቁት በቀጥታ ወንዞች ላይ ነው። ከዚህ የተነሳ ወንዙ ሙት ውሃ ይሆናል። እሱ ደግሞ ለአትክልት ልማት ይውላል፤ ያ ደግሞ በጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል። ስለዚህ ውሃ ላይ ከተሰራ ማዳንና ዘላቂነት እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል። ቆሻሻ ነው የተባለ ውሃም አስፈላጊው እንክብካቤ ከተደረገለት ለአትክልትና ለመሰል አገልግሎት ማዋል ይቻላል። ከውሃ ጋር ተያይዞ በብዛት የሠራናቸው ሥራዎች እነዚህን ይመስላሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ከውሃ ጋር ተያይዞ የሰራችኋቸው ሥራዎች እሱ፤ በጥናታችሁ ያገኛችሁት ግኝት በዋናነት የሚደርሰው ለማን ነው? ምንስ እንዲደረግ ነው?**

**ዶክተር ጌቴ፡-** የጥናቱ ግኝት አንዱ ዋና ባለቤቱ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርና የተፋሰስ አስተዳደር ናቸው። ለጊዜው የሚያስተባብሩትም የዓባይ፣ የአዋሽና የስምጥ ሸለቆ አስተዳደር ጽህፈት ቤቶች ናቸው። ሁለተኛው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመስኖና ቆላማ አካባቢ እና የግብርና ሚኒስቴር ናቸው። ሌላው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው። ኢንዱስትሪዎች የሚያወጧቸውን ፍሳሾች አጣርተው መስራት እንዳለባቸው እንደግዴታ መቀመጥ አለበት። አራተኛው የከተማ ልማት ሚኒስቴር ነው። የከተሞች ማስተር ፕላን ሲሰራ ውሃን ታሳቢ ያደረገ ነው ወይ? የሚለው ሲታይ የአዲስ አበባ ከተማን ጨምሮ አይደለም። ስለዚህ ውሃን ማዕከል ያደረገ የከተሞች ፕላን በሚል አንድ ፕላን ጀምረናል። አዲስ አበባን እንደ ማሳያ ወስደን እየሰራንበት ነው።

ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ ማስተር ፕላኖች እንዴት አድርገን ውሃን በማእከልነት የሚያዩ ይሁኑ የሚለው ነው። የዚህንም ጥናት እየሰራን ሲሆን፣ እሱ በአጭር ጊዜ ይወጣል። ከዚያ በኋላ እኛ ያሰብነው የከተማ ልማት ፕላን ሚኒስቴር እንደ አንድ የቤት ሥራ ወስዶ ከተሞች ሲሰሩ ውሃን ማዕከል ያደረጉ መሆን እንዲገባቸው ነው። በጥቅሉ ከዚህ በኋላ ያሉት የከተሞች ማስተር ፕላኖች ውሃን ታሳቢ ያደረጉ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ነባር ከተሞችስ ምን መሆን አለባቸው?**

**ዶክተር ጌቴ፡-** እነሱ መከለስ መቻል አለባቸው። ለምሳሌ ጎንደር ከተማን ለአብነት ብንወስድ የውሃ አቅርቦቱ 25 በመቶ ብቻ ነው። አዲስ አበባም እንዲሁ አነስተኛ ነው። ባህርዳር ዙሪያው ውሃ ሆኖ ሳለ ተመሳሳይ ችግር ያለበት ነው። ስለዚህ የከተሞች ስፋት ውሃን ታሳቢ ባደረገ መንገድ ስለማይታቀድ ከተሞች መስፋታቸው አይቀርም፤ መጨረሻ ላይ ግን ውሃ የለም።

በሌላ በኩል የሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ነው። ባለስልጣኑ ለምሳሌ ወንዞችም ሆኑ የከርሰ ምድር ውሃ እንዳይበከል መቆጣጠር አለበት። ኢንዱስትሪዎችና የተለያዩ የንግድ ማዕከላት ቆሻሻቸውን ወደ ወንዝ እንዳይለቁ በጣም ሰፊ ሥራ መስራት አለበት። በዚህ ላይ ብዙ ሥራ እየተሰራ አይደለም። የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ይህን የመቆጣጠር ስልጣን አለው። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የሃይድሮ ፓወርና የመስኖ ትልልቅ ግድቦችን እየሰራች ነው። ወደዚያ የሚገባው ደለል (የዓባይን ግድብ ጨምሮ) ምን ያህል ነው? የሚለውን ለማየት ሞክረናል።

የዓባይ ግድብ ለሕዝቡ ኩራት የሆነ ነው። ነገር ግን ግድቡ ሲጀመር ስለታላቅነቱ እንጂ ወጣ ያለ ነገር እንዲወራበት አይፈለግም። ግድቡ ለትውልድም ለአገርም ትልቅ መልዕክት ያለው ነው። ነገር ግን ግድቡ ዘላቂ መሆን አለበት። ግድቡን ገድበን 75 እና 100 ዓመት ብቻ ብንጠቀምበት ዋጋ የለውም። ስለዚህ ግድቡ እየወጣበት ያለው ትልቅ ሀብት እንደመሆኑ አገልግሎቱም የዚያን ያህል ዘላቂ መሆን አለበት በሚል ዝርዝር ጥናት አጥንተን ለሚመለከተው መናገር ጀመርን።

አንዳንዶቹ በወቅቱ ቅር ቢላቸውም፤ በኋላ መረዳት ጀመሩ። እንደዋና አጀንዳም ሆኖ መሄድ ቀጠለ፤ ይሁንና ብዙ የሚቀረን ነገር አለ። እኛ በዓባይ ግድብ ላይ ተያይዞ ያጠናነው ዝርዝር ጥናት አለ። በዓመት የሚገባው ደለል ምን ያህል ነው? በዚህስ ከቀጠለ እድሜው ምን ያህል? ተፋሰሱን አልምተን ሃምሳ በመቶ ደለሉን ብንቀንሰው አሁን ከሚባለው ከዲዛይኑ እድሜው በተጨማሪ ምን ያህል ዓመት መቆየት ይችላል? የሚለውን አጠናን። 50 በመቶ ወደግድቡ የሚገባውን ደለል መቀነስ ብንችል 246 ዓመት፣ በ70 በመቶ ያህል ደግሞ ብንቀንሰው ኃይል እያመነጨ እስከ 375 ዓመት ድረስ መቆየት እንደሚችል በጥናታችን ማግኘታችንን አሳወቅን። ይህን ወደገንዘብ ቀይረን ለመንግስት አሳይተናል። ነገር ግን በመሃል ለውጡ መጥቶ ለተወሰነ ጊዜ ዝብርቅርቅ ሲል መንግሥትም ትኩረቱ አገር ማረጋጋት ላይ በመሆኑ ያሰብነውን ትልቁን ሥራ ለጊዜ ያዝ አደረግነው።

**አዲስ ዘመን፡- ጥናታችሁን ለመንግሥት ማሳወቅ ችላችኋልና የመንግሥት ምላሽ ምን ይመስል ነበር?**

**ዶክተር ጌቴ፡-** መንግሥት ገና ብዙ ይቀረዋል፤ እኛ ባሰብነው መንገድ እየሄደ አይደለም። በእርግጥ ተቋማትም ሆኑ በወቅቱ የነበሩ ግንዛቤውን ያስጨበጥናቸው ሰዎችም ሲቀያየሩ በታሰበው ልክ ማስኬድ አይቻልምና ሁኔታዎች እስኪረጋጉ እየጠበቅን ነው። በእኛ በኩል የት ቦታ ምን መሰራት እንዳለበት ጥናቱን አጥንተን ጨርሰናል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ዝርዝሩ በእጃችን አለ።

እኛ እያልን ያለነው ወደግድቡ የሚገባውን ደለል መቀነስ ከፈለጋችሁ ስራው መሰራት ያለበት የእኛ የመማሪያ ተፋሰሶችን በሚመስል መንገድ ነው። እሱ ሁለት ጥቅም አለው፤ አንዱ በተፋሰሱ ውስጥ ያለውን የአርሶ አደር ኑሮ ሙሉ በሙሉ ይቀይረዋል። ሁለተኛ ደግሞ ወደተፋሰሱ የሚገባውን ደለል እስከ 70 እና 80 በመቶ ድረስ ያስቀራል። ስለዚህ የግድቡን እድሜ ያራዝማል። ይህ ደግሞ ተጨማሪ የኃይል ምንጭ ወደ መቶ እና ከዛ በላይ እንዲያመነጭ ስለሚያደርግ በኢኮኖሚውም የሚገኘው ብዙ ትሪሊዮን ዶላር ነው። ከዚህ በተጨማሪ የኃይል መኖር ብዙ የኢኮኖሚ መንገዶች እንዲከፈቱ ያደርጋል። ለምሳሌ እኛ በምንሰራቸው በአነስተኛ ተፋሰሶች ላይ በ2 እና 3 ዓመት የአርሶ አደሩ ገቢ በዓመት ሦስት እጥፍ ድረስ ሲጨምር አስተውለናልና ስር ነቀል ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ማምጣት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- የዚህን ያህል ፋይዳ ያለው ጥናት እስከሆነ ድረስ መንግሥት ተቀብሎት ወደትግበራው የማይገባው ለምንድን ነው ይላሉ?**

**ዶክተር ጌቴ፡-** የሆነው ነገር እኛ ሙሉ ጥናቱን ጨርሰን ባለንበት ወቅት ለውጡ መምጣቱ ነው። ዲዛይን ያደረግነው ስትራቴጂ አለ፤ አንዳንዱን ወዲያው ብናቀርበው ነገሮች ባልተመቻቹበት ጊዜ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለጩሉሌዎች ሲሳይ እንደማድረግ ነው። ስጋታችን ጩልሌዎች ፍላጎታቸው ገንዘብ ብቻ ስለሚሆን ዘለው ገብተው እንዳያበላሹት ነው።

ሰላም ሆነ በሚል ልንጀምር ስንል ደግሞ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በተከሰተው የሕልውና ዘመቻ ለጊዜው ቆመ። እኛ አሁን ያደረግነው ነገር ተጨማሪ ጥናት እንቀጥላለን። የመማሪያ ተፋሰሶችን ደግሞ እያሰፋን ነው። ከነበሩት ስድስት ተፋሰሶች ላይ በኔዘርላንድ መንግሥት ድጋፍ በላቀ ደረጃ የሚተገበሩ 18 ተፋሰሶችን ጨምረናል። በየአካባቢው ይህን ተሞክሮ እንዲያሰፉትም በማድረግ ላይ ነን።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አገር ያለው የተፋሰስ ቁጥር ምን ያህል ነው? እየለማ ያለውስ?**

**ዶክተር ጌቴ፡-** እንደ አገር ከሦስት ሺ በላይ ተፋሰሶች አሉ። ይሁንና እነዚህ ሁሉ የእኛን አካሄድ እየተከተሉ አይደለም። ነገር ግን ያንን እንዲከተሉ ለማድረግ እየሞከርን ነው። ምክንያቱም ለግብርና ሚኒስቴር የዘላቂ የተፋሰስ ልማት፣ የክህሎትና የመረጃ ሥርዓቱን ዲዛይን አድርገንላቸዋል። በዛ ውስጥ የእኛ የመማሪያ ተፋሰሶች ተሞክሮ ሶፍትዌር ውስጥ እንዲገባ አድርገነዋል። ፍላጎታችንም ቀስ በቀስም ቢሆን ወደዚህ ሥርዓት እንዲገቡ ማድረግ ነው። እኛ የመማሪያ ተፋሰሶችን ከስድስት ወደ 24 አሳድገናል፤ ከተሳካልን ደግሞ ተጨማሪ አስር የመማሪያ ተፋሰሶችን በእምነት ቤዝኖች ከቀጣዩ ዓመት ጀምሮ ለመስራት ተዘጋጅተናል። መንግሥት ደግሞ በተረጋጋ ሁኔታ ከቀጠለ ያልኩሽን ጥናት ይፋ እናደርጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- ከመሬት ጋር ተያይዞ ወደምትሰሩት ሥራ እንምጣ ዶክተር?**

**ዶክተር ጌቴ፡-** ከመሬት ጋር ተያይዞ የምንሰራው ሁለት መሰረታዊ ሥራዎችን ነው። አንደኛው የመሬት አጠቃቀም ለውጡ ምን ይመስላል? የሚለውን መፈተሽ ነው። አንዱ የሦስተኛ ዲግሪዬ አካል እሱ ነው። በዚህም ጥናቴ አሁን ያለው የመሬት አጠቃቀም ሁኔታ በጣም ያስፈራል። ምክንያቱም ደኖች በከፍተኛ ሁኔታ እየተመነጠሩ ነው፤ በኢንቨስትመንት ስምም ሆነ ከተሞችን ለማስፋፋት በሚል እየተመነጠረ ነው። ረግረጋማ ስፍራ አሁን አሁን በነዋሪው መስፈር የተነሳ እየተወገደ ነው። ረግረጋማ ስፍራዎች ግን በርካታ ጠቀሜታ ያላቸው እንደመሆናቸው መጥፋት የለባቸውም።

**አዲስ ዘመን፡- ብዙዎች ረግረጋማ ቦታን የመሬት ኩሳሊት ነው እስከማለት ይደርሳሉና ስለዚህ ቦታ ይንገሩን እስኪ?**

**ዶክተር ጌቴ፡-** ረግረጋማ ቦታዎች ትልቁ ጥቅማቸው የከርሰ ምድር ውሃን መልሶ እንዲያገግም ማድረጊያ ስፍራዎች ናቸው። ሌላው ቀርቶ በአንድ ስፍራ ያለው ረግረጋማ ቦታ ለየትኛው ስፍራ የከርሰ ምድር ውሃ እንደሚያጎለብት ራሱ አይታወቅም። ረግረጋማ ቦታን ማጥፋት ማለት የውሃውን ምልልስ እንደማበላሸት ይቆጠራል። በረግረጋማ ቦታ መጥፋት ምክንያት የሚጠፋ ጥልቅ ውሃ ይኖራል። ሁለተኛው ፋይዳው አካባቢውን የመቀየር አቅም አለው። ብዝሃ ሕይወትን የማነቃቃት አቅም አለው። በአግባቡ ራሱን እየተቆጣጠረ የሚሄድ የተፈጥሮ ሥርዓትን ማዛነፍ ዋጋ ያስከፍላል። ስለዚህ ለዚህም ቦታ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

በዚህ ዙሪያ ልክ እንደ ውሃው ሁሉ የመሬት አሁናዊ አቅምንም ጭምር ዝርዝር ጥናት አጥንተን ለመንግስት አቅርበናል። በተለይ ከመናገር ይልቅ ያለውን አስፈሪ አካሄድ እንዲያስተውሉ በሚል በተለያየ አምስት አቅጣጫ ከአዲስ አበባ ጎንደር፣ ጅማ፣ መቀሌ፣ ነቀምት ሐዋሳና አዳማ በኋላ ላይ ሰመራንም ጨምርንና በእያዳንዱ አቅጣጫ ከመንገዱ 20 ኪሎ ሜትር በግራም በቀኝም 40 ኪሎ ሜትር ዲያሜትር ያለውን ቦታ ወስደን ዝርዝር ጥናት አጠናን። እኤአ ከ1985 ጀምሮ እስከ 2016 ድረስ የመሬት ለውጡ ምን ይመስላል? የሚለውን ዝርዝር ጥናት የያዘ ጥናት ነው። በጥናታችን ደኖች መመንጠራቸውን፣ ረግረጋማ ቦታዎች ወደእርሻነት መቀየራቸውን፣ ከተሞች መስፋታቸውንና ሌላም ዝርዝር ሁኔታ ለቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ለክቡር አቶ ኃይለማርያም አቀረብንላቸው። ጥናቱን ማቅረብ እንድንችል የግብርና ሚኒስቴር በጣም አግዞናል።

በወቅቱም በጥናታችንም መፍትሔ የሚሆነውን አመላክተናል። በተለይ ጉዳዩ በዘፈቀደ የሚሄደው አገሪቱ የመሬት ፖሊሲ ስለሌላት ነው። የመሬት አጠቃቀም ፕላንም የላትም። ስለዚህ እርሳቸውም በወቅቱ ፖሊሲውም ፕላኑም እንዲወጣ ሴክሬታሪያት እንዲቋቋም ተደርጎ ስራም ተጀምሮ ነበር። በዚህ መሃል ለውጡ በመምጣቱ በአሁኑ ወቅት የት እንዳለ አላውቅም። እኛ በወቅቱ ያጠናነው እኤአ እስከ 2016 ያለውን ነበር፤ አሁንም እስከ 2022 ያለውን ለውጥ እያየነው ነው። አሁን ላይ የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራሙ በተወሰነ ደረጃ እገዛ ያደረገ ይመስላል።

ሌላው በትኩረት የምንሰራው የመሬት አያያዝ ላይ ነው። የተፋሰስ ልማት ሲባል ዝም ብሎ የአፈርና ጥበቃ ስራ አይደለም። ችግኝ መትከልም ብቻ አይደለም። ቅንጅታዊ ስራ መሆን አለበት። የተፋሰስ ልማት በአጭር ጊዜ የሚያስገኙ ሁለት ጥቅሞች አሉት። አንዱ ሕዝቡ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ እንዲይዝ ማድረግ ነው። እንዲያ ሲሆን፣ ምርታማነት ይጨምራል፤ መራቆት አይኖርም፤ የአየር ንብረት የሚያመጣውን ተጽዕኖ መቋቋም ያስችላል።

ሁለተኛው ደግሞ የረጅም ጊዜ ጥቅም ሲሆን፣ የተራቆቱ ቦታዎች እንዲያገግሙ ማድረግና ምርታማ መሬት ማድረግ መቻሉ ነው። በዚህ ስራ ጠፍቶ የነበረው ምንጭ ይጎለብታል፤ ብዝሃ ሕይወት ይመጣል። በዘላቂነት ግን ሶስት ጥቅም አለው፤ አንዱ ጤናማ ኢኮሲስተም ሰርቪስ እንዲመጣ ያደርጋል፤ ኑሮን ያሻሽላል፤ በአየር ንብረት ጉዳት እጅ የማይሰጥ ሁኔታ ይፈጠራል። አሁን እኛ በምንከተለው ተፋሰሶች ላይ በተግባር እያሳየን ያለነው እሱን ነው። እርከን ብቻ ከምንሰራ ሌሎች ቋሚ የሆኑ ተክሎችንም መትከል አዋጭ ነው። እኛ ተፋሰስ ላይ ይህ ሁሉ አለ። በየተፋሰሱ ካሉ ነዋሪዎች ቢያንስ አብዛኛዎቹ የሚኖሩት በተስተካከለ የአኗኗር ስርዓት ሲሆን፣ ሌሎቹም ወደዚህ ስርዓት እንዲገቡ ተሞክሮዎችን እያጋራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በጣም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ጌቴ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## የጤናው ዘርፍ የደረሰበትን ደረጃ ያሳየ አውደ ርዕይ

**እፀገነት አክሊሉ**

ጤና መሰረታዊ ከሆኑ የግለሰብ፣ የህዝብና የአገር ጉዳዮች መካከል ግንባር ቀደም ነው። ጤና ካለ ሰርቶ ቤተሰብንና አገርን መደገፍ ማሳደግ ይቻላል። ጤናው የተጠበቀ ማህበረሰብም በተሰማራበት መስክ ሁሉ ምርታማ ሆኖ አገሩ የምትፈልግበትን ለመወጣት አቅም አያንሰውም። ጤና ከጠፋ የትኛውም የማህበረሰብ ክፍል አምራች ከመሆን ይልቅ ለቤተሰብ እንዲሁም ለአገር ሸክም የመሆን እድሉ የሰፋ ነው።

ጤና ሚኒስቴር በየጊዜው የአገሪቱን የጤና አጠባበቅ ስርዓት ከፍ የሚያደርጉ የተለያዩ ስራዎችን በራስ አቅም እንዲሁም ከአጋር ድርጅቶችና መንግስታት ጋር በመሆን ይሰራል። በዚህም በርካታ አወንታዊ ለውጦችን በተለያዩ የጤና ሴክተሮች ላይ ማምጣት ተችሏል። ይህም በግልፅ የሚታይ ተጨባጫ ለውጥ ስለመሆኑ ብዙ ማሳያዎች አሉ። ጤና ሚኒስቴር የህብረተሰቡን የጤና አጠባበቅ ስርዓት ከፍ ለማድረግ የህክምና ተቋማትን እስከ ገጠር ድረስ ማስፋት ችሏል። የጤና ባለሙያዎችን ቁጥርም በማሳደግ ተደራሽነታቸውን ማስፋት ተችሏል። የመድሃኒት አቅርቦቱ በተቻለ መጠን ሁሉን አቀፍ የሚሆንበትን መንገድ በማመቻቸትም ምስጉን ስራ አከናውናል።

የእናቶችና ህጻናት ጤናን የሚያሳድጉ አሰራሮችን ከገጠር እስከ ከተማ በመዘርጋት የእናቶችን ሞት ቀድሞ ከነበረበት ደረጃ እንዲቀንስ በማድረግ የተከናወኑ ስራዎችም ትልቅ ለውጥ በማምጣታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን አስመስግነውታል።


ጤና ሚኔስቴር እስከ አሁን በዘርፉ ያከናወናቸውን ስራዎች እንዲሁም አገሪቱ በዘርፉ የደረሰችበትን ደረጃ የሚያሳይ ለአንድ ወር የሚቆይ አውደ ርዕይ ከሰኔ 13/2015 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ሳይንስ መዚየም አዘጋጅቷል። አውደ ርዕዩ በጤናው ዘርፍ ስላለው ነባራዊ ሁኔታ ለማወቅና ለመወያየት በር የሚከፍት መሆኑም ተነግሯል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት በይፋ የተጀመረው አውደ ርዕይ በጤናው ዘርፍ ከአገር በቀል ዕውቀቶች ጀምሮ ዘመኑ እስካፈራቸው አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የሕክምና ቴክኖሎጂዎች ኢትዮጵያ የደረሰችበትን ደረጃና የተጓዘችባቸውን የዕድገት መንገዶች እንዲሁም የወደፊቱን የጤናው ዘርፍ አቅጣጫዎች የሚያመላክቱ ናቸው። ነጻ የጤና ምርመራን ጨምሮ ሌሎች ሁነቶችም ለእይታ የሚቀርቡበት ነው። አገር አቀፍ የጤና አውደ ርዕዩ የጤና ሚኒስቴር ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት እና ከኢትዮጵያ ጤና ክብካቤ ፌዴሬሽን ጋር በመተባበር «የመጪው ትውልድ ጤና» በሚል መሪ ቃል ያዘጋጀው ሲሆን፤ ከአንድ መቶ ሺ በላይ ጎብኚዎች ይመለከቱታል ተብሎ ይጠበቃል።

በአውደ ርዕዩ ለእይታ ከቀረቡ በርካታ የጤናው ዘርፍ እሴቶች መካከል ከኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ ጋር አብሮ የዘለቀው የባህል ህክምና አንዱ ነው። የባህል ህክምና ዘርፍ በተለያዩ የህክምና አሰጣጥ ዘዴዎች ተግባራዊ የሚሆንና በተለያዩ አካባቢዎች ትልቅ ቦታ ተሰጥቶች ብዙዎች የሚጠቀሙበት ነው። ዘርፉ የተለያዩ አገር በቀል እፅዋት በመቀመም በአገር በቀል እውቀትና ጥበብ ፈዋሽ መድሃኒቶች የሚዘጋጁበት ከመሆኑ አንጻር በአውደ ርዕዩ ትልቅ ትኩረት አግኝቶ ጎብኚዎች የማያውቁትን እንዲያውቁ እንዲጠቀሙበት ግንዛቤ ለመፍጠር ትልቅ እድል ሆኗል።

‹‹ይህ የአገር በቀል ህክምና ኢትዮጵያ ከምትታወቅበት የተለያዩ አገር በቀል እውቀቶች ግንባር ቀደሙም ነው›› ይላሉ በአውደ ርዕዩ ላይ የተገኙት የባህል ሐኪም አብርሃም ዋለልኝ ለአዲስ ዘመን አስተያየት ሲሰጡ። እንደ ባህል ሐኪሙ ማብራሪያ፣ አገር በቀል የባህል ህክምና ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ የመጣ ነው። የሚዘጋጀውም ከእጽዋት፣ እንስሳት እንዲሁም ከማዕድናት ነው። እነዚህ የተዘጋጁ መድሃኒቶችም ለተለያዩ ህመሞች ፈውስን የሚሰጡ ናቸው።

የባህል መድሃኒቶች ትልቅ ጥቅም ይኑራቸው እንጂ እውቀቱንም ግብዓቶቹንም በደንብ እንዳልተጠቀምንባቸው የሚናገሩት የባህል ሐኪም፣ በኢትዮጵያ ከ 7 ሺ በላይ የሚሆኑ ለመድሃኒትነት የሚያገለግሉ እጽዋቶች እንዳሉ ይጠቁማሉ። ከዚህ እምቅ ሀብት ግን በአግባቡ የተጠቀምንበት እምብዛም መሆኑን ነው የባህል ሀኪሙ የሚናገሩት። ይሁን እንጂ አገር በቀል የህክምና አሰጣጥ በፊት ከነበረበት ደረጃ አሁን ላይ ብዙ መሻሻሎች እንዳሉ አልሸሸጉም። ይህን ሲያስረዱም ‹‹ከዚህ በፊት እውቀቱ



እንዲሁም ባለሙያው የተለያዩ ስያሜዎች እየተሰጡት ወደኋላ የመቅረት ሁኔታ ነበር፤ ዛሬ ላይ ግን ከጊዜው ጋር እየተራመደና ለብዙዎች አገልግሎት እየሰጡ ነው›› ይላሉ።

የባህል ህክምና እውቀቶች አገር በቀል ቢሆኑም ከዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ጋር እንዲናበቡ ብሎም ከዘመናዊው ህክምና ሳይንስ ጋር እንዲገናኙ ለማድረግ ባለሙያዎች እንዲሁም ጤና ሚኒስቴር ብዙ ስራ እየሰራ መሆኑን የሚናገሩት የባህል ሀኪሙ፣ በዚህም ጥሩ መሻሻሎች እየታዩና ለወደፊቱም ተስፋ ሰጪ ነገሮች እየመጡ ህብረሰተሰቡም በሚገባ እየተጠቀመበት እንደሚገኝ ያብራራሉ።

ጤና ሚኒስቴር በየጊዜው ከሚያወጣቸው ፖሊሲዎች አንዱና ግንባር ቀደሙ የባህል ህክምና አሰጣጥን ማሻሻል ነው። በዚህም ከዚህ በፊት የነበሩ ኋላ ቀር አሰራርና ልምዶች ወደዘመናዊ እንዲቀየሩ በማድረግ በኩል ሰፊ እንቅስቃሴን በማድረግ ባለሙያውም እየተበረታታ እውቀቱን በሚገባ አውጥቶ እንዲጠቀም ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህም ከመንደር አልፎ እንደ አገር ተደራጅቶ ውጤታማ ከመሆን በዘለለ አገርን በዘርፉ ሊያስጠራ የሚችል ተግባር መሆኑን የባህል ሐኪሙ ተናግረዋል።

ጥናቶች ባይደረጉም አሁን ባለው መረጃ መሰረት ከ 80 በመቶ በላይ የሚሆነው የህብረተሰብ ክፍል በአንድም በሌላ መንገድ የባህል ህክምና ተጠቃሚ መሆኑን የሚጠቁሙት የባህል ሐኪም፣ ለዚህ ማሳያ ነው የሚሉት በተለያዩ ዘመናዊ ህክምናዎች ፈውስ ያልተገኘላቸው የህመም አይነቶች በባህል ህክምና እየዳኑ መሆኑ ነው። ከዚህ አንጻርም አሁን ያለው የዜጎች የባህል ህክምና አጠቃቀምና ፍላጎት ተስፋ የሚሰጥ፣ ባለሙያውንም ለተጨማሪ ስራ የሚያነሳሳ መሆኑም ያብራራሉ።

‹‹ባህል ህክምናን ከዘመናዊው ህክምና ጎን ለጎን በመስጠት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ መንግስት እንዲሁም ባለእውቀቱ በርካታ ስራ እየሰራ ይገኛል፤ እንደዚህ ባለ ትልቅ አውደ ርዕይ ላይ እንድንገኝ መደረጉም ለስራው የተሰጠውን ትኩረት ያሳያል፤ በመሆኑም በቀጣይ ህብረተሰቡን ከህመም የሚያድኑ የጎንዮሽ ጉዳታቸው ዝቅተኛ የሆኑ መድሃኒቶችን ለማዘጋጀት እንሰራለን›› በማለት የባህል ሐኪም አብርሃም አውደ ርዕዩ የፈጠረባቸውን ተነሳሽነት ተናግረዋል።

የባህል ሐኪሙ እንደሚናገሩት፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለባህል ህክምና የተሰጠው ትኩረት ጥሩ ቢሆንም ባለሙያዎች እውቀታቸውን አሳድገው ምርቶቻቸውን ወደሌሎች አለማት በመላክ ኢትዮጵያን በህክምናው ዘርፍ ለማሳወቅ ወይም ለማስጠራት የሚያደርጉት ጥረት የመንግስትን ድጋፍ ይሻል። በሌላ በኩል ዝርያቸው በመጥፋት ላይ ያሉ ግን ደግሞ ከፍ ያለ የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ተክሎችን በመጠበቅና በመንከባከብ ከተቻለም ወደአንድ ማዕከል የሚሰበሰቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ዘርፉን ኢንደስትሪያላይዝ ማድረግ ያስችላል።

ሌላው በአውደ ርዕዩ የቀረበው የፌደራል የሰቆጣ ቃል ኪዳን ስምምነት (ዲክላሬሽን) ሲሆን የስምምነቱ ሲኒየር የፕሮግራም ማኔጀር ዶክተር ሲሳይ ሲናሞ አውደ ርዕዩን ሲያስጎበኙ ‹‹የስርዓተ ምግብ በአገር ኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ላይ የሚኖረውን አወንታዊ ሚና ለማሳካት እንደ አገር 14 ሴክተሮች በጋራ ሆነው የሚተገብሩት የ10 ዓመት የምግብና ስርዓተ ምግብ ስትርቴጂና የሰቆጣ ስምምነት ትግበራ ነው›› በማለት ያስረዳሉ።

እንደ ዶክተር ሲሳይ ገለፃ፣ በአውደ ርዕዩ ይዘው የቀረቡት በተለይም በሙከራ ትግበራው በ5 ዓመት ውስጥ በአማራና በትግራይ 40 ወረዳዎች ላይ መቀንጨርን በዓመት እስከ 3 በመቶ ለመቀነስ በተሰራው ስራ ትልቅ ተሞክሮ መገኘቱን ለማሳየት ነው። ይህንንም ተሞክሮ ከ 2014 ዓ.ም ጀምሮ በ 140 ወረዳዎች ላይ እየተተገበረ ይገኛል። ይህም በብዝሃ ሴክተር ተባብሮ ማህበረሰብን ባለቤት የማድረግ ውጤት መሆኑን የሚያሳይ ነው።

እንደ አገር በ2022 ዓ.ም መቀንጨርን ዜሮ ለማድረግ የተቀመጠ ግብ መኖሩን የሚጠቁሙት ዶክተር ሲሳይ፣ ሌሎችም የስርዓተ ምግብ ግቦች ያሉ በመሆኑ እነዚህን ለማሳካት የብዝሃ ሴክተር ቅንጅትና ትብብርን ማጠናከር፣ በዚህም የአመራሩ ድጋፍና ቁርጠኝነት ማስቀጠል እንዲሁም ለትግበራው የሚያስፈልገውን የገንዘብ ድጋፍ ማሟላት አስፈላጊ መሆኑንም ይናገራሉ።

‹‹የጤናው ሴክተር እናቶችን ህጻናትንና አፍላ ወጣቶችን ተደራሽ ለማድረግ የሚተገብራቸው የስርዓተ ምግብ ልየታ፣ የእድገት ክትትል እንዲሁም የምክር አገልግሎትና ስርዓተ ምግብ ችግር ያለባቸውን ህክምና መስጠት አለ›› የሚሉት ዶክተር ሲሳይ በማህበረሰብ ደረጃ በአካባቢ የሚመረቱት ምግቦችን አሰባጥረው እንዲመገቡ በማስተማር ረገድ ሰፊ እንቅስቃሴ በመኖሩ ውጤትም እየታየበት እንደሚገኝ አስረድተዋል።

የተለያዩ ንጥረ ምግቦችን በአስፈላጊ ሚኒራሎች በማበልጸግ ማህበረሰቡ እንዲጠቀም የማስተማር ስራም እየተከናወነ እንደሚገኝ ያነሱት ዶክተር ሲሳይ፣ አሁን ያለበት ደረጃ ጥሩ የሚባል መሆኑን ይናገራሉ። ባለፉት 20 ዓመታት መቀንጨር ከ 58 በመቶ ወደ 37 በመቶ ማውረድ መቻሉ ደግሞ ለዚህ ማሳያው ነው ይላሉ። ነገር ግን በሌሎች እንደ ድርቅና ጦርነት፣ የዓለም የምግብ ዋጋ መናር ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የሆነ የምግብ ችግር በዓለምም በአገራችንም እየተስተዋለ ስለመሆኑም ያብራራሉ። እነዚህ አባባሽ ምክንያቶችም ሁኔታውን ወደነበርንበት እንዳይመልሱ ለማድረግ የተለያዩ ስራዎች በመሰራት ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል። ‹‹መቀንጨር በሰው መታመምና መሞት በትምህርትና ፈጠራ ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም ምርታማነት ላይ የቀነሰ ውጤት ማምጣት በሚል ከዚህ በፊት ጥናት ተደርጓል፤ በውጤቱም እንደ አገር ከአጠቃላይ እድገታችን 16 በመቶ ያህል እንደምናጣ አሳይቷል፤ ይህ ማለትም ትልቅ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እድገት ተግዳሮት ነው፤ በዚህ የተነሳም መንግስት ከሁለት ዓመት በታች ያሉ ህጻናትን ከመቀንጨር ነጻ ለማድረግ እየሰራ ይገኛል›› ሲሉም አክለዋል።

የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ኮሌጅን በመወከል የተቋሙን የታካሚዎች መስተንግዶና የመረጃ አያያዝ በአውደ ርዕዩ ለማሳየት የተገኙት ሐኪምና መምህር ዶክተር ቱሉ ጌቱ ሲያብራሩ፣ ከዚህ ቀደም ወደሆስፒታሉ የሚመጡ ታካሚዎች ካርድ እየወጣላቸው ነበር የሚስተናገዱት። ዛሬ ላይ ግን ይህ አሰራር በዘመናዊ መልኩ ተቀይሮ የታካሚው መረጃ ወደ ኮምፒውተር ገብቶ ለሐኪሙ የሚላክበትና ከሐኪሙም ወደ ላብራቶሪ ክፍል እንዲሁም መድሃኒት ቤት መረጃዎች የሚሰራጩበት አሰራር ተፈጥሯል። ሆስፒታሉ በዚህ መልክ ስራውን ከጀመረ በኋላም ምንም ዓይነት የታካሚ መረጃ እንደማይጠፋ ገልጸው፣ ሐኪሞችም መረጃዎችን ቶሎ ቶሎ ስለሚያገኙ አገልግሎቱ ቀልጣፋ ከወረፋ የጸዳና በአንድ ቀን ብዙ ታካሚዎች የሚስተናገዱበትን እድል መስጠቱን ይናገራሉ።

ይህም የታካሚዎች መረጃ በዚህ መልኩ መያዙ ወደፊት ሆስፒታሉም ሆነ ጤና ሚኒስቴር እንዲሁም ሌሎች በአገሪቱ ላይ የበዛው በሽታ የትኛው ነው? የሚለውን ለማጥናት ቢፈልጉ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ስለመሆኑም ተናግረዋል። ይህንን ተሞክሮ የተከተሉ ሌሎች በርካታ ሆስፒታሎች እንዳሉም አክለዋል።

በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል የላብራቶሪ ባለሙያ የሆኑት አቶ ሞገስ ተስፋዬ በበኩላቸው፣ ሆስፒታሉ በዓለም ላይ ላቅ ያሉ የላብራቶሪ ማሽኖችን አስገብቶ ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ ይናገራሉ። ባለሙያው የደም ቆጠራ (የደም ምርመራ) የሚደረግበት በጣም ዘመናዊ ማሽን ይዘው በአውደ ርዕዩ የቀረቡ ሲሆን ይህ ማሽንም በአንድ ጊዜ መቶ ያህል የደም ናሙናዎችን ተቀብሎ በፍጥነት ሰርቶ ውጤቱን ማውጣት የሚችል ሲሆን ቀድሞ ከነበረው ጋርም ሲነጻጸር በብዙ ጊዜና ገንዘብን የቆጠበ መሆኑ አስረድተዋል። ከዚህ በተጨማሪ ባለሙያው በአውደ ርዕዩ ይዘው የቀረቡት ቴክኖሎጂ የጉበት፣ ኩላሊት፣ ኮሊስትሮልና የስኳር ምርመራዎችን በፍጥነትና በአስተማማኝ ሁኔታ የሚሰራ ሲሆን ሌላው የሳንባ በሽታን የሚመረምር ማሽን ነው። በተለይም የሳንባ ምርመራን የሚያደርገው ማሽን ከዚህ ቀደም ውጤት ለማውጣት 2 ሰዓት ይወስድበት ከነበረው ማሽን አኳያ እጅግ ዘምኖ በ90 ደቂቃ ውስጥ ውጤት የሚያሳውቅ መሆኑንም ይናገራሉ።

አቤት ሆስፒታል የድንገተኛ ህክምን ክፍል እየሰጠ ያለውን አገልግሎት በተመለከተም የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ዶክተር ወልደሰንበት ዋጋ ገለፃ ሲያደርጉ፣ አቤት ሆስፒታል በአገሪቱ የድንገተኛ ህክምናዎችን በመስጠት ብቸኛውና የመጀመሪያው ሆስፒታል መሆኑን ያስረዳሉ።

አቤት ሆስፒታል በአገሪቱ ብቸኛውና የመጀመሪያው የድንገተኛ ህክምና መስጫ ተቋም በመሆኑ ብዙ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም ማሽኖች ይዟል። ድንገተኛ ህክምና ደግሞ ከበር ጀምሮ ልየታ የሚሰራለት ሲሆን በቀደመው ጊዜ ማንኛውም ታካሚ ድንገተኛም ቢሆን ካርድ አውጥቶ መደበኛ ሂደቱን ተከትሎ ነበር ወደ ሐኪም የሚገባው። አሁን ግን ከበር ጀምሮ ታካሚው በምን ሁኔታ ውስጥ እንዳለና ምን ዓይነት አገልግሎት ሊያገኝ እንደሚገባው በመለየት ነው ስራው የሚጀምረው። ታካሚው መጠበቅ የሚያስችል የጤና ሁኔታ ላይ ካለ ደግሞ ወደሌላ ክፍል የሚላክ ሲሆን አጣዳፊና ድንገተኛ ከሆነ ግን በድንገተኛ ህክምና መስጫው ላይ በተሟላና ዘመናዊ በሆኑ የህክምና መሳሪያዎች እርዳታ እንዲያገኝ እንደሚደረግ ከዶክተር ወልደሰንበት ማብራሪያ መረዳት ተችላል።

በአውደ ርዕዩ ላይ አነስተኛ የድንገተኛ ህክምና መስጫ ማዕከል ይዘው የቀረቡት ዶክተር ወልደሰንበት፣ በጽኑ ታሞ የመጣ ሰው ሲያጋጥም ባለሙያዎች ሁሉ የያዙትን ትተው ሙሉ ትኩረታቸውንና ጊዜያቸውን እንዲሁም እውቀታቸውን እንደሚሰጡ ማሳያ አድርገዋል። በዚህም እርዳታ የሚፈልገው ታካሚ ደም እየፈሰሰው ከሆነ ደሙን የማቆም፣ ራሱን የሳተም ከሆነ ወደ ራሱ የሚመለስበትን መንገድ በመድሃኒትና በዘመናዊ የህክምና መስጫ ግብዓቶች በመታገዝ ስራዎች እንደሚሰሩ መሳሪያዎቹን በማሳየት ያስረዳሉ።

የድንገተኛ ክፍሉ በተለያዩ ማሽኖች የተሟላ ከመሆኑም በላይ በጽኑ ለታመመና ከፍ ያለ ክትትል ለሚያስፈልገው ሰው ስድስት ሐኪምና ነርሶች በአንድ ላይ ይመደቡለታል። መድሀኒቶቹም ከእየአይነቱ በአቅራቢያው እንዲሆኑ ይደረጋል። በዚህም የተሳካ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት መስጠት እንደተቻለ አብራርተዋል። ይህ በአገራችን አዲስ አሰራር ከመሆኑ አንጻር ብዙ ውጤቶች እየታዩበት ነው። ነገር ግን አሁንም የባለሙያዎች ቁጥር ማነስ በተለይም ከአዲስ አበባ ውጪ አገልግሎቱ በዚያ ልክ የተጠናከረ አለመሆኑ አሁንም ዘርፉ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚያስፈልግ ዶክተር ወልደሰንበት ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አውደ ርዕዩን በከፈቱበት ወቅት፤ በአሁኑ ወቅት ጤና ዓለምን ከሚያሰጉና በቀጣይም ከፍተኛ ተግዳሮት ከሚሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ መሆኑን ጠቅሰው የጤና ጉዳይ በኢትዮጵያም ቢሆን አሳሳቢ ከሚባሉትና ትኩረት ተሰጥቷቸው እየተሠራባቸው ከሚገኙ ቀዳሚ አገራዊ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነውና አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ ተናግረዋል። እንደዚህ አይነት ኤግዚቢሽኖች መዘጋጀታቸው ደግሞ በጤናው ዘርፍ ስላለው ነባራዊ ሁኔታ ለማወቅና ለመወያየት በር እንደሚከፍት አስረድተዋል።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "ቋሚ ወዳጅም ሆነ ቋሚ ጠላት…!?"

**ታሪካዊ ዳራ፤**

ሄኒሪ ጆን ቴምፕል (1784 - 1865) ታላቋን እንግሊዝ ለአሥር ዓመታት በጠቅላይ ሚኒስትርነት በመምራት ታሪካቸውን በደማቁ ያጻፉ የፖለቲካ ሰው ነበሩ። የሌበር ፓርቲን ከምሥረታ እስከ ተጽእኖ ፈጣሪነት በማድረስ አንቱታን ያተረፉት እኚህ የእንግሊዝ ፖለቲከኛ የአመራር ዘመናቸው የተሳካና ዛሬም ድረስ የሚጠቀስላቸውን በርካታ ውጤታማ አሻራ አሳርፈው እንዳለፉ የሀገራቸው የታሪክ ዘርፍ ምሁራን በየመጻሕፍታቸው አዘውትረው ይጠቅሷቸዋል።

ሚ/ር ቴምፕል ሀገራቸውን በመራሄ መንግሥት ዘመነ ሥልጣን በመሩባቸው ዓመታት የሚደነቁትና የሚወደሱት ባስመዘገቧቸው ስኬቶች ብቻ ሳይሆን በዘመን ተሻጋሪ አባባላቸው ጭምር ነው። እንዲህ ነበር ያሉት፡- "We have no eternal allies, and we have no perpetual enemies. Our interests are eternal and perpetual."

አባባላቸው በተቀራራቢ ትርጉም ወደ ቋንቋችን ሲሸጋገር እንዲህ የሚል ፍቺ ይሰጠናል። "እኛ ዘለዓለማዊ የምንለው ጠላትም ሆነ ወዳጅ የለንም። ዘላቂና ዘለዓለማዊ የምንለው የግል ጥቅማችንን ብቻ ነው።"

እጅግ በርካታ የዓለም ሀገራት ፖለቲከኞችና ዲፕሎማቶች ይህንን አባባል ዛሬም ድረስ የንግግራቸው መክፈቻ፣ የድርድራቸው አጀንዳና የዕቅዳቸው ግብ በማድረግ ጭምር ሲናገሩትና ሲተገብሩት የኖሩት መርህ ነው። ለብሔራዊ ጥቅማቸው ማስተግበሪያም እንደ ዋነኛ ፖሊሲ በመቀበል "የእንካ በእንካ" ስምምነቶችንና ውሎችን ይፈጽሙበታል።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተፋላሚ አገራት ተቀዳሚ ተዋንያን መካከል፡-

"በቸርችል ጎዳና በአንቺ አረማመድ፣
እንዴት ይዘለቃል ይህ ሁሉ መንገድ"

ተብሎ ይደነቅ የነበረውና ዛሬም ሞገሱ ያልደበዘዘው የከተማችን ዋና ጎዳና በስማቸው የተሰየመላቸውና ጠቢቡ የአገሬ ሽማኔ በአንድ ወቅት "ቸርችል ጎዳና" የሚል የወይዛዝርት የጥበብ ዓይት በስማቸው የሰየመላቸው፣ "የወዳጅ አገር መሪ" እና "ፀሐይ በግዛቴ አትጠልቅም" ባዩዋ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ዊንስተን ቸርችል የቀዳሚ መሪያቸውን የሚ/ር ቴምፕልን ጥልቅ አባባል እጅግ አግዝፈው በማስታወስ እንዲህ በማለት የወቅቱን የአገራቸውን ፖሊሲ ለዓለም ማህበረሰብ አስታውቀው ነበር።

"I am ready to put my hands in the hands of the devil for the progress of my country." ውርስ ትርጉም፡- "ለአገሬ ዕድገት የሚበጅ መሆኑን ካረጋገጥሁ፤ ከሰይጣንም ጋር ቢሆን እጅ ለእጅ ተጨባብጬ ወዳጅነት ለመፍጠር አላመነታም።" አባባሉን በተመለከተ ብዙዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩን የተቹም ያሞገሱም አልታጡም። አንዳንዶችም "ሥነ ምግባር የጎደለው ንግግር ነው" ብለው አምርረው ቢቃወሙም እውነታውን ስንፈትሽ ግን ከዓለም የፖለቲካ እውነታ ጋር በሚገባ እንደሚጎዳኝ እንገነዘባለን። ለምን ቢሉ ለአገራት የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ትርፍ ሲባል ምን የማይደረግ ነገር ይኖራል?

በቸርችል አባባል እውነታነት የሚስማሙ ደጋፊዎች ዋነኛ የመከራከሪያ ነጥባቸውን እንዲህ በማለት ጮክ ባለ ድምጽ ለማስረዳት ይሞክራሉ፡ - "Politics is an art and the techniques of distinguishing different situations to make the best use of them for national interests" የዚህ አባባል አስኳል ሃሳብ "የፖለቲካ ጨዋታ በጥበብ የተቃኘ ነው። የአሸናፊነቱ ምሥጢር የሚለካውም ለአገር የሚጠቅም አንዳች ነገር ማውጣት ሲቻል ነው" የሚል ይሆናል።

ከመቶ ሰላሳ ዓመታት በላይ ያስቆጠረውን የጠቅላይ ሚኒስትር ቴምፕል አባባል እየጠቀሱ ለአገራቸው ጥቅም ሽንጣቸውን ገትረው ሲከራከሩ የኖሩና እየተከራከሩ ያሉ የዓለማችን ፖለቲከኞችና ዲፕሎማቶች ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ሄኒሪ ኪሲንጀርም ያንን ዘመን ተሻጋሪ ጥቅስ እንዳለ ቃል በቃል በመዋስ በተለያዩ መድረኮች ይጠቀሙበት እንደነበር ግለ ታሪካቸው ይመሰክራል። "እኛ አሜሪካኖች ቋሚ ወዳጅም ሆነ ቋሚ ጠላት ብለን የምንፈርጀው የለንም። ቋሚና የማይናወጠው መርሃችን የአሜሪካንን ፍላጎት ማስጠበቅ ብቻ ነው።"

"ወዳጅ ወዳጁን አይከዳም፤ ከጅብ ወዲያ ሆዳም" የሚለው አገርኛ ብሂል አበው በዓለማችን የፖለቲካ ጨዋታ ውስጥ የሚሠራ መርህ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ የብሉይ ኪዳንን አሥርቱን ትዕዛዛት በጥቂት ቃላት ወስኖ ለአዲስ ኪዳን ደቀ መዛሙርቱና ስሙን ለሚሸከሙ ምእመናን በሙሉ "ወንድምህን እንደ ራስህ ውደድ" ብሎ ያስተማረው ወርቃማ ትምህርት ከፖለቲካ አካሄድ ጋር ፍጹም ጠበኛ ነው።

በፖለቲካ መርህ መሠረት ትናንት በወዳጅነት እፍ ባለ ፍቅር ያበዱና የከነፉ መንግሥታት የየግላቸው ጥቅም የተነካ ሲመስላቸው ወይንም ጥቅም አልባ ሲሆንባቸው "እሣት ለብሰውና እሣት ጎርሰው" የፍልሚያ ሽማ ከመጣጣል አይመለሱም። የራስ ጥቅም ካልሆነ በስተቀር "ለአንተ እንዲደረግልህ የምትፈልገውን ለወንድምህም እንዲሁ አድርግለት" የሚለው የጽድቅ ምክር ከፖለቲከኞች ጆሮ የሚደርስ፤ ለትግበራም የሚጣደፉበት ዓይነት ግብረ ገብ አይደለም።

በዲፕሎማሲውም ሆነ በፖለቲካው ዐውደ-ሠፈር ምን ይሉኝና ርህራሄ እጅግም ዋጋ እንደሌለው ካረጋገጡ የዓለማችን መሪዎች መካከል "ብረቷ እንስት" የመሰኘት አድናቆት ያተረፉት የእንግሊዟ ጠቅላይ ሚኒስትር ማርጋሬት ታቸር በዚህ የአገርን ጥቅም የማስቀደም ተቀዳሚ ጉዳይ ሁነኛ ማሳያ ተደርጎ የሚጠቀስላቸው አባባላቸው እንዲህ የሚል ነበር፤፡- "There are no personal sympathies in politics." - "ግለሰባዊ ርህራሄ ከፖለቲካ ጋር የተፋታ ነው።"

ሲያሻቸው እርስ በእርስ ጠላቶች የሚሆኑትና ፍቅራቸው የጠና ሲመስላቸው ደግሞ "ቆሎ ካልተጓረስን" የሚሉት ድራጎኖቹ ቻይናዊያን፣ ድብ ነን ባዮቹ ሩሲያዊያንና በንሥር ከፍታ እንበራለን ብለው የሚመጻደቁት አሜሪካዊያን የሚያራምዱትን የፖለቲካ አካሄድ ሰከን ብለን ብንመረምር ወዳጅነትንና ጠላትነት በእነርሱ የፖለቲካ አይዲዮሎጂ ምን ያህል እንደ ገበቴ ውሃ እንደሚያዋልል ማስተዋል አይገድም።

እኛስ? ፡- "ልካስ ያለ ታግሶ፤ እጸድቅ ያለ መንኩሶ"

በአግባቡና በወጉ የመስካሪዎችን የታሪክ ገጽ ተነፈግን እንጂ እኛም ለሉዓላዊነታችን ክብር ስንል "ከሰይጣን ጋር ተጨባብጠ" ከማሸነፍ ይልቅ "ሆድ ከአገር ይሰፋል" በሚል የትዕግስት መርህ የበርካታ መንግሥታትን ሤራና ተንኮል ተቋቁመን ታሪካችንን ያስቀጠልንባቸው አጋጣሚዎች እጅግ በርካቶች ናቸው። ጥቂት የነበር አብነቶችን እናስታውስ።

> ## ወዳጅ ወዳጁን
> **አይከዳም፤ ከጅብ ወዲያ ሆዳም**

በሚያዝያ ወር 1911 ዓ.ም የመጀመሪያውን የዓለም ጦርነት በድል ለተወጡ የአውሮፓ መንግሥታት "የእንኳን ደስ ያላችሁ መልእክት" ለማድረስ አገሬ በሦስት የተለያዩ አገራት የዲፕሎማሲ መልእክተኞችን ልካ ነበር። ወደ እንግሊዝ አገር በደጃዝማች ናደው አባወሎ መሪነት ከንቲባ ገብሩና ብላቴን ጌታ ሕሩይ ወልደ ሥላሴ ያሉበት የልዑካን ቡድን ተሰማርቶ ነበር። በደጃዝማች ወልደ ገብርኤል በሻህ የሚመራው ቡድን ደግሞ ደጃዝማች ሺበሺ በየነንና አቶ ዘውገ ኃይሉን አካቶ ወደ ፈረንሳይ አቅንቶ ነበር። ለጣሊያን መንግሥት የተወከሉት ደግሞ ደጃዝማች ጌታቸው አባተ ሊቀ መኳስ መንገሻ ውቤ እና አዛዥ ደግፌ ነበሩ። (ምንጭ፡- ከቀዳማዊ እስከ ቀዳማዊ፤ አንድ ሺህ አንድ ጥያቄዎች፤ ገጽ 377-378)።

የአገሬን የእንኳን ደስ አላችሁ መልእክት የተቀበሉት እነዚህ አገራት ከአሥራ አምስት ዓመታት በኋላ የኢጣሊያ ሠራዊት በግፍ በወረረን ወቅት አሜሪካንን በአባሪነት ከጎናቸው በማሰለፍ ውለታችንን "አመድ አፋሽ" በማድረግ ወራሪው ጦር ሕዝባችንን የፈጀበትን የመርዝ ጋዝና የጦር መሣሪያ ድጋፍ አቾጎድጉደውለት ነበር።

ከላይ በጠቀስኩት መጽሐፍ ውስጥ ዝርዝራቸው እንደሚከተለው ተመዝግቧል። የአሜሪካ መንግሥት የመርዝ ጭስ (ሙስታርድ ጋዝ) እና ታንኮችን፤ የእንግሊዝ መንግሥት ቦንብ ጣይ፣ የመርዝ ጋዙን የሚረጩና መትረየስ የሚተኮስባቸው 100 ሮል ሮየስ የተባሉ ተዋጊ አውሮፕላኖችን፤ የፈረንሳይ መንግሥት ታንክ፣ መድፍና መትረየሶች።

እነዚሁ አገራት ለፋሽስቱ ጦር ከረዱት የጦር መሣሪያዎች በተጨማሪ በሊግ ኦፍ ኔሽን ስብሰባ ላይ የጣሊያን መንግሥትን ወረራ በመደገፍ ኢትዮጵያን በብዙ መልኩ ጎድተዋል። አሜሪካና የጃፓን መንግሥት የመንግሥታቱ ጉባኤ በጣሊያን ላይ ጥሎት የነበረውን የኢኮኖሚ እገዳ በመጣስ ለወራሪው የፋሽስት መንግሥት ነዳጅ ይሸጡ ነበር።

አሜሪካ በግሏ ለኢትዮጵያ ምንም ዓይነት የጦር መሣሪያ እንዳይሸጥና በተለያዩ መንገዶች የተገኙትም ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ክልከላ ጥላ ነበር። ይህቺው "ታላቅ ተብዬዋ አሜሪካ" የዚያድ ባሬ ጦር በ1969 ዓ.ም አገራችንን በወረረ ጊዜ በንጉሡ ዘመን የታዘዙት የጦር መሣሪያዎች እንዳይላኩ እግድ መጣሏ አይዘነጋም።

እጅግ የሚገርመው "የፖለቲካ ተውኔት" የተፈጸመው ደግሞ ጀግኖቹ አባቶቻችን ወራሪውን የፋሽስት ጦር ድል አድርገው ባንበረከኩ ማግሥት ቀድመው ደስታቸውን የገለጹት እነዚሁ "ቋሚ ጠላትም ሆነ ቋሚ ወዳጅ የለም" ለሚል ፍልስፍና የገበሩ አገራት ነበሩ። ንጉሡ ነገሥቱን ከስደት አጅበው የገቡት እንግሊዞች መሆናቸውን ስናስብና አሜሪካም የቃኘው ሻለቃን የጦር ሠፈር በአስመራ ለመገንባት እንደምን እንደተሽቀዳደመች እነርሱ ቢክዱም ታሪካችን በሚገባ ይመሰክርልናል።

ፈረንሳይም ብትሆን የአገሪቱ ዘመናዊ ትምህርት ፈረንሳይኛ እንዲሆን ያላደረገችው ጥረት አልነበረም። በ1930ዎቹ መጨረሻ በአዲስ አበባ የተከፈተው ሊሴ ት/ቤት መታሰቢያ ያደረገው ከፋሽስቶች ጋር ትንቅንቅ በማድረግ ለወደቁት ለጀግናው ገብረ ማሪያም ጋሪ ነበር። እንዴት ሆነ ቢባል አውሮፓዊያንም ሆኑ አሜሪካኖች ፍልስፍናቸው "Politics is an art…" የሚል ስለሆነ "የጉልበታቸውን ብርታት ታናናሽ በሚሏቸው መንግሥታት ላይ ለዘመናት ሲፈትሹ የኖሩት" የፖለቲካ ድራማ እየተወኑ ስለመሆኑ ጥሩ ማሳያ ይሆናል። የአገሬ ብሂለኛ፡- "ወግቶ ይማርህ" እንደሚለው መሆኑ ነው።

ዛሬም በኢትዮጵያ ላይ ሲያሻቸው የዲፕሎማሲ ጫና፣ ሲፈልጉ የእርዳታ እህል እቀባ፣ በሉ ሲላቸውም በመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ላይ የጉዞ ማዕቀብ፣ ጠንከር ሲልም የእርዳታና የብድር ገንዘብ የሚነፍጉን "እንደ እስስት የሚለዋወጠው" የፖለቲካና የዲፕሎማሲ መርሃቸው ግድ ስለሚላቸው ነው።

"ጠላት ሲነሳብህ ወዳጆችን አበርክት" እንዲል ብሂላችን፤ አገሬ ሁልጊዜ የእነርሱን ፊትና እጅ ከመጠበቅ አንድም የውስጧን ችግሮች በቤቷ ጨርሳ እፎይ በማለት ሙሉ ኃይሏን ወደ ልማት ብታዞር፣ አንድም አሁን እየተስተዋለ እንደሚታየው በጥበብ የተቃኘ የዲፕሎማሲ አካሄዷን አጠናክራ የምዕራባዊያኑን ሚዛን በሚያስጠብቅ አማራጭ መጓዙን ብትገፋበት ይበጅ ይመስለናል። የሚ/ር ቴምፕልን ግማሽ አባባል እንዋስና "Our interests are eternal and perpetual" ብለን ሃሳባችንን እንደምድም። ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

ፖስቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

## በልጆች የጨከኑ እጆች!

**ሶሎሞን በየነ**



ከአቶ መኮንን ኃይሉ እና ከወይዘሮ ፅጌ ገመቹ ከተባሉ አባትና እናቷ በ1995 ዓ.ም በኦሮሚያ ልዩ ዞን ሰንዳፋ ቀበሌ ልዩ ቦታው 44 ማዞሪያ ሥላሴ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ይችን ዓለም ተቀላቀለች። ቤተሰቦቿ ልጆቻቸውን እንደማንኛውም ወላጆች እርሳስ፣ እስክርቢቶ፣ ደብተር ገዝቶ ለማስተማር ይቅርና በቀን አንዴ መግቦ ለማስተዳደር ኑሮው ዳገት ሆኖባቸዋል። ከእጅ ወደ አፍ ያለፈ ተቀማጭ ጥሪትም አልነበራቸውም።

ልጃቸው ሕይወት መኮንን እደሜዋ ለትምህርት ቢደርስም ቤተሰቦቿ ለማስተማር አቅማቸው አልፈቀደም። መቼም በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን አይደለም አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና አፍንጫ ስር ይቅርና እልም ያለ ገጠር ውስጥ የሚኖር አርሶ አደር ስለ ትምህርት ጥቅም ጠንቅቆ ያውቃል ቢባል ማጋነን አይሆንም። አርሶ አደሩ ትናንት የትምህርት ጥቅሙንና እድሉን አውቆና አግኝቶ ሳይማር መቅረቱ "የእግር እሳት" ሆኖበት ዛሬ ላይ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካልገጠመው በስተቀር ልጁን ትምህርት ቤት የማይልክ ወላጅ አለ ብሎ መገመት ያዳግታል። ነገሩ "ማጣት ከሰማይ ይርቃል" እንዲሉ ሆኖ የሕይወት ቤተሰቦች ግን ልጃቸውን እንደኩዮቿ ቀለም እንድትቀስም ትምህርት ቤት ለመላክ አልቻሉም። በዚህም እኩዮቿ ደብተር ይዘው ጠዋት ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱና ሲማሩ ውለው ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ዘወትር ቤተሰቦቿ ሲያዩ የልጃቸውን እድል እንደሰበሩት፣ የነገ ተስፋዋን እንዳጨለሙት፣ ከእኩዮቿ በታች እንዳደረጓት እየተሰማቸው ቅስማቸው ይሰበራል። ልባቸው ያዝናል።

በተመሳሳይ ሕይወትም እኩዮቿ ጠዋት ማልደው እየቦረቁ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ፣ ከትምህርት ገበታቸው ውለው በአንድ ላይ ሰብሰብ ብለው የቆጥ የባጡን እያወሩ፣ እየተጫወቱ፣ እንደእምቦሳ ጥጃ እየዘለሉ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ስታይ እሷም እንደእኩዮቿ ትምህርት ቤት ባለመዋሏ ታዝናላች፣ ታለቅሳለች። የትምህርት ጣሙንና ጥቅሙን ለይታ የማታውቅበት የእድሜ ደረጃ ላይ ብትሆንም ቅሉ እንደእኩዮቿ ትምህርት ቤት ውሎ መምጣት እንደውሃ ይጠማት፤ እንደእንጀራ ይርባት ነበር። እኩዮቿ ጋር ጠዋት ማልዳ ወደ ትምህርት ቤት እየቦረቀች መሄድ፤ ከትምህርት ገበታዋ ውላ ከእኩዮቿ ጋር እየተጫወተች ወደ ቤቷ መመለስ በአይኗ ይዞር ነበር። ነገር ግን ትምህርት ቤት ለመግባት እና እንደኩዮቿ ለመማር ግን አልታደለችም።

"ዓለም ለአንዱ እንቁላል ለሌላው ኩስ ትጥላላች" እንዲሉ ሕይወት እንደእኩዮቿ ትምህርት ቤት ገብቶ መማሩ ቀርቶባት ክፉና ደጉን መለየት እስከምትችልበት ዕድሜ ድረስ የቤተሰቦቿን ፍቅር አግኝታ ማደግ አልቻለችም። የሰባት ዓመት ልጅ እያለች እናቷ ለቤት ሠራተኝነት አሳልፋ ለባዳ ሰጠቻት። እስከ 12 ዓመቷ ድረስም በተለያየ ሰው ቤት በቤት ሠራተኝነት ተቀጥራ በለጋ እድሜዋ የሰው ፊት እየገረፋት ያገኘችውን የወር ደሞወዝ ለቤተሰቦቿ ትረዳ ነበር። በሰው ቤት ተቀጥራ እየሠራች ክፉውንም ደጉንም ገና በጨቅላ እድሜዎ አይታለች።

በሰው ቤት ተቀጥራ እየሠራች እያለ የተዋወቀቻት አንድ ጓደኛዋ ጋር ተያይዘው የተሻለ እንጀራ ፍለጋ ወደ አማራ ክልል ደብረ ማርቆስ ከተማ ይኮበልላሉ። ሕይወት ከቤተሰቦቿ እርቃ ወንዝ ተሻግራ ወደ ደብረ ማርቆስ መሄዷን ለቤተሰቦቿ ሳትናገር እዛው ደብረ ማርቆስ ከተማ ቀበሌ 04 አንድ ግለሰብ ቤት ውስጥ በቤት ሠራተኝነት ጓድኛ አማቾቹ ይቀጠራሉ። በዚህ ግለሰብ ቤት ለአንድ ዓመት ያህል ከሠሩ በኋላ "ያልተገላበጠ ያራል እንዲሉ" ሌላ የተሻለ ሥራ ፍለጋ በህዲስ አለማየሁ በፍቅር እስከ መቃብር መጽሃፍ ላይ ጎልቶ ስሟ ወደ ምትታወቀው ማንኩሳ ከተማ ጎራ ይላሉ። ባልንጀሮቹ በማንኩሳ ከተማ በአንድ መለስተኛ ምግብ ቤት ውስጥ በምግብ አብሳይነት ተቀጥረው ለአራት ዓመት ያህል አብረው አንድ ቤት ሠርተዋል። ክፉውንም ደጉንም፣ ማግኘት ማጣቱንም በጋራ አሳልፈዋል። አንዱ ሲከፋው ሌላኛው እያጽናና፣ አንዱ ሲደሰት ሌላኛው ቢከፋውም አብሮ እየተደሰተ አራት ዓመት እንደአራት ቀን ሳይታወቃቸው እንደዋዛ አለፈ።

ጓደኝነታቸው ልክ "ወርቅ በእሳት እንደሚፈተነው" በችግርና ፈተና ውስጥ ጸንተው በፍቅር ዓመታትን አብረው አንድ ላይ ዘልቀዋል። ፍቅራቸው እየጠነከረ ከመምጣቱ የተነሳ ልክ እንደስጋ እህትማማች ይተያዩ ነበር። ከመዋደዳቸው የተነሳም ለምን አንድ ላይ ቤት ተከራይተን አንኖርም ይሉና ማንኩሳ ከተማን ተሰናብተው ወደ ፍኖተ ሰላም ከተማ አቀኑ። በዛም በጋራ መኖሪያ ቤት ተከራይተው አንድ ላይ መኖር ይጀምራሉ። በፍኖተ ሰላም ከተማም ምግብ ቤት ውስጥ ተቀጥረው እየሠሩ በሚያገኙት ገቢ ኑሯቸውን እየደጎሙ ለሁለት ዓመታት ክፉውና ደጉን አሳልፈዋል። ሁለት ዓመታትን በአንድ ጣሪያ ስር ሲኖሩ አንዱ እሳት ሲሆን አንዱ ውሃ፤ አንዱ ሲያጠፋ ሌላኛው መካሪ እየሆነ በፍቅር በደስታ ኖረዋል።

የሰው ልጅ በሆነ አጋጣሚ እንደተገናኘ ሁሉ በተቃራኒው መለያየቱ አይቀሬ ነው። ጓደኛ አማቾቹም በአንድ አጋጣሚ ተዋውቀው ጎደኝነት መስርተው ለዓመታት አብረው ኖረዋል። በአንጻሩ ደግሞ ለዓመታት ከዘለቀው ያማረና የሠመረ የጓደኝነትና የአብሮነት ጉዞ በኋላ ሊለያዩ ግድ ሆነ። በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ሲካሄድ በነበረው የህልውና ዘመቻ መንግሥት ህብረተሰቡ የአገር መከላከያ ሠራዊትን እንዲቀላቀል ያቀረበውን ጥሪ ተቀብላ ጎደኛዋ የአገር መከላከያ ሠራዊትን ተቀላቀለች። ሕይወትና ጓደኛዋ ዳግም ለአይነ ስጋ ያብቃን ብለው እየተላቀሱ ተለያዩ። ይሄኔ ሕይወት የሆዷን የምትነግረው፣ ችግሯን የምታዋየው ጓደኛዋን ከጎኗ ስታጣ የቀን ጨለማ ዋጣት። በፍኖተ ሰላም ከተማ ያለጓደኛዋ መኖር በምድረ በዳ እንደመኖር ሆነባት። በዚህም ሰኔ መጨረሻ 2014 ዓ.ም ፍኖተ ሠላም ከተማን ለቃ ወደ አዲስ አበባ አመራች።

### አዲስ አበባ ...

ሕይወት ከፍኖተ ሠላም ወደ አዲስ አበባ እንደመጣች ሳትወጣ ሳትወርድ ቀጥታ ሥራ እንድትገባ ደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገኝ አንድ ደላላ ሥራ ያመቻችላታል። በዚህም በአዲስ አበባ ከተማ ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ልዩ ቦታው አራብሣ ኮንዶሚንየም (የጋራ መኖሪያ ቤት) ብሎክ 151 4ኛ ፎቅ የቤት ቁጥር ቢ151/30 በሆነ የአቶ መላኩ ታረቀኝ እና የወይዘሮ መሰረት የሻነው መኖሪያ ቤት ውስጥ በቤት ሠራተኝነት ትቀጠራላች።

በዚህ የመኖሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥራ እየሠራች እያለ አሠሪዋ ወይዘሮ መሰረት አንዳንዴ ስትጠራት ሳትሰማት ቀርታ አቤት ሳትላት ስትቀር "ለምንድ ነው አቤት የማትይው" ከሚል ምክር አዘል ንግግር ባሻገር የከረረ ንግግር እንኳን ተነጋግረው አያውቁም። ጸብም ጭቅጭቅም በመካከላቸው አልነበረም። በተመሳሳይ ከአቶ መላኩ ጋርም ምንም አይነት ፀብም ሆነ የከፋ ንግግር ተነጋግርው አያውቁም። እንድትንከባከብ እና እንድትጠብቅ አደራ የተሰጣትን ህጻን ጊዮናዊት መላኩና ክርስቲና መላኩን ወላጆቻቸው ጠዋት ወደ ሥራ ወጥተው ማታ ወደ ቤት እስኪመለሱ ድረስ በሥነስርዓቱ ምግባቸውን አብልታ፣ ልብሳቸውን አልብሳ፣ ሲቆሽሹ አጥባ፣ ወዘተ. አደራዋን በአግባቡ ስትወጣ ቆይታለች። ከልጆቹ ጋር ካላት ቅርበት የተነሳ ሁለቱንም ህጻናት "ማሚ" ብላ ትጠራቸው ነበር። በነ አቶ መላኩና ወይዘሮ መሰረት ቤት ሁለት ወር ሊሞላት በጣት የሚቆጠሩ ቀናት እስኪቀራት ድረስ በሰላም ሥራዋን ሥትሠራ ቆይታለች።

### ነሃሴ 26 ቀን 2014 ዓ.ም

በዚህ ጥቁር ቀን በአዲስ አበባ ሰማይ ሥር የተሰማው አስደንጋጭ ዜና በአራቱም የአገሪቱ ማዕዘን የሚገኘውን ህዝብ በእንባ ያራጨ፣ በዓለም ላይ ከዚህ ቀደም ተሠርቷል ለማለት የሚከብድ ነበር።

ሕይወት አሠሪዋ አቶ መላኩ ታረቀኝ ባልትና ሱቅ እከፍትልሻለሁ ብሎ ቃል እንደገባላት ለፖሊስ በሰጠችው የእምነት ክደት ቃል ትናገራለች። እሷም ሱቅ ከፍታ ነግዳ ከራሷ አልፋ ቤተሰቦቿን ለመርዳት ቋመጠች። ነገ ላይ የተሻለ ኑሮ ለመኖር ጓጓች። ይህንን ህልሟ ሠምሮ ለማየት ካላት ጉጉት የተነሳ አሠሪዋ የገባላትን ቃል እንዲፈጽምላት በተደጋጋሚ ትጠይቀዋለች። እርሱም የገባውን ቃል ለመፈጸም አቅም አጥሮት ይሁን ወይም ልቡ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ ቃሉን ሳይፈጽምላት ቀናቶች ተቆጠሩ። እሷ ግን ጠዋት ሲወጣ ማታ ሲገባ "የገባህልኝን ቃል ፈጽምልኝ እንጂ" እያለች ትወተውተዋለች። ይህ ሥራ ክፈትልኝ የሚለው ውትወታ አቶ መላኩ ሲበዛበት "አይመለከተኝም" የሚል ምላሽ ይሰጣታል። እሷም ተስፋ ሳትቆርጥ "ሥራ እከፍትልሻለሁ" ብለህ ቃል ገብተህልኛል፤ ክፈትልኝ እያለች ነጋ ጠባ ትጠይቀዋለች። እሱም በምላሹ "አይመለከተኝም" የሚል ምላሽ ደጋግሞ ይሰጣታል።

"የገባልኝን ቃል አልፈጸመለኝም" በሚል ቂም በቀል አቶ መላኩን ለመበቀል ወሰነች። ሕይወት ይህንን ቂም በቀል በመያዝ አቶ መላኩን በምን እንደምትበቀለው ማሰላሰል፣ ማውጣት፣ ማውረድ ጀመረች። እሱን በተኛበት በቢላ ለመውጋት አሰበች፤ ነገር ግን ‹‹ልወጋው ወደ አጠገቡ ቢላ ይዤ ስጠጋ ቢነቃና ቢይዘኝ›› ብላ ፈራች። ይህ አያዋጣም ብላ አሰበች። አቶ መላኩን እርር ድብን የምታደርግበት አንድ ክፉ ሃሳብ በአዕምሮዋ መጣ። ይህንንም ቆርጣ ለመፈጸም ወሰነች።

በዚሁ ቀን እማወራዋ ወይዘሮ መሰረት ከሁሉም ቀድማ በጥዋት ተነስታ "ይሄን ይሄን ሥሪ፣ ይሄን ብሉ" ብላ በጥዋት ወደ ሥራ ወጣች። በተመሳሳይ አቶ መላኩ ባለቤቱ ወደ ሥራ እንደወጣች እሱም እግር በእግር ተከታትሏት ወደ ሥራ ወጣ። ይህኔ አቶ መላኩን ለመበቀል አስባ ለመፈጸም ያቀደችውን ክፉ ሃሳብ የሚያስቆማት አንዳች ነገር እንደሌለ ሕይወት አረጋገጠች።

እንድትንከባከብና እንድትጠበቅ አደራ የተሰጣትን ሁለት ህጻናት በመግደል አቶ መላኩን ለመበቀል ወሰነች። በግምት ከጠዋቱ 3: 30 ገደማ ህጻናቱ አገር ሰላም ብለው ወደ ተኙበት መኝታ ክፍላቸው ገባች። መጀመሪያ መስማትና መናገር የማትችል የሶስት ዓመት እድሜ ያላትን ህጻን ጊዮናዊት መላኩን በትራስ አፏንና አፍንጫዋን አፈነቻት። ህጻኗ ትንፋሽ አጥሯት አይኗ ፈጦ እይተንፈራገጠች ስታያት በሕይወት እንድትቀጠል ልቧ ባለመራራቱ አንገቷን በቢላ በማረድ ህይወቷ እንዲያልፍ አደረገች። ይህ ብቻ ቂም በቀሏን ስላላረካላት ቀጥላ እድሜዋ ሁለት ዓመት ያልሟላትን እንቦቃቅላ ህጻን ክርስቲና መላኩን በተኛችበት አፏንና አፍንጫዋን በማፈን ሕይወቷ እንዲያልፍ ታደርጋለች። ይህንን ድርጊት ከፈጸመች በኋላ ለልጆቹ አባት ደውላ "ቤት አይደለሁም፤ ወደ ፖሊስ ጣቢያ እየሄድሁ ነው" ብላ ትነግረዋለች። እሱም መልሶ መላልሶ ሲደውልላት ስልኩን ዘጋችበት። ወደ ቤት በሮ ሲሄድ ልጆቹን ዳግም ላያገኛቸው እስከወዲያኛው አሸልበዋል።

### የፖሊስ ምርመራ

ሕይወት እንድትንከባከብና እንድትጠብቅ አደራ የተሰጣትን እህታማቾቹን በነውረኝነትና ፍጹም ጨካኝነት በሚያሳይ ሁኔታ ሕይወታቸው እንዲያልፍ ካደረገች በኋላ ቀጥታ ፖሊስ ጣቢያ ሂዳ "ሰው ገድያለሁ" ብላ እጇን ሰጠች። ለፖሊስም "አባታቸው ቢያናድደኝም፣ ምንም የማያውቁትን ህጻናቱን በመግደሌ ተፀጽቻለሁ፣ ምን ብናደድም ህጻናቱን መግደል አልነበረብኝም፣ በሚቀርብብኝ የሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ነኝ፣ ተጸጽቻለሁ" ብላ የእምነት ክህደታ ቃሏን ሰጥታለች። ፖሊስም የተከሳሽን የእምነት ክደት ቃል እና ማስረጃዎችን አጠናቅሮ ክሱን ለዐቃቤ ሕግ አሳልፏል።

### ውሳኔ

ህዳር 26 ቀን 2015 ዓ.ም በችሎቱ የተሰየመው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት በተከሳሽ ሕይወት መኮንን ኃይሉ ክስ የመጨረሻውን ውሳኔ ለመስጠት ተሰይሟል። ፍርድ ቤቱም በዚህ ቀን በዋለው ችሎት ተከሳሽ በሞት እንድትቀጣ ሲል ውሳኔ አሳልፏል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

# ጉዳይ ገዳይ ምን ሊጋብዘኝ ይሆን?

በሪሁ ኣረጋ

ከጠዋቱ 1:30 አካባቢ ይሆናል። ከሰርቪስ ወርጄ በፈጣን እርምጃ ወደ ቢሮ ልገባ እየገሰገስኩ ነበር። ከኋላየ ‹‹እህት›› የሚል ድምፅ ሰማሁ፣ ጥሪው እኔን የሚመለከት ስላልመሰለኝ ወደኋላ ሳልዞር መራመዴን ቀጠልኩኝ። ሁለተኛ ሲጠራኝ ግን እሱም ከኔ እኩል እየተራመደ ከጎኔ ሆኖ ነበር። ደግሞ እህት ሲለኝ እኔም አቤት ምን ነበር? አልኩት ፈጣን እርምጃየን ሳልገታ።

‹‹አንዴ ስሚኝማ እባክሽን የሆነ ነገር ላስቸግርሽ›› አለኝ። እኔም ለአፍታ እርምጃየን ዝግ እድርጌ ርቀቴን ጠብቄ በመቆም በድጋሚ ምን ነበር? አልኩት። በእጁ ስልክ ይዟል፣ ጠቅ ጠቅ እያልን የምንጠራት ዓይነት ስልክ፣ ‹‹እባክሽን የስራ ውድድር ነበረኝና ወደ ሲኤምሲ ሄጄ መፈተን አለብኝ እዛ በግማሽ ሰዓት መግባት ይኖርብኛል ካልሆነ በቃ ፈተናው ያመልጠኛል›› እያለ ብዙ ዝርዝር ነገር ያወራ ጀመር።

ይንተባተባል መረጋጋት አይታይበትም። የስራ ፈተና ልፈተን ነው ሲለኝ (ለወራትም ቢሆን እኔም ስራ አጥ ነበርኩኝና) በመሃል ሃሳቡን አቋርጬ ታዲያ እኔ ምን ልርዳህ አልኩት የምችለውን ልረዳው በማሰብ፡፡ ልክ ቦርሳየ ውስጥ እጄን ስሰድ አርባ ብር የሚሆን ዝርዝር አገኘሁና ይህ ሲኤምሲ ያደርስሃል? ብየ ሰጠሁት። መናገር አላቆመም እስካሁን እያወራ ነው፣ አሁንም ይቅበዘበዛል፣ እኔም እንዳይረፍድበት ውድድሩ እንዳያመልጠው ይሆናል እንዲህ የሚሆነው ብየ ልረዳው ፈለግኩኝ።

‹‹ይበቃኛል፣ በጣም ነው የማመሰግንሽ፣ እውነት ጥሩ ሰው ነሽ፣ እግዚአብሔር ይስጥልኝ›› ሌላም ሌላም አለ። እኔም ምንም አይደል መልካም እድል ብየ ትቼው ልሄድ ስሰናዳ ‹‹ ጥሩ ሰው ስለሆንሽ ላመሰግንሽም ካለፍኩኝ ደውየ መልካም ዜና እንድነግርሽ፣ አሁን ስለቸኮልሽ ምንም አልልሽም፣ ስልክሽን አትሰጪኝም? አለኝ፡፡

እኔም እሺ ብየ ከኋላየ ትቼው ወደ ፊት እየተራመድኩ 09 21....... ብየ ነገርኩት፣ ግን በጣም ፈጥኜ ስለነበር ቁጥሮቹን የጠራኋቸው ይይዘዋል ብየ አስቤ አልነበረም፡፡ እሱ ግን ካሰብኩት በላይ ፈጣን ነበርና ይዞታል። በቅፅበት ደወለ፣ ስልኬ ቦርሳየ ውስጥ ሆኖ ይነዝረኛል። ተገረምኩ ስልኬን ከቦርሳየ አውጥቼ አላየሁም። ቢሮየ ገብቼ አረፍ እንዳልኩ የተደወለውን ስልክ ሳየው እድሜ ለቴክኖሎጂ የደወለልን ሰው ማን እንደሆነ ከኛ ቀድሞ የሚነግረንን (true caller) አበበ ለማ (ስሙ የተቀየረ) ብሎ አመጣልኝ። እኔም በውስጤ መልካም እድል ይሁንልህ አበበ ብየ ስልኬን መልሼ በማስቀመጥ ወደ ስራ ገባሁ።

ወደ ከሰዓት አካባቢ የማላውቀው ስልክ ይደወላል፣ አሁንም እድሜ ለtrue caller ስሙን ማን ቢለው ጥሩ ነው?! "ጉዳይ ገዳይ" በሰዓቱ ምንም አልገባኝም ነበር፣ አንስቼም አላወራሁትም፣ አበበ ይሆናል ብየ እርግጠኛ ስላልነበርኩኝ በዝምታ አለፍኩት። ምን አይነት ስም ነው? ብየ ራሴን በመጠየቅ ዝም አልኩኝ፡፡

ብዙ ግዜ አዲስ ስልክ አላነሳም። ማታ ወደ 12:30 አካባቢ ቤት ገብቼ አገር አማን ብየ ገና አረፍ ሳልል እንደገና ሌላ አዲስ ስልክ ተደወለ። የአሁኑ ግን እንቆቅልሹን በደምብ የሚፈታልኝ ስም ነበር የመጣው "ሌባው" ይላል። ደነገጥኩኝ፣ አነሳሁና አቤት አልኩኝ። ‹‹እንደምን ዋልሽ›› ይላል ደዋዩ፣ የማውቀው ድምፅ ነው። ጥዋት 1:30 ሰምቼዋለሁ። እግዚአብሔር ይመስገን እንደምን ዋልክ፣ ‹‹የጥዋቱ ልጅ ነኝ›› አለ፣ አሁንም እንደ ጥዋቱ ንግግሩ ፋታ አይሰጥም። አወኩህ አልኩት። ‹‹ላመሰግንሽ ነው፣ ፈተናውን እኮ አለፍኩ፣ እድሜ ላንቺ...›› ምናምን እያለ ቀባጠረ፡፡

እንኳን ደስ ያለህ ደስ ይላል አልኩት። ‹‹ጥዋትም ቀንም ደውየ ነበር አታነሺም›› ሲለኝ፣ ጥሩ ማረጋገጫ ነው አልኩኝ በውስጤ፡፡ እና በቃ ደስ ብሎኛል ስላለፍክ አንተም እንኳን ደስ ያለህ ግን ደግመህ እንዳትደውል አልኩት። ‹‹እንዴ ምነው እኔማ ለዚ ጥሩነትሽ እራት ልጋብዝሽ ነበር እኮ የፈለኩት›› አለ። እራት? አልኩኝ አሁንም በውስጤ።

አይ ይቅርብኝ አመሰግናለሁ ስለው ለመቆጣት ቃጣው፣ ‹‹አሁን እኮ ብር አለኝ ችግር የለውም፣ የሆነ ጓደኛየ ከውጭ መጥቶ ብዙ ብር ሰጠኝ›› ሲለኝ... ደግሞ የማንን የፈረደበት ኪስ አጥበህ ይሆን? አልኩኝ በውስጤ። በቃ አልፈልግም አልኩህ አይደል እንዴ፣ ለምንድነው የምታስገድደኝ? ብየ ኮስተር አልኩ፡፡ እሱ ግን በቀላሉ የሚፋታ አልሆነም፡፡ ይሄኔ እርሙን ያውጣ ብየ "ማነህ ጉዳይ ገዳይ በቃ አልፈልግም አልኩህ እኮ" ስለው ይበልጥ ተንተባተበ ‹‹ማን ነው ጉዳይ ገዳይ ይባላል ያለሽ›› ሲል በንዴት መጠፉ ያስታውቅ ነበር፡፡

ማንም አልነገረኝም ግን እርግጠኛ ነኝ ብዙ ሰው በዚ ስምህ ያውቀሃል አልኩት። እቅዱን ገና ሳይጀምር ስለከሸፈበት ለእኔ የማይሰማ ነገር ከራሱ ጋር አጉተምትሞ ስልኩን ዘጋሁት። እኔም ፈጣሪየን ከዚህ ስለጠበቀኝ እያመሰገንኩ ለመረጋጋት ሞከርኩኝ።

እራት ሊጋብዘኝ ነው ወይስ የያዝኩትን በሙሉ ነጥቆ ራሱን እና መሰሎቹን ሊጋብዝ? እኔም ለታክሲ እንኳን ሳይቀረኝ ባዶ እጄን ይዤ ቤቴ እንድመለስ?።

ይህን ገጠመኜን ላወጋችሁ የተነሳሁት ካለምክንያት አይደለም፡፡ በአሁኑ ወቅት በከተማችን አዲስ አበባ ልክ እንደ ጉዳይ ገዳይ ብዙ በሌብነት የተሰማሩ ሰዎች እንዳሉ የማይካድ እውነታ ነው።

ሰዎች ከወር ደመወዛቸው ቆጥበው በዚህ ሳምንት ውጪ አውጥተን ሻይ ቡና ማለት ይቅርብን ብለው የገዙትን ስልክ፣ ሰዓት፣ ጌጣጌጥ እና የመሳሰሉት ነገሮችን ነጥቀው እዚህ ግባ በማይባል ዋጋ የሚሸጡ በርክተዋል፡ ፡ የዘመኑን ሌቦች በምንም መለየት አይቻልም። ማንም በማይጠረጥረው መንገድ ለፍቶ ጥሮ ግሮ የተለወጠ የስራ ሰው መስለው ነው ለሌብነት የሚሰማሩት፡፡

ሌብነት ብዙዎችን ያማረረና ብዙ ነገር ሊያሳጣ የሚችል ፀያፍ ተግባር ነው። ከትንሽ እስከ ትልቅ ደረጃ የሚፈፀም የሌብነት ተግባር ማህበረሰብ ውስጥ መተማመንን እስከማጥፋት የደረሰ አደጋ አለው፡፡ የእውነት ተቸግሮ እርዳታ የሚሻን ሰው ጭምር በጥርጣሬ አይን እንዲታይ ያደርጋል፡፡

ሌቦች ብራችንን ወይም ስልካችንን ብቻ አይደለም እየሰረቁብን ያሉት፣ ሰብአዊነታችንን ጭምር ነው፡ ፡ በትክክል እርዳታ ለሚፈልጉ ወገኖቻችን እንዳንራራ አድርገዉናል። እርዳታ ስንጠየቅ ኸረ ማንን ልትበላ በፍፁም አላደርገውም ብለን መንገድ ቀይረን እንድንሄድ አድርገውናልና።

# ዓለም አቀፍ



## ታይታኒክን ስመመልከት ወደ ጥልቁ ባሕር የሄዱት ሕይወታቸው አለፈ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የታይታኒክ መርከብ ቅሪትን ለመመልከት ወደ ጥልቁ ባሕር ከሄዱ በኋላ መድረሻቸው ጠፍቶ ሲፈለጉ የነበሩት አምስት ሰዎች ሕይወታቸው ማለፉ ተገለጸ።

ዕድሜያቸው ከ19-77 የሚገኙት አምስቱ ወንዶች ከረዥም ዓመታት በፊት የሰጠመችውን ታይታኒክ መርከብ ለመመልከት ነበር እሁድ ዕለት ወደ ጥልቁ ባሕር ጉዞ ካደረጉ በኋላ ግንኙነታቸው የተቋረጠው።

የጠፉትን ሰዎች ለማግኘት ከተለያዩ አገራት የተሰባሰቡ ባለሙያዎች ፍለጋ ሲያደርጉ ቆይተው ትናንት የሰዎቹ ሕይወት ማለፉን ከፍያ እየተቀበለ ወደ ጥልቁ ባሕር ጉዞ የሚያደርገው ኩባንያ አስታውቋል።

ግለሰቦቹን እንዲፈልግ ወደ ባሕሩ የተላከው ሮቦት ባሕር ሰርጓጅ ሰዎቹ ሲጓዙበት የነበረችው ሰርጓጅ መርከብ ስብርባሪን ከታይታኒክ መርከብ 480 ሜትር ርቆ አግኝቷል።

ግለቦቹ ሳይሞቱ አይቀሩም የተባለው ጉዞ ከጀመሩ በሰዓታት ልዩነት ሰርጓጅ መርከቧ ላይ ባጋጠመ ፍንዳታ ሳይሆን አይቀርም እየተባለ ነው። የአሜሪካ የባሕር ድንበር ጥበቃ ዘብ ግን እስካሁን ፍንዳታው የት እና መቼ እንዳጋጠመ በትክክል መግለጽ አይቻለኝም ብሏል።

ይሁን እንጂ አራት ኪሎ ሜትር ጥልቀት ካለው የባሕር ወለል ከታይታኒክ መርከብ 500 ሜትር ገደማ ርቆ የሰርጓጅ መርከቧ ስብርባሪ ተገኝቷል።

ሟቾቹ ሰርጓጅ መርከቧን የሚያስተዳድረው ኩባንያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ስቶክቶን ራሽ፣ እንግሊዛዊው ብሊየነር ሃሚሽ ሃርዲንግ፣ ፈረንሳይዊ ባሕር ጠላቂ ፖል-ሄነሪ ናርጌሎት እንዲሁም እንግሊዛዊው የንግድ ሰው ሻህዛዳ ዳውድ ከልጃቸው ሱሌይማን ዳውድ ጋር የቱሪስት ሰርጓጅ መርከቧን ተሳፍረው ነበር። ግለሰቦቹ ሕይወታቸው አልፏል ተብሎ ይደምደም እንጂ አስክሬናቸው አልተገኘም።

የአሜሪካ የባሕር ድንበር ጥበቃ ኃላፊዎች በባሕሩ ላይ ባለው ከባድ የአየር ጸባይ ምክንያት የሰዎቹን አስክሬን እናገኛለን ብለን መናገር አይቻለንም ብሏል።

የግለሰቦቹን ሞት ተከትሎ መሪዎች እና ታዋቂ ግለሰቦች የተሰማቸውን ሐዘን እየገለጹ ይገኛሉ። ዋይት ሃውስ የሟች ቤተሰቦችን አጽናንቷል። ዋይት ሃውስ ባለፉት ቀናት የቤተሰብ አባላት የቤተሰቦቻቸው እጣ ምን ሊሆን እንደሚችል ሳያውቁ ከባድ ውጥረት ውስጥ መቆየታቸውን ገልጾ መጽናናትን ተመኝቷል።

የዩናይትድ ኪንግደም መንግሥት ደግሞ በአደጋው ሕይወታቸውን ያጡ ሰዎች ቤተሰቦችን በዚህ ፈታኝ ግዜ እደግፋለሁ ብላለች።

የዩኬ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጄምስ ክሌቨርሊ መንግሥት ለእንግሊዛውያን ቤተሰቦች ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ገልጸው በጸሎታችን እናስባቸዋለን ብለዋል።

እአአ በ1912 በሰሜን አትላንቲክ ባሕር የሰጠመችውን ዝነኛዋን ታይታኒክን ለመመልከት 4 ኪሎ ሜትር ገደማ ወደ ጥልቁ ባሕር ለመጓዝ ኦሽን ጌት የተባለው ኩባንያ እስከ 250 ሺህ የአሜሪካ ዶላር እንደሚያስከፍል ተገልጿል።

## ፌስቡክና ኢንስታግራም በካናዳ በገጻቸው ላይ የሚቀርቡ ዜናዎችን ሊገድቡ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ፌስቡክና ኢንስታግራምን የሚያስተዳድረው ሜታ በካናዳ በማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮቹ ላይ የሚቀርቡ ዜናዎች ላይ ገደብ ሊጥል መሆኑን አስታወቀ። ድርጅቱ ይህን ያለው የካናዳ ምክር ቤት አወዛጋቢ የሆነውን የኦንላይ ዜና ረቂቅ ሕግን ካጸደቀ በኋላ ነው።

ረቂቅ ሕጉ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮቹ በገጻቸው ላይ ለሚታተሙ ይዘቶች ለዜና አሳታሚዎች ካሳ እንዲከፍሉ ያስገድዳል። ሜታ እና ጉግል ለተወሰኑ ካናዳውያን ዜና የሚገድብ ሙከራ እያደረጉ ነው።

እንደ አውሮፓውያኑ 2021 በተመሳሳይ ሕግ ምክንያት አውስትራሊያውያን ተጠቃሚዎችም በፌስቡክ ላይ ዜናዎችን እንዳያዩ እና እንዳያጋሩ ተገድበው ነበር።

የካናዳ ምክር ቤቱ ሐሙስ ዕለት ያሳለፈው የኦንላይን ዜና ሕግ እንደ ሜታ እና ጉግል ያሉ መድረኮች ለዜና ይዘቶች ከዜና ድርጅቶች ጋር የንግድ ስምምነት እንዲያደርጉ እና እንዲከፍሉ ያስገድዳል።

ሜታ ሕጉን "የማሕበራዊ ሚዲያ መድረኮቹን አሠራር እውነታ ችላ ያለ መሠረታዊ ጉድለት ያለበት" ብሎታል።

ሆኖም ሕጉ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ፌስቡክ እና ኢንስታግራም በካናዳ ላሉ ተጠቃሚዎቹ ዜና ማቅረቡን እንደሚያቆም ድርጅቱ ሐሙስ እለት አስታውቋል።

የሜታ ቃል አቀባይ " እኛ ላለጠፍነው የዜና ሊንኮች እና ይዘቶች እንድንከፍል የሚጠይቀው እንዲሁም በርካታ ደንበኞች የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮቹን የሚጠቀሙበት ምክንያት ያልሆነው የሕግ ማዕቀፍ ዘላቂነት የሌለውና የማይሰራ ነው " ሲል ለሮይተርስ የዜና ወኪል ተናግረዋል።

ድርጅቱ ጨምሮም በካናዳ ዜናን በተመለከተ የተደረገው ለውጥ በሌሎች አገልግሎቶቹ ላይ ተፅዕኖ አይፈጥርም ብሏል።

ጉግልም በበኩሉ ሕጉ አሁን ላይ ባለው አግባብ "የማይሠራ" ያለው ሲሆን ሌላ አማራጭ ለመፈለግ ከመንግሥት ጋር እየሠራ እንደሆነ ገልጿል።

የፌደራል መንግሥት በበኩሉ የኦንላይን ዜና ሕጉ ፣ ለካናዳውያን የዲጂታል ዜና ገበያ ያለውን ፍትሃዊነት የሚያሳድግ ነው፤ እየተንገዳገዱ ያሉት የዜና ድርጅቶች በማኅበራዊ መድረኮቹ ለሚያቀርቧቸው ዜናዎች እና ሊንኮች ፍትሃዊ የሆነ ካሳ እንዲያገኙም የሚፈቅድ ነው ብሏል።

ገለልተኛ የሆነው የምክር ቤቱ በጀት ተመልካች ትንታኔ የዜና ንግዱ ከዲጂታል መድረኮች በዓመት 250 ሚሊየን ዶላር ሊያገኝ እንደሚችል ገምቷል።

በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ የካናዳ የቅርስ ሚኒስትር ፓብሎ ሮዲሪጉዝ፣በቴክኖሎጂ መድረኮቹ የሚካሄደው ሙከራ " ተቀባይነት የሌለው" እና "ስጋት" መሆናቸውን ለሮይተርስ ተናግረዋል።

በአውስትራሊያ ፌስቡክ ከመንግሥት ጋር ንግግር ካደረገ በኋላ በተደረገ የሕግ ማሻሻያ ለተጠቃሚዎቹ የዜና ይዘቶችን እንደገና ማቅረብ ጀምሯል።

ሐሙስ ዕለት የሚኒስትር ሮደሪጊዝ ቢሮ ከጉግል እና ከፌስቡክ ጋር በዚህ ሳምንት መነጋገሩን ገልጾ ፣ ለተጨማሪ ውይይት ለማድረግ ማቀዱን ገልጿል። ይሁን እንጂ መንግሥት ሕጉ ተግባራዊ እንዲሆን እንደሚያደርግ ገልጿል።

"የዜና መድረኮቹን በተመለከተ መንግሥት ለካናዳውያን ካልቆመ ማን ሊቆም ይችላል?" ሲል በመግለጫው አስታውቋል።

የሚዲያ ኢንደስትሪ ቡድን በበኩሉ ሕጉ መጽደቁ ያለውን የዜና ገበያ ፍትሃዊ ለማድረግ አንድ እርምጃ ነው ብሎታል።

የሚዲያ ኢንደስትሪ ግሩፕ ሆነው የኒውስ ሚዲያ ካናዳ ፕሬዚደንት እና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፖል ዲጋን በመግለጫቸው " ካናዳውያን እውነተኛ ጋዜጠኝነትን ከትክክለኛ ጋዜጠኞች ማግኘት ይፈልጋሉ። ለዲሞክራሲያችንም ወሳኝ ነው፣ ነገር ግን ገንዘብ እያስከፈለ ነው።" ብለዋል።

የኦንላይን ዜና ሕጉ በስድስት ወራት ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል ተብሎም ይጠበቃል።

## መጋቢ አዕምሮ

# ራስህ ላይ ስራ!



**አስናቀ ፀጋዬ**

‹‹ጠንክረህ ከሰራህ ጥሩ ገቢ ስለምታገኝ ቅንጡ ሆቴል ሄደህ ልትዝናና ትችላለህ። ከስራህ በተጨማሪ ራስህ ላይ ጠንክረህ ከሰራህ ግን ያን ቅንጡ ሆቴል ትገዛዋለህ›› ይላል በአነቃቂ ንግግሮቹ የሚታወቀው እውቁ አሜሪካዊ ስራ ፈጣሪና ደራሲ ጂም ሮን። ለመሆኑ ራስ ላይ መስራት ምን ማለት ነው? ራሳቸው ላይ የሰሩ ሰዎችስ በእንዴት ያለ ሁኔታ ነው በህይወታቸው አስደንጋጭ ለውጥ ሊያመጡ የቻሉት?

አብዛኞቻችን ጠንክረን ስራችንን እንሰራለን። ግን አላደግንም። ባለንበት ቆመናል። ለብዙ ነገር ጊዜ እንሰጣለን። ለመዝናናት፣ ለመተኛት፣ ከሰዎች ጋር ለማሳለፍ፣ ስራ ለመስራት .... ወዘተ ጊዜ አለን። እራሳችን ላይ ለመስራት ግን ለራሳችን ግዜ አልሰጠንም። እንዴት ነው ታዲያ ራሳችን ላይ መስራት የምንችለው? እንዴትስ ነው የምንቀየረው? ለሚሉት ጥያቄዎች ቀጣዩ ፅሁፍ መልስ አለው።

ወጣቱ ጠቢቡን ሰው ጠየቀ። ‹‹በዚህ ዓለም ትልቁ ሸክም ምንድን ነው›› ብሎ። ጠቢቡም ሰው ምንም ሳያመነቱ መለሱ። ‹‹የኔ ልጅ የዚህ ዓለም ትልቁ ሸክምማ ምንም አለመሸከም ነው›› ብለው። ስለዚህ አንተም ካልዘራህ አታጭድም። ማንም አይመጣም። ማንም አይመጣም። ማንም ከእንቅልፍህ ቀስቅሶ ከአልጋህ አስነስቶ ጥሩ ደሞዝ ያለው ስራ እንካ ብሎ አይሰጥህም። ማንም ከህይወትህ ላይ ወስዶ ላንተ የምትሆን ሚስት፣ ላንተ የምትሆን ፍቅረኛ አግኝቼልሃለው ብሎ አያገናኝህም። ራስህ መነሳት አለብህ። ማንም አይመጣም። ማንንም አትጠብቅ። ያንተን ህይወት ማንም አይቀይረውም።

አንዳንድ ሰው ከኮሌጅ ከተመረቀ በኋላ ራሱን ማሳደግ አቁሟል። ደሞዝተኛ ነው። የስራ ልምዱ ሲጨምር ብቻ ትንሽ ትንሽ ብቻ የሚያድገውን ደሞዝ እየበላ ይኖራል። ይሄኔ እኮ የሆነ ኮርስ ቢማር፣ የሆነ ስልጠና ቢወስድ፣ ከእርሱ ከሚሻሉ ሰዎች ጋር ቢውል፣ ራሱን ቢያሳድግ ደሞዙን እጥፍ ሊያደርገው ይችላል። ግን ይህንን አያስብም። እዛው ቁጭ ብሎ ‹‹ይሄ መስሪያ ቤት በቃ! ጉልበቴን በዘበዘው›› ይላል።

ወዳጄ! ዋጋህ መጨመር አለበት። በእውቀትና ብስለትህ እንደዛፍ አስከምትችለው ድረስ ማደግ አለብህ። ከሌሎች የምጠብቅበት ዘመን ማብቃት አለበት። ለራስህ ያለሽው አንተ ነህ። ኃላፊነቱን ውሰድና ራስህ ላይ ስራ። መቃብርህ ላይ ምን እንዲነበብ ነው የምትፈልገው? ‹‹በስነ ምግባሩ የተመሰገነ፣ ለሚስቱ ታማኝ፣ ሶስት ልጆች ያሉት በዚህ ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ›› ብቻ መባል ነው የምትፈልገው? ወይስ ‹‹ይህን ሰርቶ፣ ይህን አሳክቶ፣ እንዲህ አድርጎ፣ እንዲህ ከፍቶ›› መባል ነው የምትፈልገው? አንተ ስትሄድ ስላንተ የሚያወሩት ቤተሰቦችህ ብቻ ናቸው? ወይስ የሚያውቁህ ሁሉ?

ጥንካሬህን፤ ማንነትህን ይመሰክራሉ። ስለዚህ ምርጫው ያንተ ነው። ራስህ ላይ መስራት ያለብህም ለዛ ነው። ስራህ ምንም ሊሆን ይችላል። ግን አንተ ስትጎድል መታወቅ አለበት። አንተ ስትለቅ ወየው! እሱን የሚተካ ከየት ነው የምናመጣው? መባል አለበት። አንተ ከሌለህ ብዙ ጉድለቶች መታየት አለባቸው። ያለበለዚያ ‹‹እዚህ ነበር፤ ተቀጥሮ ነበር ለቀቀ›› የምትባል ሰው መሆን የለብህም።

ድርጅት የሚከፍልህ እውቀትህን፣ ልምድህን ብሎ ነው። ያንተ እውቀት በፍጥነት ካደገ ዋጋህ ውድ ይሆናል። ተፈላጊ ትሆናለህ። አንተን የሚያክል አስተናጋጅ፣ ምግብ አብሳይ፣ ማኔጀር፣ ሶፍትዌር ኢንጂነር ወይ ዶክተር ባይኖር አስብለሃል? ሞያው አይደለም ወሳኙ ያንተ ጉብዝናና ያንተ ጥረት ነው። ልዩነት ፈጣሪው የተሰማራህበት ቢዝነስ አይደለም። ቢዝነሱን የምትሰራበት መንገድ ነው። ሙያው አይደለም ወሳኙ። ለሙያው የምትከፍለው ዋጋ ነው። ጠንክሮ መስራት ወይ መፀፀት ማለት እዚህ ጋር ነው።

ደራሲ ስብሃት ገብረእግዝአብሄር ‹‹አገርህ ላይ አብዮት ባታስነሳ ራስህ ላይ ታላቅ አብዮት አስነስተህ የምትፈልገውን ነገር ሁሉ መቀየር ትችላለህ›› ይለናል። ራስህ ላይ አብዮት የምታስነሳው ከሰዎች መጠበቅ አቁመህ ትኩረትህን ህልምህ ላይ፣ የነገ መድረሻህ ላይ ካደረክ ብቻ ነው። ሰዎች እንዲያበረቱህ የምትጠብቅ ከሆነ ዝም ያሉህ ቀን ታቆማለህ። ስለዚህ ወዳጄ! ዝም ብለህ ራስህ ላይ ስራ። ስኬትህ ራሱ ጮሆ ማንነትህን ይናገራል።

በአውሮፓ የዱባና የቲማቲም ተክሎች በአጭር ግዜ ያድጋሉ። ለረጅም ቀናትና ሳምንታት ፍሬያማ ሆነው ብዙ ምርት ይሰጣሉ። የበረዶ ግዜ ሲያልፍ ግን ፍሬያቸው ረግፎ ይሞታሉ። በተቃራኒው ዛፎች ለማደግ ብዙ ወራትንና ዓመታትን ይፈጃሉ። ካደጉ በኋላ ግን ከባዱን ግዜ በኩራት ያልፉታል። አየህ! በፍጥነት ወደላይ ከወጣህ በፍጥነት ቁልቁል ትወርዳለህ። ዛፎቹን ረጅም ጊዜ እንዲቆዩ ያደረጋቸው በዓመታት መሬት ውስጥ የዘረጉት ስር ነው። አንተም ለጊዜያዊ ስሜትህ ከጓጓህ ራስህ ላይ በደምብ ስራ። አለበለዚያ ስኬት የመሰለህ ነገር ጊዜያዊ ስለሆነ እንደንፋስ ሽው ብሎ ያመልጥሃል።

አንዳንድ ሰው ሁሌ ሩጫ ላይ ነው። ጥድፊያ ላይ ነው። ኑሮው ግን አልተቀየረም። ገቢው አልጨመረም። አየህ! ንብም ዝምብም እኩል ይሰራሉ። ንብ ማር ታመርታለች። ዝምብ ደግሞ ማር ታበላሻለች። ተመሳሳይ ነገር እያደረክ የተለየ ውጤት አትጠብቅ። ለምትወደው ነገር ዋጋ መክፈል አለብህ። ጠንካራ ሰው ለራሱ ብቻ አይኖርም። አንተን የሚጠብቁ ብዙ ሰዎች አሉ። ላንተማ አንድ እንጀራና አንድ ክፍል ቤት በቂ ነው። እሱን ለማሳካት ደግሞ ትልቅ ዋጋ መክፈል አይጠበቅብህም። ትልቅ ነገር የሚፈልግ ግን ትንሹን ስራ ለነገ አያሳድርም።

ከአልጋህ ተነስ! ስፖርት ስራ! ሻወር ውሰድ! መፅሃፉን ግለጥ! ወደ ስራ ግባ! ወዳጄ የዛሬ ትንሹ ጥረትህ ተጠራቅሞ ነው ነገ ታላቅ የሚያደርግህ። አንድ የተከበረ የአገር መሪ እንዲህ ብሎ ነበር፡- ‹‹ዛፍ ለመቁረጥ ስድስት ደቂቃ ብቻ ቢሰጠኝ አራቱን ደቂቃ መጥረቢያውን እየሳልኩ አጠፋዋለው›› አንተም ጊዜ ማጥፋት ያለብህ ራስህን ለመቀየር ነው እንጂ ስራው፣ ገንዘቡ፣ የፍቅር ግንኙነቱን ማሳመር በጣም ቀላል ነው።

ወዳጄ! መጀመሪያ አንተ በአመለካከትህና በስብእናህ ከፍ በል እንጂ ሌላውን መቀየር ማገዶ አይፈጅም። ትናንሾቹን ልማዶችህን አትናቃቸው። ጠዋት መነሳቱን፣ ለአስር ደቂቃም ቢሆን ስፖርት መስራቱን፣ ለጥቂት ደቂቃዎችም ቢሆን ማንበቡን፣ ፈጣሪህን ማመስገኑን አትናቀው። ችግር የለውም አትበል። ዛሬ አላደረኩትም ስለዚህ ነገ አደርገዋለሁ አትበል። ትናንሾቹ ልማዶችህ ናቸው አንተን ቀጥ አድርገው የያዙህ።

እንደው ከእንስሳት መካከል አንድ ምሳሌ ስጠኝ ብልህ ብዙ እንስሳዎችን ልትጠራ ትችላለህ። የትኛውም ሰው ግን ከፍጥረታት ሁሉ አስታውሶ ‹‹ትል›› አይልም። ትል ግን የምድራችን ወሳኝ እንስሳ ነው። የሰው ልጅ ባይኖር ምድር ትቀጥላለች። ዛፎች ያድጋሉ። እንስሳትም በነፃነት ይኖራሉ። ሆኖም ትል ባይኖር የፍጥረት ዓለም እንደዚህ አይቀጥልም። ዛፎች ይደርቃሉ። እንስሳት ይጠፋሉ። ምክንያቱም ትል የለም ማለት አፈር የለም ማለት ነው። ስለዚህ ትልን የሚያህል የምድራችን የአፈር መሃንዲስ የለም።

አየህ! ትንሽ ብለህ የምትንቃቸው ነገሮች በህይወትህ በጣም ወሳኝ ናቸው። ለዛ ነው ለትናንሾቹ ልማዶችህ መታመን ያለብህ። ትልቁ ቦታ ላይ የሚያስቀምጥህ ዛሬ በጠዋት መነሳትህ ነው። ዛሬ የአስር ደቂቃ ስፖርት መስራትህ ነው። ዛሬ ራስህ ላይ የሆነ ልምምድ ማድረግህ ነው።

በዚህ ዓለም ሶስት አይነት ሰዎች አሉ። የመጀመሪያዎቹ ነገሮችን በጥረታቸው የሚያሳኩ፣ ሁለተኛዎቹ ነገሮች ሲሳኩና ሲበላሹ ቆመው የሚመለከቱና ሶስተኛዎቹ ጭራሽ ምን እየሆነ እንዳለ የማያውቁ ናቸው። አንተ የቱ ጋር ነህ? ህይወት ምርጫ ነው። ከሶስቱ ሰዎች አንዱን የመሆን መብት አለህ። ስኬት እንደኪራይ ቤት ነው። ገዝተኸው ቁጭ ማለት አትችልም። ስለዚህ ሁሌም ትጥራለህ። ጠዋት ትነሳለህ፤ ታነባለህ፤ ትሰራለህ፤ ትማራለህ። በቃ! ለአላማህ እስከጠቀመህ ድረስ ዋጋ ትከፍላለህ።

ይህንማድረግቀላልአይደለም።ቀላልቢሆንማሁሉም ያደርገው ነበር። በህፃንነታችን አብረን ከተማርናቸው ልጆች መካከል አሁን አስታውሱ ብንባል ሁለት አይነት ሰዎችን ልናስታውስ እንችላለን። የመጀመሪዎቹ በጣም ጎበዞች፣ ሰቃዮች፣ የሚጨበጨብላቸውና አስተማሪ የሚያደንቃቸው ናቸው። ሁለተኛዎቹ ደግሞ በጣም ረባሾች፣ ተደባዳቢዎች፣ ሁሌ የሚገረፉ ናቸው። መካከል ላይ ያሉትን ልጆች ግን አናስታውሳቸውም። ማንም ትዝ አይለንም።

አየህ! ፀባይህና ውጤትህ ነበር መካከለኛ፣ ጎበዝና ሰነፍ የሚያስብልህ። አሁን ከፍ ካልክ ወዲህ የሚወዳደረው ግን የባንክ አካውንትህ፣ በትዳርህ ላይ ያለው ደስታ፣ መንፈሳዊ ህይወትህ፣ ....ወዘተ ነው። መካከለኛ መሆን አትፈልግም። ወይ እላይ ጫፍ ስለመውጣት አስብ። መካከለኛ መሆን አያስተማምንም። ትልቁን መመኘት አለብህ። እንደዛ የምትሆነው ግን ራስህ ላይ ከሰራህ ብቻ ነው።

መካከለኛ ነው ገቢህ?፣ መካከለኛ ነው ትዳርህ ላይ ያለው ደስታ?፣ እምነትህ ላይ ያለህ ጥንካሬስ መካከለኛ ነው? በቃ! መካከለኛ ሰው መሆን መጥላት አለብህ። እኔ ጥግ ድረስ አማኝ፣ ጥግ ድረስ ደስተኛ፣ ጥግ ድረስ ገቢ ያለው ሰው መሆን አለብኝ በል። እንደአብዛኛው ሰው መካከለኛ ጥረት እያደረክ መካከለኛ ህይወት መኖር አያዋጣም።

ራስህ ላይ ስሰራ ለውጡ አይታወቅህም። ውስጥ ለውስጥ ነው የምታድገው። የሆነ ሰዓት ግን ወሬህ ተቀይሯል። የድሮ ጓደኞችህ ጋር ስትሄድ መግባባት ሁሉ አቅቶሃል። ‹‹ለካ እንደነርሱ ነበር የማስበው። አሁን ጥያቸው ሄጃለሁ›› ትላለህ። በየዓመቱ መፀለይም ራስ ላይ መስራት ነው። የዚህን ዓለም ውጣውረድ ብቻህን መታገል የለብህም። ከፈጣሪህ ጋር መገናኘትም አለብህ።

በጠዋት መነሳት ራስ ላይ መስራት ነው። ምክንያቱም እንቅልፍህን ሳታሸንፍ ህይወትን ማሸነፍ ከባድ ነው። ለነገህ መድረሻ መማር ነው። መለማመድ፣ ክህሎቶችን ማዳበር፣ ቋንቋን ማሳደግ፣ ካንተ ከሚሻል ሰው ጋር መዋል ራስ ላይ መስራት ነው። ምክንያቱም ከፍታው ላይ ለመውጣት ብዙ ትጥቅ ያስፈልግሃል። አንድ ወታደር ወደጦርነት አንድ ጥይት ብቻ ይዞ አይሄድም እሷን ተኩሶ ይማረካልና። ስለዚህ ብዙ ጥይት መታጠቅ ይኖርበታል።

አየህ! አንተም ምትደርስበት ቦታ ትልቅ ከሆነ መዘጋጀት አለብህ። የምትዘጋጀው ደግሞ ራስህ ላይ ከሰራህ ብቻ ነው። አሁን ራስህ ላይ ስትሰራ፣ ስትማር፣ የሆነ ነገር ስትሞክር ወጪ ልታወጣ፤ ግዜህን ልትሰጥ፤ ጉልበት ልትጨርስ ትችላለህ። አንተ ራስህ ላይ በምትሰራበት ሰዓት ሌላው ወጥሮ ይሰራል። ገንዘብ ያገኛል። ወደኋላ የቀረህ ይመስልሃል። ‹‹እኔ ማስተርሴን ስል ሌላው ያለዲግሪ ሃብታም ሆነ፣ እኔ ኮርሶችን ሳሳድድ ሌላው ሁለት ሦስት ስራዎችን እየሰራ ተቀየረ፣ እኔ ቋንቋ ስለማመድ ሌላው ሩጫ ላይ ነው›› ትላለህ።

አልገባህም እንጂ ባወከው እውቀት ልክ፤ በጨመርከው አዲስ ነገር ልክ ዋጋህ እያደገ ነው። አንተ እውቀትና ልምዱን ስትይዝ ሌላው ሁለት ሶስት ስራ ሰርቶ የማያገኘውን ገቢ በሰዓት ይከፈልሃል። ትደነግጣለህ። ‹‹ወይ ጉድ! ለካ እንደዚህ ነው ራስ ላይ መስራት ውጤቱ›› ትላለህ። ስለዚህ ምን ትጠብቃለህ? ራስህ ላይ ለመስራት ዛሬውኑ ተነሳ!!

# የአርሶ አደሩ ተስፋ- ኢኮግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ከተመሰረተ ከአስር ዓመት በላይ ያስቆጠረው ኢኮ ግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ በኢፌዴሪ የግብርና ሚኒስቴር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኘው ነው። ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂ በመባልም የዋንጫና የወርቅ ሜዳሊያም ተሸልሟል። በ2007 ዓ.ምህረትም እንዲሁ በአገር አቀፍ የላቀ ሳይንሳዊ ፈጠራ መስክ የወርቅ ኒሻንና ዋንጫ ተሸላሚ ለመሆን በቅቷል። ከተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም ድርጅት እኤአ የ2015 የምርጥ ሥራ ፈጠራ (ኢንተርፕረነር) ዘርፍ አሸናፊ እንዲሁም "የአየር ንብረት ለውጥ ተስማሚ ቴክኖሎጂ" ተሸላሚ ሆኗል።

አቶ ከበደ ላቀው የኢኮግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ ኩባንያ መሥራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ ናቸው። አቶ ከበደ ኩባንያው ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ለውጤት እንደበቃ ይናገራሉ። ያን ሁሉ አልፎም በአሁኑ ወቅት ኢኮግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ መፍትሔ በመሆን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን እያበረከተ ይገኛል።

የኩባንያውን ምርት ወደ ገበያ ለማስገባት ብርቱ ትግል ጠይቋቸው እንደነበር የሚያስታውሱት አቶ ከበደ፤ ኢኮግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ ከአስር ዓመታት በላይ እድሜ ማስቆጠሩንና የፈጠራ ሃሳቡን ለማስፋት፣ ተጨባጭ ለማድረግና ቀጣይነት እንዲኖረው ለማስቻል ረዘም ያሉ የድካምና የሙከራ ዓመታትን ማሳለፋቸውን ይናገራሉ።

ከብዙ ድካምና ውጣ ውረድ በኋላ ኢኮግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያን ለአርሶ አደሩ ማቅረብ እንደቻሉ የሚናገሩት አቶ ከበደ፤ የአርሶ አደር ልጅ እንደመሆናቸው ችግሩን በቅርበት ያውቁታል። ለዚህ መፍትሔ መሆን ሲያስቡ ብልጭ ያለላቸው ሃሳብ የአርሶ አደሩን ችግር መቅረፍ የሚችለው የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ መሆኑን ተገነዘቡ። የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያውን ዕውን ለማድረግ ብልጭ ያለላቸውን ሃሳብ መነሻ በማድረግ ቴክኖሎጂን ተጠቅመው የተለያዩ ሃሳቦችን አውጥተዋል፤ አውርደዋል። በዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ ጥናትና ምርምሮችንም አድርገዋል።

ለምነቱን ያጣ መሬት ምርታማ መሆን የሚችለው ማዳበሪያ ሲጠቀም እንደሆነ ጠንቅቀው የሚያውቁት አቶ ከበደ፤ ኢኮግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ ግብርናውን ሊጠቅም የሚችልና በዘርፉ ተጽዕኖ መፍጠር የሚያስችል ሃሳብ ይዞ የመጣ እንደሆነ ነው የተናገሩት። ይህን ሃሳብ ዕውን ለማድረግ ጉዟቸው ረጅምና አድካሚ እንደነበር በማስታወስ በተለይም ከመደበኛው ትምህርታቸው በተጨማሪ ሰፊውን ጊዜያቸውን በጥናትና ምርምር በማሳለፍ በኦን ላይን የተለያዩ ስልጠናዎችን እንዲሁም ቴክኒካል ድጋፎችን ከሳይንቲስቶች የማግኘት ዕድል እንደነበራቸው አጫውተውናል።

በአሁኑ ወቅት ከአፈር ማዳበሪያ በተጨማሪ ለአርሶ አደሩ ጠቃሚ ነው ያሉትን በአገር ውስጥ መመረት የቻለውን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ ይዘው መቅረብ የቻሉት አቶ ከበደ፤ ኢኮግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ የአፈር ማዳበሪያን ተክቶ የሚያገለግል እንደሆነና በአጠቃቀሙ ላይ ብቻ ልዩነት እንዳለው ነው የተናገሩት። እሳቸው እንደሚሉት፤ ምርቱ አዲስ እንደመሆኑ ወደ ማህበረሰቡ ወስዶ ለማስተዋወቅና ለማለማመድ ፈተናው እጅግ ከባድ ነበር። ይሁንና ምርቱ ራሱን በራሱ ፈትኖ፣ አስተዋውቆና በረጅም ጊዜ ቆይታ ወደ ገበያ መግባት ችሏል።

‹‹መጀመሪያ ሃሳብ ብቻ የነበረው ኢኮግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ ሃሳቡ ተሸጦ ውጤት በማምጣት ህልሙን ዕውን ማድረግ የቻለ ምርት ነው›› የሚሉት አቶ ከበደ፤ የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያን ለማምረት በዋናነት በተፈጥሮ የሚገኙ የእንስሳትና የዕጽዋት ተረፈ ምርቶች ግብዓቶች እንደሚያስፈልጉ ይናገራሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ ኩባንያው ማዳበሪያውን ለማምረት ሙሉ ለሙሉ በአገር ውስጥ የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችን ነው የሚጠቀመው። ይህም የውጭ ምንዛሪን የሚጠይቅ ባለመሆኑ ተመራጭ ያደርገዋል። ከዚህ በተጨማሪም ማዳበሪያውን ለማምረት የሚጠቀሟቸው ቀመሮች /ፎርሙላዎች/ በሙሉ ፓተንትድ መሆናቸው ኢኮግሪንን ለየት ያደርገዋል። ኢኮግሪን ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን የአእምራዊ መብት እውቅና የተሰጠው ብቸኛ ካምፓኒ ነው።



**አቶ ከበደ ሳቀው**

ተፈጥሯዊ ከሆኑ ግብዓቶች የሚመረተው ኢኮግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ ምንም አይነት የጎንዮሽ ጉዳት የሌለው፣ ለአጠቃቀም ምቹ፣ የሆነና የአፈር ማዳበሪያን ተክቶ እንዲሁም በተጨማሪነት ጥቅም ላይ መዋል የሚችል ነው። በሰሜን ሸዋ አካባቢ አሌልቱ ቶሎፋ በሚባል ቦታ የሚመረተው ማዳበሪያው፣ ቦታው የተመረጠበት ምክንያት አንደኛ ከአየር ንብረትና ከጥሬ ዕቃ ግብዓት ግኝት በተያያዘ በጥናት ላይ በመመስረት ነው። ማምረቻ ፋብሪካው ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት መገኘቱ ግብዓቶችን ከሁሉም ክልሎች ለማምጣት እንዲሁም ምርቱን ለሁሉም ክልሎች በቀላሉ ለመላክ የሚያስችል አማካኝ ቦታ መሆኑም ሌላው ምክንያት ነው።

‹‹የምርት ሂደቱ ሁለት ነገሮችን ይፈልጋል›› የሚሉት አቶ ከበደ፤ አንደኛው ጥሬ ዕቃዎችን መሰብሰብና ለሚፈለገው አገልግሎት ግብዓት እንዲሆን የማዘጋጀት ሂደት መሆኑን ይጠቁማሉ። ሁለተኛው የተዘጋጁትን የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች ወደ መጨረሻው ሂደት ማስገባትና የሚፈለገውን ውጤት ማግኘት መሆኑን ጠቅሰው። በዚህ ሂደት የኢኮግሪን የመጨረሻው ውጤት ተፈጥሯዊ የሆነ ፈሳሽ ማዳበሪያን ማውጣት እንደሆነና ለዚህም የተለያዩ ዘመናዊና ማንዋል ማሽኖችን ይጠቀማል ብለዋል።

የኩባንያው መስራችና ዋና ስራ አስኪያጅ እንዳሉት፤ ኢኮ ግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ሁሉንም አይነት ንጥረ ነገሮች አሟልቶ የያዘ፣ ለሁሉም የሰብል አይነቶች ተስማሚ የሆነና ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ መጠን የሚያሳድግ ነው። የሰብሉን በሽታ የመቋቋም አቅም የሚያጎለብት ሲሆን፣ በተለይም ከሰው ሰራሹ ማዳበሪያ የማይገኙትንና በአነስተኛ መጠን የሚፈለጉትን ንጥረ ነገሮች አካትቶ የያዘና በሶስት አይነት መንገዶች ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ነው።

ሰው ሰራሽ የሆነውንና ዩሪያና ዳፕ የተባለውን ማዳበሪያ የተጠቀመ አንድ አርሶ አደሩ ኢኮግሪንን በተጨማሪነት ቢጠቀም ምርትና ምርታማነቱን ከማሳደግ በተጨማሪ የመሬቱን ለምነት በመመለስ ለማዳበሪያ የሚወጣውን ወጪ በሂደት እየቀነሰ ይሄዳል። ከዚህ በተጨማሪም ሰብሉ በሽታ እንዲቋቋም በማድረግ ለኬሚካል የሚወጣን ወጪ ይቀንሳል። ይህም በአንድ ጊዜ ሁለትና ሶስት ጠቀሜታዎችን የሚሰጥ ነው። ከወጪ አንጻርም እንዲሁ ኢኮግሪን በአገር ውስጥ ቴክኖሎጂ የሚመረት በመሆኑ ከመደበኛው ማዳበሪያ ይልቅ ዋጋው ተመጣጣኝ ነው። ኢኮግሪን ተፈጥሯዊ በመሆኑ ከጤና አንጻር የሚሰጠው ጠቀሜታ ሶስተኛው ጥቅም ሲሆን፤ ሰዎች ጤናው የተጠበቀ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የተለያዩ ሰብሎችን እንዲጠቀሙ በማድረግ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

ለማንኛውም እርሻ ስራ ኢኮግሪን እጅግ ተስማሚና ውጤታማ እንደሆነ ያነሱት አቶ ከበደ፤ በተለይም የአበባ እርሻዎች ኢኮግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያን በመጠቀም እጅግ ውጤታማ እንደሆኑ ነው ያስረዱት። እሳቸው እንዳሉት፤ ኢኮግሪን ወደ ውጭ የሚላኩ አበቦች መጠናቸውና ጥራታቸው እንዲጨምር አድርጓል። ብዙ ጊዜ የአበባ እርሻ መሬት መታከምን የሚፈልግ ቢሆንም ኢኮግሪን በሂደት መሬቱን እያከመላቸው ነው የሚሄደው። በመሆኑም አብዛኞቹ የአበባ እርሻዎች ኢኮግሪንን በመጠቀም ውጤታማ መሆን ችለዋል።

ኢኮግሪን የተፈጥሮ ፈሻስ ማዳበሪያ በአገር ውስጥ ግብዓት በአገር ውስጥ ቴክኖሎጂ የተመረተ እንደመሆኑ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ እንደልብ ማግኘት የሚቻል ሲሆን፤ አገሪቷ ለማዳበሪያ የምታወጣውን ከፍተኛ ወጪ በሂደት ማስቀረት ያስችላል ያሉት አቶ ከበደ፤ በተለይም በጊዜ ሂደት የመሬትን ለምነት እየመለሰ የሚሄድ በመሆኑ የሚኖረው ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ ነው። በቀጣይም ምርቱን በማስፋት በመላው አገሪቱ ለሚገኙ አርሶ አደሮች የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያን ተደራሽ ለማድረግ እንደሚሠሩ ተናግረዋል።

ፋብሪካው መሰረተ ልማቱ በተሟላለት አካባቢ ዘጠኝ ሄክታር መሬት ላይ ያረፈና በሚፈለገው ልክ መስፋት የሚችል መሆኑን የገለጹት አቶ ከበደ፤ የማምረት አቅሙም በዚሁ ልክ ማደግ እንደሚችል ነው የተናገሩት። በቀጣይም ምርቱን በየክልሎች በማምረት አርሶ አደሩ ተፈጥሯዊ የሆነውን ማዳበሪያ ከደጁ ማግኘት እንዲችል ይደረጋል ብለዋል። ለዚህም የቅድመ ዝግጅት ሥራ እየሠሩና የማስፋፊያ ቦታ መጠየቃቸውን አስታውቀዋል።

ኢኮግሪን ዛሬ ላይ እንዲደርስ ቤተሰብ፣ ጓደኛና የተለያዩ ሰዎች ሚና እንዳላቸው ያመለከቱት አቶ ከበደ፤ በተለይም እርሳቸው የሕይወታቸውን ሰፊ ጊዜ እንደወሰደባቸው ይናገራሉ። ሃሳቡ በልጽጎ ፍሬያማ እንዲሆን በአገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም ያሉ በርካታ ሰዎች ድርሻ ያላቸው መሆኑንም ጠቅሰው፣ ሃሳቡ ብዙ ጊዜ፣ ጉልበት፣ ገንዘብና ዕውቀት፣ የፈሰሰበት ብዙዎች ዋጋ የከፈሉበት ድምር ውጤት መሆኑን ያብራራሉ።

ስኬት የሚለካው በተለያየ መንገድ እንደሆነ ያነሱት አቶ ከበደ፤ በሃሳብ ደረጃ የነበረውን ኢኮግሪን ዛሬ ላይ ፈሳሽ ማዳበሪያ የሚል ምርት እንዲኖር ማድረግ በራሱ አንድ ስኬት ነው ይላሉ። ይሁንና ኢኮግሪን በብርቱ ተፈትኖ ያለፈ ሃሳብ በመሆኑ እንዳይቀጭጭ የሁሉንም እገዛ ይፈልጋል ብለዋል።

በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ የሚገባው የአፈር ማዳበሪያ በየጊዜው የሚገጥመው እጥረትና የዋጋ ንረት አርሶ አደሩን ለምሬት የሚዳርግ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መፍትሔው ራስን መቻል ነው የሚሉት አቶ ከበደ፤ በተለይም አርሶ አደሩ ራሱን በማገዝ ከውጪ የሚመጣውን የአፈር ማዳበሪያ በተፈጥሮ ማዳበሪያ የመተካትና ኢኮግሪንን የመሰሉ የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ አምራቾችን በማስፋትና በማስተዋወቅ ሁሉም ሰው የመፍትሔው አካል ሊሆን እንደሚገባ ነው ያስረዱት።

እሳቸው እንዳሉት፤ አገር በቀሉ ኢኮግሪን የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ክልሎች በተለይም ኦሮሚያ ክልል በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በአማራ ክልል ምርቱ እየተለመደ መጥቷል። በቀጣይም ምርቱን ከመጠቀም ባለፈ አጠቃቀሙን ማስረዳትና ማስተዋወቅ ሰፊ ሥራን ይጠይቃል። በተለይም አርሶ አደሩ ምርቱን በውጤታማነት መጠቀም እንዲችል የሁሉም ርብርብ ያስፈልጋል። ከዚህ ባለፈም ኢኮግሪን አገር በቀል ምርት እንደመሆኑ የአገር ሃብት እንደመሆኑ መንግሥትን ጨምሮ ማንኛውም ሰው የኔ ብሎ ሊቆምለት ይገባል።

ኢኮግሪን በአገር ውስጥ የሚመረት ከመሆኑም በላይ የጥሬ ዕቃ ውስንነት የሌለው በመሆኑ ምርቱን በተፈለገው መጠን ማምረት ይቻላል። የማሸጊያ ጥሬ ዕቃው ከውጭ የሚገባ በመሆኑ የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ ማሸጊያ ጀሪካን ለማምረት የሚስችለው የጥሬ ዕቃ አቅርቦትና ሌሎች ሁኔታዎች ምቹ ከሆኑ የማምረት አቅም ውስንነት አይኖረውም። ኩባንያው በአሁኑ ወቅት የማስፋፊያ ሥራ እየሠራ ሲሆን፣ ስራው ሲጠናቀቅም በወር እስከ ስድስት ሚሊዮን ሌትር የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያ የማምረት አቅም ይኖረዋል።

ኩባንያው በተለያየ መንገድ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለ ሲሆን፤ አንደኛ ጥሬ ዕቃውን በማቅረብ፣ ሁለተኛ በማምረት፣ ሶስተኛ ምርቱን በመሸጥ ሥራ ላይ ለተሰማሩ 300 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል። ድርጅቱ በቀጥታ ከቀጠራቸው በተጨማሪ ምርቱ በስፋት በሚፈለግበት ወቅት ተጨማሪ የቀን ሠራተኞችን ይቀጥራል።

ማህበራዊ ኃላፊነት ከመወጣት አንጻር እንደ ኩባንያ ችግር ፈቺ የሆነና አገር በቀል የተፈጥሮ ፈሳሽ ማዳበሪያን ለአርሶ አደሩ ማቅረብ መቻል እንዲሁም ከትርፍ በላይ አርሶ አደሩ ላይ ውጤት ለማምጣት እየተጋ ያለ ኩባንያ ስለመሆኑ የተናገሩት አቶ ከበደ፤ አቅም ለሌላቸው አርሶ አደሮች ምርቱን በነጻ በመስጠት እንደሚያስተዋውቅም ገልጸዋል። በአካባቢው የሚገኙ አርሶ አደሮች ውጤታማ መሆን እንዲችሉ ስልጠና ይሰጣል። አገራዊ በሆኑ ጉዳዮች መንግሥት ለሚያደርገው ጥሪም ምላሽ ይሰጣል።

‹‹ስራ ፈጣሪዎች ሁልጊዜም ችግር ፈቺ ናቸው›› የሚሉት አቶ ከበደ፤ ማንኛውም ችግር የሚነሳው ከአካባቢ እንደሆነ ይናገራሉ። በመሆኑም በትውልድ አካባቢያቸው ሰሜን ሸዋ አካባቢ ቤተሰባቸውን ጨምሮ በአካባቢው የሚገኙ አርሶ አደሮችን ችግር በማስተዋል እነሆ መፍትሔ በማለት ተፈጥሯዊ የሆነ ፈሳሽ ማዳበሪያ ለገበያ ማቅረብ መቻላቸውን ተናግረዋል። ኢኮግሪን፤ ለሁሉም አይነት የሰብል አይነቶች ማለትም ለቤት ውስጥ አበባ፣ ለልዩ ልዩ የአትክልት፣ እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ፣ በቆሎ ለመሳሰሉት ጥራጥሬ ሰብሎች፣ ለፍራፍሬና ለማንኛቸውም አይነት ችግኞች ልማት መጠቀም ይቻላል። ምርቱም ከአንድ ሌትር ጀምሮ እስከ 200 ሌትር ተዘጋጅቶ ይቀርባል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የተፈጥሮ ሀብቶቹን በሚገባ እንዳይጠቀም መሰረተ ልማት ያጠረው ክልል

አንተነህ ቸሬ

ከዚህ ቀደም በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ስር የነበሩትን የምዕራብ ኦሞ፣ የቤንች ሸኮ፣ የከፋ፣ የዳውሮና የሸካ ዞኖች እና የኮንታ ልዩ ወረዳን በአንድነት በመያዝ በኅዳር ወር 2014 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ 11ኛው ክልላዊ መንግሥት ሆኖ የተዋቀረው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል፤ በተፈጥሮ ሀብት የታደለ ነው።

ክልሉ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጣና ብቻ ሳይሆን ለሌሎቹ የአገሪቱ አካባቢዎችም የሚበቃ የተትረፈረፈ ሀብት አለው። ዓመታዊ ሰብል፣ ቡናና ቅመማ ቅመም፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ኢንዱስትሪ እና አገልግሎት ዘርፎች በክልሉ በኢንቨስትመንት ለመሰማራት የሚያስችሉ የምጣኔ ሀብት መስኮች ናቸው። በተለይም ክልሉ ያለው የቡና፣ የሻይ ቅጠል፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የማዕድናት ሀብት አገርን የሚያኮራ፣ ባለሀብቶችን በኢንቨስትመንት ለመሰማራት የሚያነሳሳ እና የሕዝብን የልማት ጥያቄ ለመመለስ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር መልካም አጋጣሚና ፀጋ ነው።

ክልሉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት የሀገር ኢኮኖሚን በብርቱ የሚደግፉ ምርቶች መገኛ ነው። ከፍተኛ የቡናና የማዕድን ሀብቶችን የያዘው ይህ ክልል፤ ሀብቱ ከክልሉ አልፎ ለአገርም የሚተርፍ ፀጋ ነው። ክልሉ አስደናቂ የሆነ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ልምላሜና የተፈጥሮ ሀብት ያለው በመሆኑ የባለሀብቶችን ትኩረት የሚስብ መሆኑ አያጠያይቅም።

የክልሉን ሀብቶች ለመለየት የሚደረጉ ተጨማሪ ጥናቶች እንደተጠበቁ ሆነው፤ እስካሁን በተካሄደው ጥናት 88ሺ 786 ሄክታር ለዓመታዊ ሰብሎች፣ አራት ሺ 875 ሄክታር ለቡናና ቅመማ ቅመም እና 20ሺ 565 ሄክታር ለአትክልትና ፍራፍሬ፤ በአጠቃላይ 134ሺ 126 ሄክታር መሬት ለግብርና ዘርፍ ምቹ እንደሆነ ታውቋል። በአገልግሎትና በኢንዱስትሪ ዘርፎችም ክልሉ የኢንቨስትመንት መዳረሻና አማራጭ መሆን የሚችል አካባቢ ነው።

የክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ኤጀንሲ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ ክልሉ ወርቅን ጨምሮ የተለያዩ ማዕድናት ባለፀጋ ነው። ከወርቅ ማዕድን በተጨማሪ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውል የድንጋይ ከሰል በክልሉ በዳውሮ እና በኮንታ አካባቢዎች በስፋት ይገኛል። ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን የብረትና የድንጋይ ከሰል ማዕድናትም ሌሎች በክልሉ የሚገኙ ሀብቶች ናቸው። በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ማዕድን ለማዕከላዊ ገበያ ከሚያቀርቡ የሀገሪቱ አካባቢዎች መካከል አንዱ ሆኗል። በክልሉ ገና በጥናት ያልተለዩ ብዙ ሀብቶች አሉ። ኦፓልና ሌሎች ማዕድናትም በክልሉ ይገኛሉ ተብሎ ይገመታል።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የተትረፈረፈ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት ቢሆንም በመሰረተ ልማት አቅርቦት፣ በተለይም በመንገድ ዝርጋታ ረገድ ከፍተኛ ችግሮች ያሉበት ክልል መሆኑን ከክልሉ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። በክልሉ ግንባታቸው ያልተጠናቀቁ እንዲሁም በአፈፃፀም ድክመት ምክንያት ውላቸው እንዲቋረጥ የተደረጉ ፕሮጀክቶች አሉ። መንገዶችን በፍጥነት አጠናቅቆ ለአገልግሎት ክፍት በማድረግ ረገድም ከፍተኛ ውስንነቶች አሉ።

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የመሰረተ ልማት ክላስተር አስተባባሪና የትራንስፖርትና መንገድ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ፋጂዮ ሳፒ ስለክልሉ የመንገድ መሰረተ ልማት የሥራ እንቅስቃሴ ከ‹‹አዲስ ዘመን›› ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገዋል።

### የክልሉ የመንገድ ሽፋንና ግንባታ

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በመሰረተ ልማት አቅርቦት ወደኋላ ከቀሩ አካባቢዎች መካከል ይጠቀሳል። በተለይ የመንገድ መሰረተ ልማት ችግሮች በስፋት ይስተዋሉበታል። ለአብነት ያህል ተርጫ አካባቢ የሚከናወኑ ሦስት የመንገድ ፕሮጀክቶች አልተጠናቀቁም። ከሸሸንዳ ወደ ቴፒ እንዲሁም ከቴፒ ወደ ማሻ ጎሬ የሚወስዱት መንገዶችም አፈፃፀማቸው ደካማ ነው። በቤንች ሸኮ እና በከፋ ዞኖች ውስጥ እየተገነቡ ከነበሩ መንገዶች መካከል በአፈፃፀም ድክመት ምክንያት ውላቸው እንዲቋረጥ የተደረጉ ፕሮጀክቶች አሉ። መንገዶችን በፍጥነት አጠናቅቆ ለአገልግሎት ክፍት በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ውስንነቶች ይታያሉ።

ይህን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ግንባታቸው በፌዴራል መንግሥት እየተከናወኑ የሚገኙ የመንገድ ፕሮጀክቶች አሉ። እነዚህ የአስፋልት መንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ከነጉድለታቸውም ቢሆን በጥሩ አፈፃፀም ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል በምዕራብ ኦሞ ዞን የሚከናወነው የማጂ መንገድ ግንባታ በተሻለ አፈጻጸም ላይ ይገኛል።

በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች የሰላም መደፍረስ የነበረ ቢሆንም፣ ሕዝቡ ከፍተኛ የመሰረተ ልማት ፍላጎት ያለው በመሆኑ የፀጥታ ችግሮችን እየተከላከለና ተቋራጮችን እየጠበቀ በአካባቢዎቹ የሚከናወኑ የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታዎች እንዳይቋረጡና ግንባታቸውም በተቻለ መጠን በፍጥነት እንዲከናወን ከፍተኛ እገዛ እያደረገ ይገኛል።

ክልሉ ሰፊ የመንገድ መሰረተ ልማት ችግሮች (በተለይም የመንገዶችና የድልድዮች ችግሮች) እንዳሉ በመገንዘብና ለችግሮቹ ምንጭ የሆኑ የመልካም አስተዳደር ድክመቶችን በመለየት የተጀመሩ ፕሮጀክቶች እንዲጠናቀቁ ጥረት እየተደረገ ነው።

በ‹‹ሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት መርሃ ግብር›› (Universal Rural Road Access Program (URRAP)] ተጀምረው የተቋረጡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን አቅም በፈቀደ መጠን ግንባታቸውን ለማስቀጠል እየተሰራ ነው። ለአብነት ያህል በዚህ ዓመት የመንገድ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ርብርብ እየተደረገ ነው። ከመንገዶቹ በተጨማሪ የአራት ድልድዮች ግንባታም እየተጠናቀቀ ይገኛል። በክልሉ መንገዶች ባለስልጣን የሚገነቡ ድልድዮችም አሉ። ባለፈው ዓመት አምስት ድልድዮች ግንባታቸው ተጠናቆ ለአገልግሎት በቅተዋል።

የትምህርትና የጤና ዘርፍ መሰረተ ልማት ስራዎች ጥሩ አፈፃፀም ቢኖራቸውም፣ ቀላል የማይባሉ የአፈፃፀም መጓተቶች ይስተዋሉባቸዋል። የግንባታ ግብዓቶች (ሲሚንቶ፣ ብረት...) ዋጋ መናር አንዳንድ የትምህርትና የጤና ዘርፍ መሰረተ ልማት ግንባታዎች እንዲቋረጡ ምክንያት ሆኗል። እነዚህ ችግሮች ቢኖሩም የክልሉን ሕዝብና መንግሥት አቅም በመጠቀም እንዲጠናቀቁ የተደረጉ የትምህርትና የጤና ተቋማት ፕሮጀክቶች አሉ። ከተቋራጮች ጋር በመነጋገር ግንባታቸው የተቋረጡት ፕሮጀክቶች እንዲጠናቀቁ ይደረጋል።

### የተቋራጮች አቅም

የመንገድ ግንባታዎችን የሚያከናውኑት አብዛኞቹ ተቋራጮች የውጭ አገራት ድርጅቶች ናቸው። ግንባታዎቹ የጥራት ጉድለቶች ይታዩባቸዋል፤ በሚፈለገው ፍጥነትም አይሰሩም። እንዲህ አድርገው ውላቸው እንዲቋረጥ ይፈልጋሉ፤ውላቸው ሲቋረጥ ግንባታውን ትተው ይሄዳሉ። የግንባታ ውላቸው ከተቋረጠ ፕሮጀክቶች መካከል ብዙዎቹ በውጭ ተቋራጮች የተያዙ ናቸው። የአገር ውስጥ ተቋራጮች የተሻለ አፈፃፀም አላቸው። የአገር ውስጥ ተቋራጮች ችግሮችን ተቋቁመው የመስራት ልምድ አላቸው። ጥሩ አፈፃፀም ያለውና በምዕራብ ኦሞ ዞን፣ ማጂ አካባቢ እየተገነባ የሚገኘው መንገድ በአገር ውስጥ ተቋራጮች የተያዘ ነው። ይህ የሚያመለክተው በግንባታው ዘርፍ ያሉ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የአገር ውስጥ ተቋራጮችን አቅም ማሳደግ አስፈላጊ እንደሆነ ነው። አቶ ፋጂዮ ‹‹የውጭ ተቋራጮች አፈጻጸማቸው ደካማ ነው። ስለሆነም የአገር ውስጥ ተቋራጮችን አቅም ካላሳደግን የፕሮጀክቶች ግንባታ መጓተት ችግር ተባብሶ መቀጠሉ አይቀርም›› ይላሉ።

> የመንግሥት አቅም ውስን በመሆኑ፣ ኅብረተሰቡን ማሳተፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የክልሉ ሕዝብ በመሰረተ ልማት ግንባታዎች እንዲሳተፍ እየተደረገ ነው። በዚህም ሕዝቡ ገንዘቡንና ጉልበቱን በመሰረተ ልማት ግንባታና ማስፋፊያ ተግባራት ላይ እያዋለ ይገኛል። ለአብነት ያህል የቤንች ሸኮ ዞን ሕዝብ በራሱ ተነሳሽነት ገንዘቡንና ጉልበቱን አስተባብሮ ሦስት ድልድዮችን ሰርቶ በማስመረቅ ለአገልግሎት አብቅቷል። ይህ ተግባር ኅብረተሰቡ ተነሳሽነት የሚፈጥርለትና የሚያስተባብረው አካል ካገኘ ትልልቅ የልማት ተግባራትን ማከናወን እንደሚችል አሳይቷል።

### የበጀት እጥረት

የበጀት እጥረትም አሳሳቢ ችግር ነው። የሰሜኑ ጦርነት እንዲሁም ሌሎች አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ችግሮች በአገሪቱ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ በማሳደራቸው ለፕሮጀክቶች ግንባታ በቂ ገንዘብ ያለማግኘት ችግር አለ። በክልሉ ለመንገድ የሚመደበው በጀት አነስተኛ ነው። ባለፈው ዓመት ለመንገዶችና ድልድዮች ግንባታ የተመደበው በጀት 53 ሚሊዮን ብር ነበር፤አሁን ባለው አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታ በ53 ሚሊዮን ብር ጥራት ያለው መንገድ መገንባት አይቻልም። ለመንገድ የሚመደበው በጀት አነስተኛ በመሆኑ ያሉንን ትንንሽ ማሽኖችን በመጠገንና በማስተካከል ብዙ የመንገድ ጥገና ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው።

### የኅብረተሰብ/ባለሀብቶች ተሳትፎ

የመንግሥት አቅም ውስን በመሆኑ፣ ኅብረተሰቡን ማሳተፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የክልሉ ሕዝብ በመሰረተ ልማት ግንባታዎች እንዲሳተፍ እየተደረገ ነው። በዚህም ሕዝቡ ገንዘቡንና ጉልበቱን በመሰረተ ልማት ግንባታና ማስፋፊያ ተግባራት ላይ እያዋለ ይገኛል። ለአብነት ያህል የቤንች ሸኮ ዞን ሕዝብ በራሱ ተነሳሽነት ገንዘቡንና ጉልበቱን አስተባብሮ ሦስት ድልድዮችን ሰርቶ በማስመረቅ ለአገልግሎት አብቅቷል። ይህ ተግባር ኅብረተሰቡ ተነሳሽነት የሚፈጥርለትና የሚያስተባብረው አካል ካገኘ ትልልቅ የልማት ተግባራትን ማከናወን እንደሚችል አሳይቷል።

‹‹አሁን ያለው የመንግሥት ሀብት ውስን ነው፤ የመንግሥትን ሀብት ብቻ ከምንጠብቅ አንዳንድ ሥራዎችን በራሳችን አቅም መስራት እንችላለን›› በሚል እሳቤ መነሻነት፣ ይህ ተሞክሮ ወደ ሌሎች የክልሉ ዞኖች እንዲሰፋና እንዲተገበር እየተደረገ ይገኛል። የከፋ ዞን ሕዝብ ከ35 ሚሊዮን ብር በላይ በማሰባሰብ ያከናወናቸው የመንገድና የድልድይ ስራዎች የዚህ ተሞክሮ ማሳያዎች ናቸው። ሌሎች ክልሎችም ውስን የሆነውን የመንግሥትን በጀት ከመጠበቅ ይልቅ በተቻለ መጠን የሕዝብ ንቅናቄ በመፍጠር አንዳንድ የልማት ፕሮጀክቶችን ግንባታ ቢያከናውኑ የኅብረተሰቡ ተጠቃሚነት ያድጋል።

ክልሉ ለኢንቨስትመንት ከፍተኛ አቅም ያለው በመሆኑ በክልሉ በኢንቨስትመንት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ባለሀብቶች በክልሉ የመሰረተ ልማት ዘርፎች ግንባታ ላይ የራሳቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ይጠበቃል። በዚህ ረገድ አንዳንድ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቻቸው በሚገኙባቸው አካባቢዎች የሚያከናውኗቸው ተግባራት አሉ። ኅብረተሰቡ በሚሳተፍባቸው የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ላይ የራሳቸውን ተሳትፎ የሚያደርጉ ባለሀብቶችም አሉ።

ክልሉ ካለው አቅም አንፃር ከዚህ የበለጠ ሥራ ስለሚጠበቅ በቀጣይ ይህን አሰራር በተደራጀ መልኩ መምራት ያስፈልጋል። ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ ባለሀብቶችን በማስተባበር በመሰረተ ልማት ግንባታ ተግባራት ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይደረጋል። በክልሉ በርካታ ባለሀብቶች የቡናና የሰብል ልማትን ጨምሮ በሌሎች ዘርፎችም በኢንቨስትመንት ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። ባለሀብቶቹ ክልሉን በመንገድ ብቻም ሳይሆን በሌሎችም ዘርፎች ተጠቃሚ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በቀጣይ ክልሉ ብዙ ባለሀብቶች በሁሉም ዘርፎች በኢንቨስትመንት ላይ እንዲሰማሩ እና በየቦታው በሚገነቡ የመንገድና ድልድዮች ግንባታ ላይ ከእስካሁኑ የበለጠ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ አሰራሮችን ያመቻቻል።

### የዘርፉ ተስፋዎችና ቀጣይ እቅዶች

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት የሆነ አካባቢ ነው። ይህ ሀብት በሚገባ ቢታወቅና በመሰረተ ልማት ቢተሳሰር ኢትዮጵያን ሊያሻግር የሚችል አቅም አለው። ቀደም ባሉት ስርዓቶች እንኳን የሀገሪቱ መሪ ይቅርና ሚኒስትሮች አካባቢውን በሚገባ ጎብኝተውት አያውቁም። አሁን ግን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ ከፍተኛ አመራሮች አካባቢውን በመጎብኘት በአካባቢው ያለውን የመሰረተ ልማት ችግር ተመልክተዋል፤የክልሉን አቅም ተገንዝበዋል።

ይህን ተከትሎ በክልሉ የአውሮፕላን ማረፊያን ጨምሮ ሌሎች የመሰረተ ልማት ግንባታዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። ይህ ደግሞ ለክልሉ የመሰረተ ልማት ግንባታም ሆነ አጠቃላይ ልማት ተስፋ ሰጪ ጅምር ነው። ግንባታቸው የተቋረጡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን በዝርዝር ለኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በማሳወቅ የአስተዳደሩ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ፕሮጀክቶቹን ጎብኝተዋል። በአካባቢው ያለውን ሀብትና አቅም ለይተው ማወቃቸው በቀጣይ የክልሉን የመሰረተ ልማት ችግሮች ለመፍታት ለሚደረገው ጥረት መደላድል ይፈጥራል። አቶ ፋጂዮ ‹‹ከፍተኛ ትኩረት ከሚፈልጉ የክልሉ ችግሮች መካከል አንዱ የመንገድ መሰረተ ልማት አቅርቦት እጥረት በመሆኑ አቅምን አስተባብሮ በመጠቀም የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር አቅጣጫ አዘጋጅተናል›› ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በማደግ ላይ ያሉ አገራትን የማደግ ፍላጎት እውን ለማድረግ!

በማደግ ላይ ያሉ አገራት የማደግ ፍላጎታቸውን በሚፈታተኑ መልከ ብዙ ፈተናዎች ውስጥ መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። አገራቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚከሰቱ ችግሮች እና ችግሮቹ በሚፈጥሯቸው ጫናዎች ሕዝቦቻቸው ብዙ ዋጋ ለመክፈል እየተገደዱ ነው። ይህም ተስፋ ባደረጓቸው ነገዎቻቸው ላይ ጥላ እያጠላ ይገኛል።

በአንድ በኩል አገራቱ የተሸከሙት እዳና እዳውን ለመክፈል ያለባቸው ከፍያለ ጫና፤ በሌላ በኩል በየወቅቱ የሚከሰቱ ዓለም አቀፍ ችግሮች "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ " እየሆኑባቸው ሕዝቦቻቸው የዕለት ተዕለት ሕይወታቸውን በአግባቡ መምራት የሚችሉበትን አቅም እያጡ ነው። ይህ ደግሞ አሁን አሁን ከፍ ባለ የኖሮ ውድነት እየተገለጠ ይገኛል።

አገራቱ ከትናንት የወረሷቸው የእርስ በርስ ግጭቶችና ግጭቶቹ እየፈጠሩት ያለው ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ፣ እነዚህን ቀውሶች በግልጽም ይሁን በስውር የሚያባብሱ ማቆሚያ ያጡ ጣልቃ ገብነቶች የእነዚህን አገራት ሕዝቦች አድጎ የመገኘት ህልም እየተፈታተኑት ነው። በአጠቃላይ ወደ ህልማቸው የሚያደርጉትን ጉዞ ጎታች ተግዳሮት ሆኗል።

ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ እነዚህ አገራት ችግሮቻቸውን አሸንፈው እንዲወጡ የሚያስችላቸውን የፋይናንስም ሆነ ሌሎች ድጋፎች በሚፈልጉት መጠንና ጊዜ ኃላፊነት በሚሰማው መልኩ ለመስጠት አለመቻሉ ፣ አብዛኞቹ ቃል የተገቡ ርዳታዎች በወቅቱ አለመለቀቃቸው ፣ ከዚያ ይልቅ የተለያዩ የማስገደጃ ጫናዎች ይዘው የመምጣታቸው እውነታ አገራቱ እነሱን ታሳቢ አድርገው በሚጀምሯቸው ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ የጎላ ክፍተት እየፈጠረ ነው።

እነዚህ አገራት የጀመሯቸውን የልማት ፕሮጀክቶች ለማስፈጸም የሚያስፈልጋቸውን ከፍያለ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት፤ ቀደም ሲል የነበረባቸውን እዳ የመክፈል አስገዳጅ ሁኔታዎች ውስጥ መሆናቸው፤ በብዙ ልፋት የሚያገኙትን የውጭ ምንዛሪ መልሰው ለእዳ ማቀለያ በመክፈል እየሄዱበት ያለው መንገድ "ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ" ሆኖባቸው፤ የድካማቸውን ያህል መራመድ የሚችሉበትን አቅም መግዛት እንዳይችሉ አድርጓቸዋል።

ዛሬ ላይ የዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ትልቁ ስጋት እየሆነ የመጣውን የአካባቢ የአየር ብክለት ለመከላከል የሚያደርጓቸው የተለያዩ ጥረቶች፤ ስጋቱን መከላከል የሚያስችል አቅም መፍጠር የሚችሉ ቢሆኑምለስራው የሚያስፈልጋቸውን ፋይናንስ ከመደገፍ አኳያ ያለው ኃላፊነት የጎደለው አካሄድ በቀጣይ ለአገራቱ ህዝቦች የከፋ ስጋት ይዞ መምጣቱ የማይቀር ነው።

ችግሩን በመፍጠር ሂደት ውስጥ እዚህ ግባ የሚባል ተሳትፎ የሌላቸው እነዚህ አገራት ፤ ችግሩ እየፈጠረባቸው ካለው አሁናዊም ሆነ በቀጣይ ሊያስከትልባቸው የሚችለው ከፍያለ ተጽዕኖ አሁን እየተፈታተኗቸው ካሉ መልከ ብዙ ችግሮች ጋር ተዳምረው የአገራቱን ሕዝቦች ሕይወት የከፋ አደጋ ላይ እንደሚጥለው ይታመናል። ይህም በብዙ ዓለም አቀፍ መድረኮች መደመጥ ከጀመረ ውሎ አድሯል።

እነዚህን መልከ ብዙ ችግሮች በመቅረፍ በማደግ ላይ ያሉ አገራት ነገዎች ብሩህ እንዲሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ «የ21ኛው ክፍለ ዘመን ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የባለብዙ ወገን ልማት ባንኮችን ሞዴል ማሻሻል» በሚል ርዕስ በፈረንሳይ ፓሪስ በተዘጋጀው ውይይት ላይ እንደገለጹት፤ ዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ከዚህ በፊት ከእነዚህ አገራት ጋር የገቧቸውን ስምምነቶች መተግበር ይጠበቅበታል።"

አገራቱ ለልማታቸው የሚያስፈልጋቸውን ሀብት ከተለያዩ ጫናዎች ነጻ በሆነ መንገድ ፤ የኮንሴሽናል ፋይናንስ አቅርቦትን በማሳደግ የሚፈታበትን መንገድ ማስፋት ፣ ወደ አረንጓዴ ልማት ሽግግር የሚያደርጉትን ጥረት መደገፍ ፣ የዕዳ ቀውስን ማቆም ትኩረት ተሰጥቷቸው ከፍባለ የኃላፊነት መንፈስ ሊተገበሩ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ጽንፈኝነት የከፋ ዋጋ ሳያስከፍለን

ከመርደቂዮስ

በቀደሙት ዘመናት ሆነ ዛሬም ዓለምን ከምንም በላይ ዋጋ ካስከፈሉት አንዱ እና ዋንኛው ጽንፈኝነት እንደሆነ ይታመናል። በቀጣይም የሰው ልጅ ብሩህ ነገዎችን ሊያጨልም ይችላል ተብሎ የሚሰጋውም ይኸው የአስተሳሰብ መዛነፍ እንደሚሆን በብዙዎች ዘንድ የጋራ እሳቤ አለ።

ዥንጉርጉር በሆነ ዓለም ውስጥ ለአንድ አስተሳሰብ ግዝፈት ሰጥቶ እሱን አልፋና ኦሜጋ አድርጎ የማየት፤ ከዛም አልፎ አስተሳሰቡን በኃይል ሆነ በተለያዩ መንገዶች በሕዝቦች ላይ ለመጫን የሚደረገው ይህ አይነቱ አስተሳሰብ /ጽንፈኝነት /በተለይም ብዝሃነት በሰፈነበት ማህበረሰብ ውስጥ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ የከፋ እንደሚሆን ይታመናል ።

ጽንፈኝነት ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መሰረት ይዞ ላለፉት መቶ ዓመታት ዓለማችንን የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈላት ከሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ባለፈ፤ ጽንፈኛ አስተሳሰቦችን በተለያዩ የዓለም ሕዝቦች ላይ ለመጫን በስውርም ይሁን በግልፅ የተካሄዱ ጦርነቶችና ከዚሁ ጋር ተዳምረው የሄዱ ሴራዎችን መጥቀስ ይቻላል።

> ጽንፈኝነት ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መሰረት ይዞ ላለፉት መቶ ዓመታት ዓለማችንን የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈላት ከሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ባለፈ፤ ጽንፈኛ አስተሳሰቦችን በተለያዩ የዓለም ሕዝቦች ላይ ለመጫን በስውርም ይሁን በግልፅ የተካሄዱ ጦርነቶችና ከዚሁ ጋር ተዳምረው የሄዱ ሴራዎችን መጥቀስ ይቻላል

አፍሪካ ውስጥ ጸረ-ቅኝ ግዛት ትግል ስኬት እያስመዘገበ በመጣበት ማግስት ፤አፍሪካውያን በብዙ መስዋእትነት የተጎናጸፉትን የፖለቲካ ነጻነት በአግባቡ ሳያጣጥሙ ፤በተለያዩ ጽንፈኛ የፖለቲካ አስተሳሰቦች ተጠልፈው ዛሬም ድረስ የግጭትና የሁከት ማእከል ሆነዋል። የአህጉሪቱ የነጻነት አባቶች ተስፋ ያደረጓትን አፍሪካ እስከ ዛሬ መፍጠር ሳይቻል ቀርቷል።

በጎረቤት አገር ሶማሊያ ያለው እውነታም ከዚህ የተለየ አይደለም። አንድ አይነት ቋንቋ ተናጋሪ ፤ የጋራ ባህል እና ሀይማኖት ባለቤት የሆነው የሀገሪቱ ህዝብ ሳይወድ በግድ ጽንፈኛ አስተሳሰቦች በፈጠሩት ግራ መጋባት ብሄራዊ ማንነቱን አጥቶ ተለያይቶ ለመኖር ተገድዷል። በዚህም ለተለያዩ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ተዳርጓል።

በመካከለኛው ምሥራቅ የብዙ ዘመናት አገረ መንግስት ታሪክ ባለቤት የሆኑ፤ ለዓለም አሁነኛ ስልጣኔ ትልቅ ድርሻ የነበራቸው እንደ ሶሪያና ኢራቅ የመሳሰሉ አገራት ፤ ዓለም አቀፍ ሴራ በወለዳቸው ፅንፈኛ አስተሳሰቦች ተጠልፈው የወንድማማችነት ፍቅራቸውን እና ብሔራዊ ክብራቸውን አጥተው፤ አገራዊ ሕልውናቸው ዛሬም በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ይገኛል።

"እኔ ካልኩት በቀር ሊላ ምርጫም አማራጭም የለም፤ ያለው አማራጭ መቀበል ወይም አለመቀበል ነው፤ ከዚህ ውጪ ሊኖር የሚችለው አሸንፎ መውጣት፤ ወይም ተሸንፎ ለአሸናፊው አስተሳሰቡ መገዛት ነው " በሚለው የተዛነፈ አስተሳሰብ ላይ መሰረቱን ያዋቀረው ጽንፈኝነት፤ በኛም አገር ትልቁ አገራዊ ስጋት ከሆነ ውሎ አድሯል። እያስከፈለንም ያለው ዋጋ በቀላሉ ሊሰላ የሚችል አይደለም።

መንግሥት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በውይይትና በድርድር ላይ የተመሰረተች ለሁሉም እኩል የሆነች አገር በትናንቱ መሰረት ላይ ለመገንባት የያዘውን አዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብ የአቅመ ቢስነት መገለጫ በማድረግ አገርና ሕዝብን ብዙ ያልተገቡ ዋጋዎችን ያስከፈሉ በጽንፈኛ አስተሳሰቦች የተነዱ የጥፋት ተግባራት ተከናውነዋል።

በዚህም በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ዜጎች ለሞት፤ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ለስደት ተዳርገዋል። የሕዝቦችን ተቻችሎ በአንድነት የመኖር ባህልን ጨምሮ አገረ መንግስቱን ስጋት ላይ የጣሉ ብዛት ያላቸው ክስተቶች ተፈጥረዋል፤ ዛሬም ቢሆን አገራዊ የእለት ተእለት ዜናዎቻችን ጽንፈኝነት እንደአስተሳሰብ የወለዳቸው ፈተናዎች መገለጫ ናቸው።

በአገሪቱ ጽንፈኝ ግለሰቦችና ቡድኖች በየወቅቱ መልካቸውን እየቀያየሩ ሕዝባዊ አጀንዳዎችን ሳይቀር በመጥለፍ አገርን ሰላምና እረፍት በመንሳት ዜጎች በብዙ ተስፋ ከፍ ያለ ዋጋ ከፍለው የጀመሩትን ለውጥ እንደቀደሙት የለውጥ ተሞክሮዎች ለማምከን በግልጽ ፣ በአደባባይ ፣ በስውር የታሪካዊ ጠላቶቻችን ተልእኮ አስፈጻሚ እስከመሆን በደረሰ ባንዳነት እየተንቀሳቀሱ ነው።

እነዚህ ኃይሎች በአገራችን ረጅም ታሪክ ውስጥ ባልታየ መንገድ የሃይማኖት ስፍራዎችን እና ሃይማኖታዊ /መንፈሳዊ አጀንዳዎችን ለጽንፈኛ አስተሳሰባቸው ማስፈጸሚያ እስከ ማድረስ በደረሰ መታወር ውስጥ ይገኛሉ። የዜጎችን ሰላም ከዛም አልፎ ህይወት በመቅጠፍ ይህንንም የፕሮፓጋንዳ አቅም መግዣ ለማድረግ በስፋት ሲንቀሳቀሱ ይስተዋላል።

ለዚህም ከአገር ውጪ ሆነ በአገር ውስጥ የሚገኙ በአስተሳሰቡ የተጠለፉ ግለሰቦችን በጋዜጠኝነት ፣ በማህበራዊ አንቂነት ... ወዘተ ስም በማሰለፍ አስተሳሰቡን በሕዝቦች ውስጥ ለማስረጽ ረጅም ርቀት ተጉዘዋል። እንደ አገርና ሕዝብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከበሬታን ያተረፍንባቸውን ማህበራዊ እሴቶቻችንን የሚገዳደሩ ተግባራትን እለት እለት በተናበበ መንገድ ሲፈጽሙም ማየትና መስማት የተለመደ ከሆነ ውሎ አድሯል።

ሕዝብን በሕዝብ ላይ ሆነ ሕዝብን በመንግሥት ላይ ለማነሳሳት ብዙ የሀሰት ትርክቶችን ከመፍጠር ጀምሮ የራሳቸውን የጥፋት ኃይሎች በሕዝቡ ውስጥ በማስረግ የሕዝቦችን ሰላም ከመፈታተን አልፈው አገረ መንግሥቱን ስጋት ውስጥ ለመጨመር ተንቀሳቅሰዋል።

ጽንፈኛ አስተሳሰባቸውን በሕዝብ ላይ ለመጫን ሕሊና ቢስ በሆነ መንገድ የሚንቀሳቀሱ እነዚህ ኃይሎች በተለይም ባለፉት አምስት ዓመታት እንደአገር ብዙ ያልተገቡ ዋጋዎችን እንድንከፍል አስገድደውናል። እነዚህን ኃይሎች ከእስካሁኑ የከፋ ዋጋ እንዳያስከፍሉን አሁን ላይ በቃችሁ ልንላቸው ይገባል። ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነትና ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠር ይጠበቅብናል።

ይህን ማድረግ ባለመቻላችን ለሚፈጠር ማህበረሰባዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስብራት ሆነ የሞራል ውድቀት ማንም ከታሪክ ሆነ ከህሊና ተጠያቂነት ሊያመልጥ አይችልም።

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታተሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍሳችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ስለ ሰው ሰው መሆን ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

የዛሬው ኑሮዋ ከተማ ላይ ቢያቆማትም የማንነቷ ምንጭ የሚቀደው ከገጠሩ ክፍል ነው፡፡ ትውልድና ዕድገቷ ሰሜን ጎንደር ዞን ጭልጋ ወረዳ ልዩ ስሙ «ኩሻይና» ከተባለ ስፍራ ነው፡፡ የአርሶአደር ልጅ ነች። እንደማንኛውም የገጠር ጉብል በአካባቢው ወግና ባህል አድጋለች፡፡

አጸደ ሰማው ለወላጆቿ በወጉ ስትታዘዝ፣ አድጋለች። የገጠር ልጅ ሁሌም የተባለውን ሊሰራ፣ ሊታዘዝ ግድ ነው፡፡ አጸደ ሰማውም ወላጆቿ ለሚሏት ሁሉ ጉልበቷን ሳትሰስት ስታገለግል ቆይታለች፡፡

ልጅነቷ እንደእኩዮቿ ከብት በማገድ ብቻ አላለፈም። ቤተሰቦቿ ባይማሩም ሴት ናት ብለው አልጨከኑባትም፡፡ ዕድሜዋ ሲደርስ ደብተር አስይዘው ትምህርትቤት ላኳት። እሷም ብትሆን አላሳፈረቻቸውም። ዓላማዋን ሳትዘነጋ በርትታ ተማረች፡፡

አጸደ መንገዷን አልሳተችም፡፡ ነገን ከተሻለ ዓለም ለመድረስ ለትምህርቷ ትኩረት ሰጠች፡፡ በዚህ ሁሉ ጥረት ከጎኗ ያልራቁት ወላጆች ያሻትን እየሰጡ፣ የጎደለውን እያሟሉ ከፍላጎቷ አደረሷት፡፡

የአጸደ ሀሳብ በህክምና ሙያ ጠንክራ መዝለቅ ነው፡፡ የእሷ ዓዕምሮ ሁሌም አርቆ ያስባል፡፡ ወገኖቿን በጤናው ዘርፍ ማገዝ፣ መደገፍን ትሻለች፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ ወላጆቿ ያቅማቸውን አድርገዋል፡፡ እስካሁን ከትምህርት ሳያግዷት በወጉ ተምራለች፣ በነጻነት



ተራምዳለች፡፡ ከእንግዲህ ምኞት ፍላጎቷን መሙላት የእሷ ድርሻ ይሆናል፡፡

**ልፋትን በውጤት...**

ያሰበችው ከመሆን አልቀረም፡፡ ትምህርቷን አጠናቃ ኮሌጅ ለመግባት ተዘጋጀች፡፡ የመረጠችው የትምህርት ዘርፍ የፋርማሲስት ሙያን ነበር፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከትውልድ አገሯ ርቃ ቤኒሻንጉል ክልል ተገኘታለች፡፡

አጸደ የያዘችውን ትምህርት በርትታ ቀጠለች፡፡ የልጅነት ህልሟ ዕውን ሲሆን በሙያዋ መስራትን ትሻለች፡፡ ሳይማሩ ያስተማሯትን ቤተሰቦች መደገፍ፣ ማመስገን የቀን ተሌት ህልሟ ነው፡፡ ተመልሳ አገሯ ስትገባ ለታናናሾቿ ምሳሌ መሆን እንዳለባት ታውቃለች።

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ሌሎች የአካባቢው ልጆች በእሷ መንገድ ቢያልፉ ደስታዋ ነው፡፡ ሁሌም ለቤተሰቦቿ አክብሮት አላት፡፡ እነሱ እንደቀድሞው ወግ ባህል በሴትነቷ «ቤት ትዋል፣ ትዳር ትያዝ» ብለው አላገዷትም፡፡ በማጀት ስራ፣ ልጆች በማሳደግ ግዴታ ስር አልጣሏትም፡፡ ለነጻነቷ ነፃነት ሰጥተው፣ ለህይወት ምርጫዋ አብቅተዋታል፡፡

አጸደ በቤኒሻንጉል ክልል የትምህርት ቆይታዋ ከቤተሰብ ተነጥሎ መኖርን አወቀች፡፡ ይህ ጊዜ ራስን ለመቻል፣ ፈተናዎችን ለመቋቋም ዕድል ሰጣት፡፡ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ብዙ ይፈልጋል፡፡ ለዕለት ወጪ፣ ለኑሮ መደጎሚያ ለፍላጎት መሙያ ገንዘብ ማግኘትን ይሻል፡፡ እሷን ጨምሮ በርካታ ተማሪዎች ድጋፍ የሚያገኙት ከወላጆቻቸው እጅ ነው፡፡

አጸደ ለትምህርት ቆይታዋ ብዙ እንደሚጎድላት ታውቃለች፡፡ እስከዛሬ ፍላጎቷን ለመሙላት ቤተሰቦቿ ሲደግፏት ቆይተዋል፡፡ አንዳዴ ግን እነሱን ብቻ «አምጡ» እያሉ ማስቸገሩ ይከብዳታል፡፡ አሳድገው፣ አስተምረው ቁምነገር ካደረሷት ወላጆች ጫንቃ ዛሬም ድረስ ያለመውረዷ ያስጨንቃታል፡፡

**ራስን ስመቻል...**

አሁን ለቆመችበት መንገድ የወላጆቿ እጆች ሰፊ ነበሩ፡፡ እሷ ስትማር የበታች እህት ወንድሞቿ ተከትለዋታል፡፡ እስካሁን በቤት ሳለች የሚያሻትን በእኩል ተጋርታ ከእነሱ መስላ አድራለች፡፡ አሁን ደግሞ ከቤት ስትርቅ የግል ፍላጎቷ ጨምሯል፡፡ ከታናናሾቿ በበለጠ ገንዘብና ቁስ ያስፈልጋታል፡፡

አጸደ ይህ እውነት ሁሌም እያሳሰባት ትጨነቃለች፡፡ አሁን ከቤት ውጭ ሆና የእህት ወንድሞቿን ኢኮኖሚ መሻማት አትፈልግም፡፡ ይህ ጉዳይ ሁሌም ወደ ዓይምሮዋ ሲደርስ «አይሆንም፣ አይደረግም» የሚል ቃልን ሹክ ይላታል፡፡ ይህኔ በይሉኝታ ተከባ በምንይሉኝ ስሜት ስትተከዝ ትውላለች፡፡

እንዲህ ባሰበች ጊዜ ዓይምሮዋ ለውሳኔ ይፈጥናል። እጅ እግሮቿ ለስራ ይሰላሉ፡፡ «እኔ እኮ! ተማሪ ነኝ» የሚለውን ሀሳብ ትተውና ራሷን ለጉልበት ስራ ታዘጋጃለች። ከምትማርበት ትርቃለች፡፡ ዝቅ ብላ በየሰው ቤት ልብስ ስታጥብ፣ በጉልበት ስራ ስትውል መፍራት ማፈርን አታውቅም፡፡

እንዲህ ካልደፈረች ከሰው ጫንቃ አትወርድም። እንዲህ ካልወሰነች ማጣት መንጣቷን አትቅርፍም። በስራ ውሎ የድካሟን ዋጋ ስትወስድ የወላጆቿን ዕዳ እንደከፈለች ይሰማታል፡፡ የእህት ወንድሞቿን ድርሻ ያለመቁረሷ ይታያታል፡፡ ይህኔ ዓይምሮዋ በእርካታ ይመላል፤ የነገ ዕቅድ ውጥኗን በነፃነት እያነሳች ትጥላለች፡፡

ከትናንትናው ... ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## ከአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## የአልኮል መጠጥ ሱሰኝነትና መዘዙ

ሱስ ብዙ የጤና ጉዳቶች እንዳሉት እየታወቀም የሱስ አምጭ ነገሮች ተጠቃሚ በዓለም አቀፍና በአገር አቀፍ ደረጃ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት በተለያዩ አገራት አእምሮን የሚያነቃቁ አደንዛዥ እፆች የሚጠቀሙ ሰዎች ቁጥር በአስገራሚ ሁኔታ ጨምሯል፡፡

አገራችን ኢትዮጵያም ከአደንዛዥ እፅ ጋር ተያይዘው በሚከሰቱ ችግሮች ዋነኛ ተጠቂ ከሆኑት አገሮች አንዷ ስትሆን በማህበረሰብ ጤና ችግር መካከልም የአደንዛዥ እፅ አጠቃቀም ዋናው ጉዳይ እየሆነ መጥቷል፡፡ የችግሩን አሳሳቢነት በመገንዘብ ስለሱስ ባህሪያትና ስለሚያስከትለው ጉዳት ሰፋ ያለ ማብራሪያ በተከታታይ ክፍል የምናስነብብ ሲሆን በዛሬው እትማችን በርካታ ሰዎች ስለተያዙበት የአልኮል ሱስ እንደሚከተለው አዘጋጅተን አቅርበናል።

በተለያዩ ጊዚያት በተደረጉ ጥናቶች 76 ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሰዎች አብዝተው አልኮልን የሚጠቀሙ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ በትንሹ 15 ነጥብ ሶስት ሚሊዮን የሚደርሱ ሠዎች ሱስ አስያዥ ንጥረ ነገሮችን ከመጠቀም ጋር ተያይዞ የአዕምሮ እክል ይገጥማቸዋል። ከገጠር እስከ ከተማ በባሕላዊ መንገድ ከሚዘጋጁት ጠላ፣ ጠጅ፣ እና አረቄን ጨምሮ በዘመናዊ መልክ እስከሚዘጋጁት ድራፍት፣ ቢራ፣ ጅን፤ ውስኪ እና ሌሎችም የአልኮል መጠጥ ዓይነቶችን ህብረተሰቡ እየተጠቀማቸው ይገኛል፡፡ የአልኮል መጠጥ ሱስ ከሚያስይዙ ንጥረ-ነገሮች አንዱ ነው፡፡ በዓለም ላይ በየዓመቱ የሶስት ሚሊዮን ሠዎች ሞት የሚከሰተው አልኮልን ያለአግባብ ከመጠቀም ጋር በተያያዘ ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ የሞት ምጣኔ አምስት ነጥብ 31 በመቶ ይሸፍናል፡፡

በዓለም ላይ ካሉ የበሽታዎች ጫናና ጉዳት ውስጥ አምስት ነጥብ አንድ በመቶ የሚሆነው በአልኮል ምክንያት የሚከሰት ነው፡፡ ከ20 እስከ 39 ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ 13 ነጥብ አምስት በመቶ የሚሆነው ሞት አልኮልን





አብዝቶ በመጠቀም የሚከሰት ነው፡፡ ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች አልኮልን ይወስዳሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ለጊዜ ማሳለፊያነት፣ በጓደኛ ተፅዕኖ፣ ለጊዚያዊ ደስታና በአዕምሮ ህመም ምክንያት የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

**የአልኮል መጠጥ እና ጉዳቶቹ**

ምንም እንኳን የአልኮል መጠጥ በብዙዎቹ ዘንድ ለጊዚያዊ ደስታ እና ለጊዜ ማሳለፊያነት ቢዘወተርም የአልኮል መጠጥ አብዝተው በሚጠቀሙ ሰዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የአካል እና የአይምሮ ጤና ጉዳት፣ የማህበራዊ ኑሮ እና የኢኮኖሚ ችግሮችን ያስከትላል። የአልኮል መጠጥ በአእምሮ ጤና ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት መካከል በዋነኝነት የሚጠቀሱት የድብርት በሽታ፣ የጭንቀትና የመርሳት በሽታ፣ ስንፈተ ወሲብ፣ የእንቅልፍ መዛባትና ለፀብ መዳረግ ይጠቀሳሉ፡፡

የአልኮል መጠጥ አዘውትረው በሚጠቀሙ ሰዎች የጤና ችግሮች ይከሰቱባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል የጉበት፣ የልብ፣ የደም ቧንቧ፣ የጨጓራ በሽታ፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ የቁም ቅዠት፣ የደም ግፊት መጨመር፣ በሽታን የመከላከል አቅም መቀነስ፣ አልኮል ከሚወስዱ እናቶች የሚወለዱ ሕጻናት ላይ የአእምሮ እድገት ውስንነት ማስከተል፣ ላልተገባ እና ልቅ ለሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት በመዳረግ ለኤች አይ ቪ እና ለአባላዘር በሽታዎች መከሠት እንዲሁም መዛመት ምክንያት ይሆናል፡፡

በማሕበራዊ ኑሮ ላይ የሚያደርሰው ችግር

በአልኮል መጠጥ ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮች በተጠቃሚው ላይ ብቻ ተወስነው የሚቀሩ ባለመሆናቸው በቤተሰብ እና በማሕበረሰቡ ላይ የሚከተሉትን ከፍተኛ ችግሮች ያስከትላል፡፡

- የአልኮል መጠጥ የሚጠጡ ወላጆች ለልጆቻቸው መጥፎ አርአያ ይሆናሉ
- ለትዳር መፍረስ እና ለቤተሰብ መበተን ምክንያት ይሆናል
- ልጆች ወደ ጎዳና እንዲወጡ ምክንያት ይሆናል፡፡
- ማሕበራዊ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዳይወጡ ያደርጋቸዋል
- የግል እና የአካባቢ ንፅህናን ያለመጠበቅ ያስከትላል
- የአካባቢን ፀጥታ እና ሠላም ያውካል
- ለህግ እና ደንብ አለመገዛት

የአልኮል ሱስ በማሕበራዊ ኑሮ ላይ ከሚያደርሰው ችግር ባሻገር በኢኮኖሚ ላይ ጉዳት ያስከትላል፡፡ አልኮል አዘውትረው መጠጣት የግለሰቡን ብሎም የቤተሰቡን ኪስ ያራቁታል፤ የስራ ብቃት እና ተነሳሽነትን በማዳከም ምርታማነትን ይቀንሳል፡፡ በመጠጥ ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮች እና ችግሮችን ለማከም የሚወጣው ወጪ በአገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

የአልኮል መጠጥ በድንገት ማቆም የሚያስከትላቸው ችግሮች

የአልኮል ሱስ ችግር ያለባቸው ብዙ ሰዎች አልኮል በሚያቆሙበት ጊዜ ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ ደረጃ የሚደርሱ ችግሮች ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ ከእነዚህም ችግሮች ውስጥ የእጅ መንቀጥቀጥ፣ ማላብ፣ የእንቅልፍ ሰዓት መዛባት፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ እና ማቅለሽለሽ ይጠቀሳሉ፡፡

በአብዛኛው እነዚህ ምልክቶች ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በራሳቸው መንገድ ወይም በህክምና እርዳታ ሊወገዱ የሚችሉ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ አልኮልን በድንገት በማቆም ዴሊርየም ተሬመንስ የተባለ ችግር ሊከሰት ይችላል፡፡ የዚህ አይነት ችግር መገለጫዎቹም የቁም ቅዠት፣ ራስን መሳት ወይም መቆጣጠር አለመቻል፣ አለመረጋጋት፣ የመረበሽ ስሜት፣ መንቀጥቀጥ፣ አካባቢን፣ ሰዎችንና ጊዜን መለየት አለመቻል፣ ከፍተኛ ትኩሳትና ላብ፣ ከእውነታ የራቀ እይታ እና ፍርሃት ናቸው፡፡ ምልክቶቹም መጠጥ ካቆሙ በኋላ ከሶስት እስከ አምስት ባሉት ቀናት ውስጥ የሚከሰቱ ናቸው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለማስቀረት የአልኮል ሱስ ተጠቂው ግለሰብ አልኮል ለማቆም ሲወስን ለጤና ባለሙያ በማማከር ተገቢ የሆነ የህክምና ድጋፍ እንዲደረግለት መጠየቅ አለበት፡፡

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

## የአልኮል መጠጥ ...

ከ16ኛው ገጽ የዞረ

አጻደ ውስጧ ለሰዎች ያዝናል፡፡ የሌሎች መቸገር ማጣት ያሳስባታል፡፡ የመረጠችው የትምህርት ዘርፍ በአንድም በሌላም ከሰብአዊነት ጥግ የሚያደርሳት ነው። ሙያዋን ተጠቅማ ከምትሰጠው መልካምነት ባለፈ ከእሷ ድጋፍን ከሚሹ ወገኖች ጎን ብትቆም ትወዳለች። ይህን ስታስብ የልቧ ሁሉ ይከወናል፡፡ ያቀደችው የሞላ የወጠነችው የተሳካ ይመስላታል፡፡

የቤኒሻንጉሏ ተማሪ አጻደ ትምህርቷን ባሰበችው ጊዜ አጠናቀቀች፡፡ ወደ ቤተሰቦቿ ስትመለስ የህይወቷን ዕቅዶች የማሳካት መንገዷን ጀምራው ነበር፡፡ አሁን በተመረቀችበት ሙያ አካባቢዋን ማገዝ፣ ቤተሰቦቿን መደገፍ ይኖርባታል።

ውሎ አድሮ የወጣቷ ዕቅድ እንደታሰበው ተሳካ፡፡ ለተመረቀችበት ሙያ የሚመጥን ስራ አግኝታ ደሞዝ መቁጠር ጀመረች። አጻደ ዛሬን ለቆመችበት ማንነት ያበቋትን ወላጆች ውለታ አልዘነጋችም፡፡ የልፋት ዋጋቸውን በስራ መንዝራ በተግባር አስመስክራለች፡፡

አጻደ አሁን በሙያዋ ደሞዝ የሚከፈላት ሰራተኛ ሆናለች፡፡ ይህ ውጤት የእሷ ብቻ ሳይሆን የቤተሰቦቿ ጭምር ሆኗል፡፡ ዛሬ ላይ አንገቷን የሚችል ራስ አላት። እንደ ተማሪነት ዘመኗ ከሰው እጅ አትጠብቅም። እንደትናንት ህይወቷ ‹‹ስጡኝ.ለግሱኝ›› ማለትን አትሞክርም፡፡

**አጋጣሚው...**

ከቀናት በአንዱ አጻደ አክስቷን ለመጠየቅ ወደ ባህር ዳር ተጓዘች፡፡ ይህ አጋጣሚ ግን ዘመድ በመጠየቅ ብቻ አልተቋጨም፡፡ በአካባቢው መዘዋወሯ ከእሷ ውስጣዊ ማንነት ጋር ለመገናኘት ምክንያትን ፈጠረ።

በዚህ ቀን እግሮቿ ወደ አንድ ስፍራ አደረሷት፡፡ በቦታው በተገኘች ጊዜ የሰማችው እውነት ከተለመደው ወሬና ጨዋታ ተለየባት፡፡ አጻደ አብሯት የኖረው የሰብአዊነት ስሜት ውስጧን ቢፈትነው ጆሮዋን ሰጥታ በትኩረት አዳመጠች፡፡ አዎ! እየሰማች ያለችው ሀቅ ከእሷ ማንነት ጋር በቀጥታ ይዛመዳል፡፡ ‹‹በጦርነት የተጎዱ ወገኖችን መልሶ ማቋቋምና ማገዝ፡፡ ››

ከጥቂት ዓመታት በፊት በአጻደ የትውልድ አካባቢ ጦርነት ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ በዚህ ጦርነት በርካታ ወገኖች ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡ ቤት ንብረታቸው ወድሞ ለመፈናቀል ተዳርገዋል፡፡ ከነዚህ መሀል በርካቶችን በስራቸው ያስተዳድሩ የነበሩ ባለሀብቶች ጭምር ይገኙበታል፡፡

አጻደ እነዚህን ወገኖች ጨምሮ በርካታ የአካባቢው ነዋሪ በጦርነት ስለመጎዳቱ የዓይን ምስክር ነች። የመለያየት፣ ያለመግባባትን ስር የሰደደ ችግር አሳምራ ታውቃዋለች፡፡ በዚህ መንገድ ባለፈችበት አጋጣሚም ሰው መሆንዋን እስኪትጠላው ተሰምቷት ያውቃል፡፡

በጦርነት እሳት የተማገዱ በርካቶች የአሁን ኑሮ የወደፊት ተስፋ ይሉትን እውነት ይነጠቃሉ፡፡ ህልማቸው ይመክናል፣ ዓላማቸው ይነጥፋል፡፡ እነሱን ከወደቁበት አንስቶ በሁለት እግራቸው ለማቆም ደግሞ የሌሎች እጆች እገዛ ሊኖር የግድ ነው፡፡

አጻደ የባህርዳር ቆይታዋ ያገናኛት ከእንዲህ አይነቱ ሀቅ ጋር ነበር፡፡ መገኛውን አዲስ አበባ ያደረገ ‹‹ወገን ለወገን›› በሚል ስያሜ የተደረጀ ማህበር በእንቅስቃሴ ላይ መሆኑን ሰምታለች፡፡ ደጋግማ ሙሉ መረጃውን ጠየቀች። በቂ ምላሽ አላጣችም፡፡ የማህበሩ ዓላማ በችግር ላይ የሚገኙ ወገኖችን ማገዝና ማቋቋም ላይ ያተኩራል፡፡

አጻደ በአካባቢያዋ የጦርነት ሀሩር ያረፈባቸውን ወገኖች አሰበች፡፡ አብዛኞቹ ከቤት ከቀያቸው ተፈናቅለው ከከፋ ችግር ወድቀዋል፡፡ በዕድሜያቸው መማር ያለባቸው ህጻናት፣ በቤታቸው መኖር፣ መከበር የሚገባቸው አረጋውያንና፣ እናቶች ካላሰቡት መንገድ ውለዋል፡ ፡ እሷ በእነሱ ህመም ስትታመም፣ በሀዘናቸው ስታዝን ቆይታለች፡፡

አጻደ በመቋቋም ላይ ስላለው ማህበር መለስ ብላ አሰበች፡፡ ታላቅ ዕቅዱ ዕውን ይሆን ዘንድ ከጎኑ የቆሙት ጊዜ ጉልበት፣ ዕውቀትና ገንዘባቸውን የሚሰጡ በጎ ፈቃደኛ ወገኖች ናቸው፡፡ አጻደ ይህን ባወቀች ጊዜ ራሷን ለሰብአዊ አገልግሎት አሳልፋ ለመስጠት ወሰነች። አብሯት የኖረው ሰው የመርዳት ማንነቷ ተግባር ላይ የሚውልበት ጊዜው አሁን መሆኑን አመነች፡፡

**ቆራጥ ውሳኔ...**

እንዲህ መሆኑ በገባት ጊዜ ከማንም ሳትመክር በራሷ ውሳኔ አሳለፈች፡፡ ተምራ ከተመረቀች በኋላ በአንድ የግል ድርጅት ተቀጥራ በቂ ደሞዝ እየተከፈላት ነው፡፡ አሁን ከራሷ አልፋ ለሌሎች የምተተርፍበት ጊዜ ላይ ነች፡፡ እንዲያም ቢሆን የእሷ የህይወት ሙላት ብቻ የሌሎችን ጎድሎ እንደማይደፍን ከገባት ቆይቷል። ስራዋን ትታ፣ ቤተሰቦቿን ርቃ የሚጠበቅባትን ግዴታ ልትወጣ ቆርጣለች፡፡

አሁን የአጻደ ውሳኔ በሌሎች ምክር የሚታገዝ፣ የሚደገፍ አልሆነም፡፡ ለሚቀርቧት ሀሳቧን ብታማክር ማንም ‹‹ስራሽን ትተሽ ለበጎፈቃደኝነት ቁሚ›› እንደማይላት ታውቃለች፡፡ ቤተሰቦቿ ከእሷ ብዙ እንደሚሹ አልጠፋትም። አሳድገው፣ አስተምረው ቁምነገር አድርሰዋታል፡፡ ይህ ሁሉ እውነት ግን ከምታስበው ሀያል ጉዳይ በልጦ አልታያትም፡፡

ከጀመረች ጥቂት ጊዚያት በቆጠረችበት ስራ ያስቀመጠችው ብዙ የማይባል ገንዘብ አለ፡፡ ከእንግዲህ ካሰበችው አድርሶ የልቧን ሊሞላላት የሚችለው ቀጭን መስመር እሱ ብቻ ይሆናል፡፡ እቅዷን ለማሳካት የማትሆነው የለም፡፡ ይህን ካደረገች፣ ዓይምሮዋ ያርፋል፣ ውስጧ ይሞላል፡፡

አጻደ የልቧን እቅድ ከመከወን አልታቀበችም፡ ፡ እንዳሰበችው ሆኖ አንድ ቀን ስራዋን አቆመች፡፡ ኳሷን ሸክፋ በእጇ ያለውን ገንዘብ ቆጠረች፡፡ ካሰበችው ዓላማ ያደርሳታል፡፡ ቆራጥ ሀሳቧ ከበጎ ፈቃደኛው ልቧ ተጣምሮ ረጅሙን መንገድ ተያያዘችው፡፡ የት እንደምትሄድ አልጠፋትም፡፡ ተጓዥ እግሯ ከአንድ ግቢ አድርሶ አንድ ዓይነት ዓላማ ካላቸው ነፍሶች ጋር አገናኛት፡፡

**ህይወት በአዲስ አበባ ...**

አጻደና አዲስ አበባ ከተገናኙ ጥቂት ጊዚያት ተቆጥረዋል፡፡ በዚህ ስፍራ ምቾትና ለራስ ማደር ይሉት ዓለም የለም፡፡ እሷን ጨምሮ ሌሎች ለማህበሩ ህልውና የሚታገሉ ወገኖች የአቅማቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡ እንደ ትናንቱ ለሰሩበት፣ ላገለገሉበት ወር ጠብቆ ደሞዝ መጠየቅ አይታሰብም፡፡ ሁሉም የእጁን እያዋጣ ለዕለት ኑሮው፣ ለወደፊት ዓላማው ይታገላል፡፡

አጻደ ‹‹ወገን ለወገኑ ›› የተባለው ማህበር በእግሩ እስኪቆም የሚጠበቅባትን ታደርጋለች፡፡ በሀሳብ በበጉልበት ታግዛለች፡፡ ወደፊት ለሚኖረው ሰብአዊ እገዛ መለመን፣ መጠየቅ ቢኖርባት ወደኋላ አትልም፡፡ እራሷን ለሰብአዊ አገልግሎቶች አዘጋጅታለችና ስለክብሯ አትጨነቅም፡፡

አንዳንዴ አጻደ ስለቤተሰቦቿ ወሬ ትሰማለች፡፡ ሁሉም ስራዋን ትታ ወንዝ አቋርጣ በሄደችበት ጉዳይ አመኔታ የላቸውም፡፡ ከእነሱ የራቀችው ላልተገባ ዓላማ እንደሆነ ያስባሉ፡፡ እነሱ እንዲህ በማሰባቸው አዝናባቸው አታውቅም፡፡ አንድቀን ርቃ የመጣችበትን ዓላማ ሲረዱ እንደሚደሰቱ እንደሚያመሰግኗት ታውቃለች፡፡

አጻደ ያሰበችውን ለማሳካት ዛሬን በቆመችበት መንገድ ብቻ መቀጠል አትሻም፡፡ ሁኔታዎች ሲመቻቹ ትምህርቷን መቀጠል፣ በሙያዋም ማገልገል ትፈልጋለች፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ የምታገኘውን ደሞዝ ለሰብአዊ አገልግሎት የማዋል ዓላማዋ እንደተጠበቀ ይቀጥላል፡፡

**እንዲህም ይኖራል...**

የአጻደ የህይወት መንገድ ከብዙዎቻን ልማዳዊ አቅጣጫ ይለያል፡፡ እሷ ከራስ ጥቅም ይልቅ ለሌሎች የመኖር እውነትን መተግበር ይዛለች፡፡ ይህች ወጣት ህይወትን እየኖረች ያለችው ከራስ ብቻ በመጀመር አልሆነም፡፡ የሌሎች ህመምና ስብራት አስቀድሞ ይሰማታል፡፡ የብዙዎች ለቅሶና ሀዘንም ከልቧ ደርሶ ይፈሳል፡፡

ይህ ስሜት በውስጧ መዝለቁ ማንነቷን ለሌሎች መኖር አሳልፋ እንድትሰጥ አስገድዷል፡፡ ለሰብአዊነት፣ ለበጎነት ዓላማ ማደሯም ከኑሮዋ አንዳች አላጎደለም፡፡ ዛሬም፣ ነገም ስለሰዎች መልካም መሆንን ታስባለች፡፡

እሷ በነዚህ ነፍሶች ፍስሀ ፈጽሞ ኪሳራ አያገኛትም። በየዕለቱ የሚኖራት ትርፍም የመንፈስ እርካታን ያጎናጽፋታል፡፡ ሁሌም የራሷን ዓለም በእፎይታ እንድትገነባና ‹‹ሰው›› ለሚለው ሰብአዊ ፍጡር እንዲህ ሆና እንድትኖር ታድላለችና፡፡

## ኦሮሚያ ክልል

በከሳሽ ቪዥን ፈንድ ማይክሮ ፋይናንስ ጅማ ቅርንጫፍ እና በተከሳሽ 1ኛ ቤዛዊት ተሻለ 2ኛ ገዳ ዳባ መካከል ያለውን የክርክር ጉዳይን አስመልክቶ እነዚህ ተከሳሾች መከሰሳቸውን አውቀው በቀን 22-10-2015 8:30 ቀጠሮ ላይ ቀርበው መልስ ካላቸው ሰጥተው እንዲከራከሩ ካልቀረቡ ደግሞ እነሱ በሌሉበት ክርክሩ ቀጥሎ ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት**

## ሶማሌ ክልል

ባለንብረቱ በአቶ ይነበብ ዘሪሁን ስም የተመዘገበ የሰሌዳ ቁጥር 03-06795 ሱማ የተሸከርካሪው ዓይነት አውቶቢስ የሻንሲ ቁጥር JTGSX23P3A6080808 የሞተር ቁጥር 2TR-8254909 የሊብሬ ቁጥር2383 ከላይ የተጠቀሰው የተሸከርካሪ ባለንብረት የተሸከርካሪ የፊት ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 05/10/2015 ዓ.ም አመልክተዋል ፡፡ የፊት ሰሌዳውን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገባዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን ፡፡

**የሶማሊ ክልል መንግስት የንግድና ትራንስፖርት ቢሮ**

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም :- ኢትዮ ሃይጂኒክ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>የአመልካች አድራሻ:- ወረዳ 07 የቤት ቁጥር. አዲስ, አቃቂ ቃሊቲ, አዲስ አበባ ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር :- LTM/14427/2015<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን:- 21/09/2015 E.C. | | |
| 3 | ምልክት:- | 4 | የምልክቱ መግለጫ:-የቃልና ምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት:- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኝነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ:- 5 እና 9 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች:-<br>የሴቶች ንፅህና መጠበቂያ(ምድብ 5) እና በሐኪም የሚታዘዙ ሌንሶች መነጽሮች/ የእይታ (ምድብ 9) | | |

አመልካቾች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል። ስለሆነም፣ ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን መ/ቤት ካልቀረበ፣ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን። ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል።

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOI-LXXXII No-287 17/10/2015 (24/6/2023)**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የፍ/ባለሙብት ሜታ አቦ ቢራ አ/ማ እና የፍ/ባለዕዳ ግርማ ታደሰ መካከል ስላለው የአፈፃፀም ክስ ጉዳይ ተከሳሽ መከሰስዎትን አውቀው ለ28/10/2015 ዓ.ም. በ8፡00 ሰዓት ፌ/ከ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 10ኛ ፍ/ብሄር 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 405 ቀጥታ ክስ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም እዮብ አለሙ ማሞ የሠሌዳ ቁጥር አአ 02-01 B57305 የተሸከርካሪው ዓይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር TMAJ2811 2LJ983805 ሞዴል Tucson የሞተር ቁጥር G4FD-KZ969698 የሊብሬ ቁጥር 159094/525830 ከላይ የተጠቀሰው የተሸከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር / ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ16/10/2015 ዓ.ም አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገባዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን**
**የቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክ/ከ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር ወ5/58 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0057232827 ዮርዳኖስ ብዙአየሁ እና ጓደኞቻቸው የኮብል ስቶን ንጣፍ ህብ/ሽርክና ማኅበር በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ገቢዎች ሚ/ር አራዳ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ውስጥ ከቁጥር 001 እስከ 250 /5 ፓድ/ ሁሉም ያልተሰራበት ደረሰኝ ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር አራዳ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ዮርዳኖስ ብዙአየሁ እና ጓደኞቻቸው የኮብል ስቶን ንጣፍ ህብ/ሽርክና ማኅበር**

# ስፖርት



## የሻምበል አበበ ቢቂላ ማራቶን ነገ በአዲስ አበባ ይካሄዳል




ውድድሩን የተሳካ ለማድረግ ዝግጅቱ መጠናቀቁን ፌዴሬሽኑ በሰጠው መግለጫ አስታውቋል፤

ዓለማየሁ ግዛው

የታሪካዊውን አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ መታሰብያ የሆነው የማራቶን ውድድር በነገው ለ39ኛ ጊዜ በአዲስ አበባ ይካሄዳል። ውድድሩ ነገ ከጠዋት 12፡00 ጀምሮ መነሻውንና መድረሻውን ሰሚት ለስላሳ ፋብሪካ አካባቢ በማድረግ እንደሚካሄድ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሰጠው መግለጫ አሳታውቋል።

ውድድሩ ለከተማ አስተዳደር፣ ለክለቦችና ለግል ተወዳዳሪ አትሌቶች የአገር ውስጥ የውድድር ዕድል ለመፍጠርና ተተኪ የማራቶን አትሌቶችን ለማፍራት ታስቦ እንደሚካሄድም ተጠቁሟል። በተጨማሪም በክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና ክለቦች መካከል በስፖርቱ ፉክክርን ለመፍጠርና ውድድሩን የሚያሸንፉ አትሌቶችን በሽልማት ለማበረታታት እንደሚካሄድ ተጠቁሟል።

ፌዴሬሽኑ ውድድሩን በጀግናው አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ ስም የሚያካሂደው ጀግናውን አትሌት ለመዘከርና ውጤታማ የማራቶን አትሌቶችን በዘላቂነት ለማፍራት ትልቅ መነቃቃት ይፈጥራል ብሎ ሲሆን፣ በማራቶን ውድድር ትልቅ ስም ያላቸው 12 ክለቦች፣ 2 ክልሎችና 1ከተማ አስተዳደሮ እንደሚሳተፉ ጠቁሟል። በውድድሩ አንጋፋ(ቬተራን) አትሌቶችና የግል ተወዳዳሪ አትሌቶችም የሚሳተፉ ይሆናል።

የአበበ ቢቂላ ማራቶን ለመጀመሪያ ጊዜ 51 አትሌቶች በማፎካከር የተጀመረ ሲሆን ውድድሩን ያጠናቀቁት 27 ብቻ ነበሩ። ውድድሩንም አንደኛ በመውጣት ያሸነፈው አትሌት ሻምበል ከበደ ባልቻ ሆኖ ይታወሳል። 42 ኪሎ ሜትሩን ያጠናቀቀውም በ2 ሰዓት ከ16 ደቂቃ ነበር። በዘንድሮ ውድድር 92 ሴትና 262 ወንድ በድምሩ 354 አትሌቶች በውድድሩ እንደሚሳተፉ የተገለፀ ሲሆን፣ 11 ታዋቂ አትሌቶች የሚያደርጉት ፉክክርም ይጠበቃል።

በሴቶች ዘርፍ ከሚካፈሉት ውጤታማ አትሌቶች አንዷ የሆነችው የኢትዮ ኤሌክትሪኳ ደጊቱ አዝመራው ትጠቀሳለች። ይቺ የማራቶን ውጤታማ አትሌት እአአ በ2019 በሞሮኮ ራባት በተካሄደው መላው አፍሪካ ጨዋታዎች የብርና በተመሳሳይ ዓመት በኔዘርላንድ በተካሄደ የማራቶን ውድድር 1ኛ በመውጣት የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት መሆኗ ይታወሳል። ደጊቱ በ2021 የለንደን ማራቶን 2ኛ ሆና ያጠናቀቀች አትሌት እንደመሆኗ የነገው ውድድር ድምቀት ትሆናለች ተብሎ ይጠበቃል። ወጣቷ አትሌት ጽዮን አበበ፣ብዙአገር አደራው፣ ማሚቱ ባልቻ በነገው ውድድር ጎልተው ከሚጠቀሱ ታዋቂ አትሌቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

በወንዶች መካከል በሚካሄደው ውድድር ወጣቱ ኃይለማርያም ኪሮች ከኢትዮ ኤሌክትሪክ የማሸነፍ ቅድመ ግምት የተሰጠው አትሌት ሲሆን ጽዳት አበጀና ልመንህ ጌታቸውን የመሳሰሉ የርቀቱ ጠንካራ ተፎካካሪዎች ይጠበቃሉ።

ለውድድሩ አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት መጠናቀቁን ፌዴሬሽኑ የገለፀ ሲሆን 1.2 ሚሊዮን ብር ለሽልማትና ሌሎች ወጪዎች በጀት መመደቡም ታውቋል።

በሁለተም ጾታ ከ1ኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ ለሚወጡ አትሌቶች የወርቅ፣ ብርና የነሐስ ሜዳሊያዎችን ከመሸለም በተጨማሪ እንደየደረጃቸው የገንዘብ ሽልማት ይበረከትላቸዋል። በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-8ኛ በመውጣት የሚያጠናቅቁ አትሌቶች በተቀመጠው የሽልማት መጠን እያንዳንዳቸው ሽልማት የሚያገኙ ይሆናል።

ፌዴሬሽኑ ለሽልማት 400ሺ ብር ያዘጋጀ ሲሆን 1ኛ 50ሺ፣ 2ኛ 25ሺና 3ኛ 20ሺ ብር ሽልማት የሚያገኝ ይሆናል። 8ኛ ደረጃን ይዞ የሚያጠናቅቅ አትሌት ደግሞ ዝቅተኛ የተባለውን የ10ሺ ብር ሽልማት የሚወስድ ይሆናል። የገንዘብ ሽልማቱ ለአንጋፋ አትሌቶችም የተዘጋጀ ሲሆን ከ1ኛ-6ኛ ደረጃን ይዘው ውድድራቸውን ለሚያጠናቅቁ የሚሰጥ ይሆናል። በዚህም 1ኛ ለሚወጡት 12ሺ ብር፣ 2ኛ ለሚወጡት 6ሺ ብርና 3ኛ ለሚወጡት 5ሺ ብር ይበረከታል። በሁለቱም ጾታ በቡድን አሸናፊ ለሚሆኑ ደግሞ የዋንጫ ሽልማት እንደሚሰጥ ተገልጿል።

ውድድሩን የሚመሩ በአለም አትሌቲክስ ደረጃ የሰለጠኑ 80 ዳኞች ዝግጅታቸውን ጨርሰዋል።

የሻምበል አበበ ቢቂላ መታሰቢያ ውድድር በ1974 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተጀመረ ሲሆን፤ በየዓመቱ በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች እየተካሄደ አሁን 39ኛ ዓመቱን አስቆጥሯል። በመጀመሪያው ውድድር ኢትዮጵያን ጨምሮ ሦስት አገራት ማለትም ጅቡቲና ሶቪየት ተካፍለዋል። እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ የአበበ ቢቂላ ዓለም አቀፍ ማራቶን ውድድር የሚል ስያሜን በመያዝ የውጭ አገራት አትሌቶችን ተሳታፊ ሲያደርግ ቢቆይም ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ግን ውድድሩ አገራዊ መልክ እንዲይዝና ስያሜውም የሻምበል አበበ ቢቂላ ማራቶን ውድድር በሚል ተሰይሞ እየተካሄደ ዛሬ ላይ ደርሷል።